የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
ADDIS NEGARI GAZETA
OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.80
Addis Ababa 28th Jun, 2024

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር፻፸/፪፻፲፮**
**የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር ደንብ**
**ገፅ.................................................... ፫ሺ፬፻፸፪**

**CONTENT**

**REGULATION No. 170/2024**
**THE ESTABLISHMENT AND OPERATING OF COOPERATIVE SOCIETIES**
**Page..............................................3472**

## ደንብ ቁጥር፻፸/፪፻፲፮

## የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ቀደም ሲል በተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች የተደራጁ ማህበራትን ውጥታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የህብረት ሥራ ማህበራቱን ለመደገፍ፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የወጡ በርካታ መመሪያዎችን ወደ አንድ ሰብሰብ በማድረግ ለአፈጻጸም ምቹ፣ ግልጽ እና ለሕብረት ሥራ ማህበር አባላት በቀላሉ ተደራሽ መሆን የሚችል ደንብ አድርጎ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## REGULATION No. 170/2024

## THE ESTABLISHMENT AND OPERATING OF COOPERATIVE SOCIETIES

**WHWREAS,** it has been found necessary to ensure as a legal framework for effectiveness of the cooperative societies previously organized in different types of societies in Addis Ababa City Administration Cooperative Society Commission;

**WHEREAS,** it is has been found necessary to issue clear and easily accessible regulation to the members of the cooperative societies bring together several directives to support, monitor and control the cooperative societies that is convenient for implementation;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪፻፲፮ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃትና አሰራር ደንብ ቁጥር ፻፸/፪፻፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩ **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪ **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫ **"አዋጅ"** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፱፹፭/፪ሺህ፰ ነው፤

፬ **"ኮሚሽኑ"** ማለት የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ነው፤

፭ **"ጽህፈት ቤት"** ማለት እንደአግባብነቱ የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ የኅብረት ሥራ ጽህፈት ቤት ነው፤

፮ **"የኅብረት ሥራ ማህበር"** ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እና በተናጠል ሊፈቱ ያልቻሏቸውን ችግሮች በጋራ ለማቃለል ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት የሚያቋቁሙት፣ በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሠረት የሚመሩትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚቆጣጠሩት ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023 the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this regulation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This regulation may be cited as "The Establishment and Operating of Cooperative Societies Regulation No. 170/2024".

**2. Definition**

In this regulation, unless the context requires otherwise:

1. "**City**" means the Addis Ababa City.
2. "**CityAdministration**" means Addis Ababa City Administration;
3. "**Proclamation**" means Cooperative Societies Proclamation No. 985/2016;
4. "**The Commission**" means the Cooperative Society Commission;
5. "**Office**" means the Sub-City or District Cooperative Society Office, as the case may be;
6. "**Cooperative Society**" means an autonomous cooperative society having legal personality and democratically controlled by persons united voluntarily to meet their common economic, social and cultural needs and other aspirations, which could not addressed individually, through an enterprise jointly owned and operated on the basis cooperative society principles;

፯ **"የሙያ ኅብረት ሥራ ማህበር"** ማለት የተለያዩ ሙያን መሰረት በማድረግ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፰ **“ውህደት”** ማለት በንብረት ባለቤትነት ፣ በአስተዳደር ፣ በሥራ አካባቢ ፣ በስያሜ እና የተለያዩ ህጋዊ ሰውነት የነበራቸውን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት አንድ ጠንካራ ኅብረት ሥራ ማህበር ለመመስረት የሚያደርጉት መቀላቀል ውህደት ነው፤

፱ **“የኅብረት ሥራ ማህበራት መከፈል”** ማለት በንብረት ባለቤትነት፤ በአስተዳደር፤ በሥራ አካባቢ፤ በስያሜ፤ አንድ የህጋዊ ሰውነት የነበረውን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት መክፈል ነው፤

፲. **“የንግድ ሥራ ዕቅድ”** ማለት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራውን ሲጀምር ወይም ሲያስፋፋ ለሚያደርገው የሥራ እንቅስቃሴ እንደ ፍኖተ ካርታ የሚጠቀምበት ዕቅድ ነው፤

፲፩ **"መተካካት"** ማለት በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር እና በጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር ውስጥ አባላት በተለያየ ምክንያት መቀጠል ሳይችሉ ሲቀሩ በእነሱ ቦታ ሌላ ተክተው መብትና ግዴታቸውን በማስተላለፍ የሚወጡበት ሂደት ነው፤

፲፪ **"የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር"** ማለት በጋራ ህንጻ ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸/፩ሺህ፱፻፺፭ መሰረት የተቋቋመ የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤቶች ማህበር ነው፤



7. "**Professional Cooperative Society**" means a cooperative society organized on the basis of various professions;
8. "**Amalgamation**" means the amalgamation of two or more cooperative societies with different ownership, management, working environment, name and legal personality to form one strong cooperative society;
9. "**Division of Cooperative Societies**" means ownership of property, in administration, in the work environment, splitting what used to be one legal entity into two or more cooperative societies;
10. "**Business Plan**" means a plan that the cooperative society uses as a roadmap for its business activities when starting or expanding its business;
11. "**Replacement**" means a process in housing cooperative societies and condominium owners' societies, when members are unable to continue for various reasons, they are replaced by others and their rights and obligations are transferred;
12. "**Condominium Owners Society**" means the societies of condominium owners established under the Common Building Ownership Proclamation No. 370/2003;

፲፫ "**የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር**" ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ያላቸውን ጉልበት፣ ሀብትና እውቀት በጋራ በማንቀሳቀስ ያሉባቸውን የመኖሪያ ቤት ችግሮች ለመፍታትና የሚያስፈልጓቸውን ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ የሚደራጁ ናቸው፤

፲፬ "**የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር**" ማለት የቁጠባ፣ የብድር እና የብድር የሕይወት መድን አገልግሎቶችን ለአባላቱ ለመስጠት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፲፭. "**ቁጠባ**" ማለት አንድ አባል ከሚያገኘው ገቢ ላይ ቀንሶ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያጠራቅመው ገንዘብ ነው፤

፲፮ "**ብድር**" ማለት አንድ አባል ወይም ኅብረት ሥራ ማህበር የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመው ከአንድ ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም ከሌላ ህጋዊ አካል ጋር በሚኖር የውል ስምምነት መሰረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተወስዶ ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ ነው፤

፲7. "**የብድር ህይወት መድን ዋስትና**" ማለት ከኅብረት ሥራ ማህበር ብድር የወሰደ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ብድሩን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ሳይጨርስ በሞት ቢለይ ቀሪውን ብድር ለመክፈል የሚሰጥ የመድን ዋስትና ነው፤

፲8. "የገቢ ማስገኛ ተቋማት" ማለት በሕግ ወደ ሸማች የኅብረት ሥራ ማህበራት የተዘዋወሩ ሆነው ለአባላትና ለህብረተሰቡ ተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ እንደ መዝናኛ ክበባት፣ ወፍጮ ቤቶች፣ ሥጋ ቤቶች፣ መጋዘኖች፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ ተከራይተው ያሉ ቤቶችና ሌሎች ገቢ የሚያስገኙ ተቋማት ናቸው፤

**Housing Cooperative Society**" means people organized by the commission or the office to solve their housing problems and get the related services they need by mobilizing their energy, wealth and knowledge to build housing voluntarily;

13. "**Savings and Loan Cooperative Society**" means a cooperative society formed to provide savings, loan and credit life insurance services to its members;
14. "**Savings**" means the money saved by the cooperative society according to the bylaws of the cooperative society, deducted from the income earned by a member.
15. "**Loan**" means money that is taken and returned within a certain period of time when a member or cooperative society has a shortage of funds according to a contractual agreement with a cooperative society or other legal entity;
16. "**Loan Life Insurance**" means an insurance given by a cooperative society to its members to cover loan taken by a deceased member before full repayment of debt;
17. "**Income-Generating Institutions**" means those institutions that have been transferred to consumer cooperative societies by law and provide various services to members and the community, such as entertainment clubs, mills, butchers, warehouses, sports venues, restaurants, bars, rented houses and other income-generating institutions;

፲፱. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳. በአዋጁ የተደነገጉ የቃላትና የሀረጎች ትርጉም ለዚህ ደንብ ያገለግላሉ፤

፳፩. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያየ ዓይነት እና ደረጃ በተደራጁ እና በሚደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት አመሠራረት እና የአመሠራረት ሂደት</u>

**፬. <u>ስለ ኅብረት ሥራ ማህበር አመሠራረት</u>**

የአዋጁ አንቀጽ ፯ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲመሠረቱ በአንድ በተወሰነ የመኖሪያ ወይም በሥራ ክልል የሚኖሩ ወይም የሚሰሩ ወይም በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩና ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ሆኖ የአባላት ብዛት እንደየ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነትና አደረጃጀት መነሻ ቁጥር አዋጁን መሰረት አድርጎ ይደራጃል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ቁጥራቸው ከ፶ በታች ያነሱ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የኢኮኖሚ አዋጭነት በማጥናት የአባላትን ቁጥር መነሻ ሊያሻሻል ይችላል፤ ሆኖም የመነሻ ቁጥሩ ከ ፲ ማነስ የለበትም፤

፫. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት በግል በመንቀሳቀስ ሊያገኙት የማይችሉትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማግኘት በፍቃደኝነት አባል የሚሆኑበትና የሚመሠርቱት ኅብረት ሥራ ማህበር ሆኖ አባላት ሊያገኙት ከሚፈልጉት ጥቅም አንፃር ሊደራጁ ይችላሉ፤

18. "**Person**" shall mean any physical or juridical person;
19. The definitions of words and phrases defined in the proclamation shall apply to this regulation
20. In this regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This regulation shall apply to Cooperative Societies established in different types and levels in Addis Ababa city administration.

## <u>PART TWO</u>
## <u>FORMATIONS AND FORMATION PROCESS OF COOPERATIVE SOCIETIES</u>

**4. <u>Formations of a Cooperative Society</u>**

Subject to the provisions of article 7 of the proclamation:

1. When primary cooperative societies are established, the number of members who live or work in a certain area of residence or work, or are engaged in the same profession and have similar interests, is organized according to the type and organization of the cooperative society based on the starting number of the proclamation;
2. Despite the provisions of sub article (1) of this article, the number of cooperative societies whose number is less than 50 may be revised by studying the economic viability of the starting point of the number of members, however, the starting number should not be less than 10;
3. The members of the cooperative society can be organized in terms of the benefits that the members want to obtain as a cooperative society that they voluntarily become members of and establish in order to obtain economic and social services that they cannot obtain by acting individually;

፬. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የአባላትን ፍላጎት ለማርካት በሚያደርገው አደረጃጀት በንግድ ሥራ ዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ሊያደርግ የሚፈልገውን የሥራ ዘርፍ መፈፀም ይችል ዘንድ የአባላትን አቅም ያገናዘበ የመነሻ ካፒታል ያስፈልገዋል፤

፭. በዚህ ደንብ መሰረት የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሙያ ብቃት በሚጠይቁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች ላይ ሁሉም አባላት በተናጠል ከሚመለከተው አካል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፭. **የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት**

፩. የአዋጁ አንቀጽ ፯ ድንጋጌ እንተጠበቀ ሆኖ ተመሳሳይ ዓላማና ተግባራት ያላቸው ግለሰቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር መደራጀት ይችላሉ፤

፪. በአዋጁ አንቀፅ ፳፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የከተማው ነዋሪ የሆነና በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ በኅብረት ሥራ ማህበር መደራጀት ይችላል፤

፫. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገ ቢኖርም ኗሪነቱ ከአዲስ አበባ ውጭ የሆነ ሰው ሊደራጅ አይችልም፤

፬. ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጥያቄ በጽሑፍ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚመዘገብበት ጊዜ ድረስ ተገቢውን የሙያ ድጋፍ መስጠት አለበት፤

፭. ማንኛውም ሰው እራሱ ምርት በማምረት ስራ ላይ እስካልተሳተፈ ድረስ አባላት በቀጥታ ምርት በማምረት በሚሳተፉባቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ መደራጀት አይችልም፤

4. In order to satisfy the needs of the members, the cooperative society needs an initial capital that considers the capacity of the members in order to be able to carry out the work it wants to implement according to the business plan;
5. In the cooperative societies organized according to this regulation, all members must submit a certificate of professional qualification from the relevant body.

5. **Establishment of the Primary Cooperative Society**

1. Subject to the provisions of article 7 of the proclamation, individuals with similar objectives and activities can organize themselves in a primary cooperative society to solve their social and economic problems together;
2. Subject to the provisions of article 24 of the proclamation, any resident of the city who is employed in government and non-government institutions in the city administration can organize a cooperative society;
3. Notwithstanding the provisions of sub article (1) and (2) of this article, a person whose residence is outside of Addis Ababa cannot be organized;
4. The commission or the office must provide appropriate professional support from the time the cooperative society's request is received in writing until the time of registration;
5. Any person cannot be organized in cooperative societies where members directly participate in production unless he is involved in production

፮. ሴቶች ወይም ወጣቶች ወይም አካል ጉዳተኞች ከሚሰሩት ልዩ የሥራ ባህሪ በመነሳት ችግሮቻቸውን ለመፍታት የማህበራዊና የኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናትን መሠረት በማድረግ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በፍላጎታቸው ለብቻቸው ሆነው ሊደራጁ ይችላሉ፤

፯. የሚሰሩበትን ቦታ መሰረት አድርገው የሚደራጁ ማህበራት የሚመዘገቡት መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ ይሆናል፤

፰. ማንኛውም የቅጥር ሠራተኛ የሚጠበቅበትን የአባልነት ግዴታ በመወጣት በተቀጠረበት መሠረታዊ ማህበር ውስጥ አባል መሆን ይችላል፤

፱. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፰) የተደነገገው ቢኖርም በህብረት ስራ ማህበር ውስጥ የቅጥር ሠራተኛ ሆኖ በኮሚቴ አባልነት ከተመረጠ ሠራተኛነቱን ይለቃል፡፡

፮. <u>**የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አደረጃጀት**</u>

በአዋጁ አንቀፅ ፳፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

፩ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የዩኒዬን አባል ለመሆን በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የተደራጀና ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆን አለበት

፪ ኮሚሽኑ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በጽሑፍ ጥያቄ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚመዘገብበት ጊዜ ድረስ ተገቢውን የሙያ ድጋፍ መስጠት አለበት፣

፫ ኮሚሽኑ የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ብቻውን ሊሰራው የማይችለው ተግባር መኖሩ በጥናት ሲያረጋግጥ በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የኅብረት ሥራ ዩኒዬን እንዲደራጅ ሊያደርግ ይችላል፤

6. Based on the social and economic feasibility study to solve their problems based on the special nature of the work done by women or youths or people with disabilities, they can be independently organized according to their needs in various fields;
7. Cooperative societies organized based on their place of work will be registered in the District or Sub-City where the office is located;
8. Any employee can become a member of the primary union in which he is employed by fulfilling the required membership obligations;
9. Notwithstanding the provisions of sub article (8) of this article, if he is elected as a member of the committee as an employee in a cooperative society, he shall resign as an employee.

6. <u>**Establishment of Cooperative Societies Union**</u>

Subject to the provisions of Article 24 of the proclamation:

1. Any primary cooperative society must be organized and have a legal personality in the city administration to be a member of the union;
2. The commission must provide appropriate professional support from the time the cooperative society makes a written request to the time of registration;
3. When the commission confirms that there is a task that cannot be done by the primary cooperative society alone, it may organize the cooperative society union based on the need;

፬ እያንዳንዱ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር ከጠቅላላ ካፒታሉ ፳፭ በመቶ ያህል ዕጣ ለመግዛት ፈቃደኛ መሆን አለበት፤

፭ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባላት በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ተመዝግበው የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ መሆን አለባቸው፤

፮ ኮሚሽኑ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለመደራጀት የፍላጎት ጥያቄ ሲቀርብለት ከምስረታው አስቀድሞ የአዋጪነት ጥናት በማካሄድ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለመመስረት ፈቃደኛ የሆኑ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል የመሆን ጥያቄው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መፅደቅ አለበት፤ ዩኒዬኑም ለምዝገባ በሚቀርብበት ወቅት የጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቃለ-ጉበኤ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፤

፰ ከዩኒዬኑ ጋር ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ያለው ማንኛውም መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ዩኒዬኑ ከተመሰረተ በኃላ አባል መሆን ይችላል፤

፱ በአንድ የሥራ ክልል ተመሳሳይ አላማና ተግባር ላይ የተሰማሩ ከአንድ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ማቋቋም አይቻልም፡፡

## ፯. የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አደረጃጀት

፩ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ዩኒዬን የፌደሬሽን አባል ለመሆን በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የተደራጀና ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው መሆን አለበት፤

፪ ኮሚሽኑ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች አቅም በላይ የሆኑ ተግባራት መኖራቸውን በጥናት ሲያረጋግጥ በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን እንዲደራጅ ሊያደርግ ይችላል፤

፫ እያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ዩኒዬን ከጠቅላላ ካፒታሉ ፴ በመቶ ያህል ከፌደሬሽኑ ዕጣ ለመግዛት ፈቃደኛ መሆን አለበት፤

4. Each primary cooperative society must be willing to purchase 25 percent of its total capital;
5. The members of the cooperative societies union must be registered with the commission or the office and obtain a certificate of legal personality;
6. When the commission is asked to organize a union by cooperative societies, it should confirm by conducting a feasibility study before the establishment;
7. The request to become a member of the primary cooperative societies that are willing to form the cooperative societies union must be approved by a special resolution of the general assembly, the union must submit a report of the special resolution of the general assembly to the commission when applying for registration;
8. Any primary cooperative society that has the same objective and function as the union can become a member after the union is established;
9. It is not possible to establish a union of more than one cooperative society engaged in the same objective and function in the same work area.

## 7. Establishment of Cooperative Societies Federation

1. Any cooperative society union must be organized and given legal personality in the city administration to be a member of the federation;
2. When the commission confirms that there are activities that are beyond the capacity of the cooperative society unions, it may organize a federation of cooperative societies based on the need;
3. Each cooperative society union must be willing to purchase 30 percent of its total capital from the federation;

፬. የኅብረት ሥራ ዩኒዬኖቹ ተመዝግበው የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ መሆን አለባቸው፤

፭. ኮሚሽኑ በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለመደራጀት ጥያቄ ሲቀርብለት ከምስረታው አስቀድሞ የአዋጪነት ጥናት በማካሄድ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

፮. የኅብረት ሥራ ፌደሬሽን ለመመስረት ፈቃደኛ የሆኑ የኅብረት ሥራ የኒዬኖች ፍቃደኝነታቸውን በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ማስጸደቅ አለባቸው፤ ፌደሬሽኑ ለምዝገባ በሚመጣበት ወቅት የጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቃለ-ጉባኤን ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፯. ከፌደሬሽኑ ጋር ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ያለው ማንኛውም ዩኒዬን ፌደሬሽኑ ከተመሰረተ በኃላ አባል መሆን ይችላል፤

፰. ማንኛውም መሰረታዊ ማህበር በተደራጀበት አካባቢ ተመሳሳይ ዓላማ ያለው ዩኒዬን ባለመኖሩ በዩኒዬን ያልተደራጀ መሰረታዊ ማህበር ካለ በቀጥታ የፌዴሬሽን አባል ለመሆን ይችላል፡፡

፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) የተደነገገው እንደተጠቀበ ሆኖ ከዚህ ቀደም በኅብረት ሥራ ዩኒዬን አባል የሆነ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር ከዩኒዬን አባልነት ወጥቶ የፌዴሬሽን አባል መሆን አይችልም፤

፲. በተመሳሳይ ዓላማና ተግባራት ላይ የተሰማሩ ከአንድ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ሊደራጁ አይችሉም፡፡

፰. **<u>በኅብረት ሥራ ማህበር የመደራጀት ጥያቄ አቀራረብ</u>**

፩. በመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት የአባላት የጥያቄ አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

4. The cooperative society unions must be registered and obtain a certificate of legal personality;
5. When the commission is asked to be organized by the federation of cooperative societies, it should confirm by conducting a feasibility study before its establishment;
6. Cooperative society unions willing to establish a cooperative society federation must approve their consent through a special resolution of the general assembly, the federation must submit the minutes of the special resolution of the general assembly to the commission at the time of registration;
7. Any union that has the same objective and function as the federation can become a member after the federation is established;
8. Any primary cooperative society union can become a member of the federation if there is a primary cooperative society union that is not organized by the union because there is no union with the same objective in the area where it is organized.
9. Subject to the provisions of sub article (8) of this article, a primary cooperative society that was previously a member of the cooperative society union cannot withdraw from the union and become a member of the federation;
10. More than one federation of cooperative societies engaged in the same objectives and activities cannot be organized in the city administration.

8. **<u>Presentation of Request to Established a Cooperative Society</u>**

   1. The request of members to be established in a primary cooperative society will be as follows:

ሀ) በመኖሪያ አካባቢ፣ በሥራ ቦታ፣ ተመሳሳይ የሙያ ችሎታ መደራጀት የሚፈልጉ ግለሰቦች ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በአካል ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ፤

ለ) ኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት እያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ማህበር የተደራጁን ግለሰብ መታወቂያ ፎቶ ኮፒ፣ ስም እና የተደራጁን ግለሰብ ፊርማ ያቀርባል፤

ሐ) በልዩ የሙያ መስክ የተደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት እሴት ጨምረው ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የጥራት ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ምስክር ወረቀት ወይም ደብዳቤ ሊኖራቸው ይገባል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሐ) ላይ የተጠቀሰው የሙያ ብቃት እንዲቀርብ የሚጠየቀው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያወጡ በሚያስገድዱ የሥራ መስኮች ብቻ ላይ ይሆናል፤

ረ) በመደራጀት ጥያቄ ላይ የጋራ መግባባት ሲደረስ የመሥራች ኮሚቴ ይቋቋማል፤

፪ የግለሰብ የአባልነት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅፅ የሚከተሉት ይዘቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ሙሉ ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜ፤

ለ) የትምህርት ደረጃ፤

ሐ) አድራሻ፤

መ) የሥራ ዓይነት፤

ሠ) የሚደራጅበት ዓላማ፤

ረ) ማመልከቻው የቀረበበት ቀንና ፊርማ፤



a) Individuals who want to be organized in their residential area, workplace, or similar professional skills shall submit their requests to the commission or the office in person or through their representatives;

b) According to the form prepared by the commission or the office, each cooperative society shall submit a photocopy of the identity of the organized individual, name and signature of the organized individual;

c) Cooperative societies organized in a special professional field must have a certificate or letter from the relevant body confirming the quality of the value-added products they produce or the services they provide;

d) The professional qualification referred to in sub article (1) of this article, ordinary letter (c), is required to be submitted only in the fields of work that require the issuance of a professional qualification certificate;

e) When a consensus is reached on the question of cooperative society, a founding committee will be established;

2. The individual membership application form shall have the following contents:
   a) Full name, gender, age;
   b) Level of education;
   c) Address;
   d) Type of work;
   e) The objective for which it is established;
   f) Date and signature of the application;

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በነባር ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ የአባልነት ጥያቄ የሚቀርብ ከሆነ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ባዘጋጀው የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሠረት ሊቀርብ ይችላል፤

፬ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለመደራጀት ጥያቄ የሚያቀርቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም ዩኒዬኖች ጥያቄ የሚከተሉትን በማሟላት ይሆናል፡-

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የፀደቀና በኅብረት ሥራ ማህበሩ ማህተም የተረጋገጠ ቃለ-ጉባኤ ኮፒ ሲቀርብ፤

ለ) አመልካች ኅብረት ሥራ ማህበራት በተመዘገቡበት ኮሚሽኑ ዘንድ በመቅረብ የሊቀ-መንበር ወይም የተወካይ ስም እና ፊርማ ያረፈበት የጥያቄ ማቅረቢያ ቅፅ ሲሞላ ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የዘመኑን የኦዲት ሪፖርት የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ ሲቀርብ፤

መ) ኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ የመደራጀት ጥያቄ በፅሁፍ እንደደረሰው ማመልከቻውን በአግባቡ በማየት ጥያቄው ተገቢነት እንዳለው በማረጋገጥ የምስረታ ሂደቱን መጀመር አለበት፤ኮሚሽኑ የቀረበለትን ማማልከቻ ከገመገመ በኃላ ጥያቄው በጠቅላላ ጉበኤው ልዩ ውሳኔ መሰረት ፀድቆ መምጣቱን ያረጋግጣል፣

ረ) ኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ የመደራጀት ጥያቄውን የማይቀበል ከሆነ በአምስት ቀናት ውስጥ ምላሹን ጥያቄውን ላቀረበው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፤

3. Subject to the provisions of sub article (2) of this article, if a request for membership is made in an existing cooperative society, it may be submitted according to the membership application form prepared by the primary cooperative society;

4. Cooperative societies and unions applying to be organized as a cooperative societies union or a federation of cooperative societies must complete the following:

a) When a copy of the meeting minutes approved by the general meeting and sealed by the seal of the cooperative society is submitted;

b) When applicant cooperative societies are registered with the commission and fill in the request submission form with the name and signature of the chairman or representative,

c) When the cooperative society's current audit report and profit and loss statement is submitted along with the application;

d) Once the commission or the office receives a request for establishment in writing, it must review the application properly and confirm that the request is appropriate and start the formation process;

e) If the commission or the office does not accept the request for establishment, it will notify the response in writing to the party that submitted the request within five days;

ሰ) በዩኒዬንና በፌዴሬሽን ለመደራጀት ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተመሠረተ ሦስት ዓመት የሞላው መሆን አለበት፤

ሸ) ከምስረታ በኋላ ሌሎች ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው እና የመተዳደሪያ ደንብ ግዴታዎችን ተቀብሎ ለመፈፀም ፈቃደኛ የሆኑ መሰረታዊ ወይም ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በአባልነት ሊታቀፉ ይችላሉ፡፡

፱. <u>መሥራች ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የምስረታ ሥራ ለማቀላጠፍ ሲባል ፭ ወይም ፯ አባላት ያሉት የመሥራች ኮሚቴ ይመሰረታል፤

፪ ፫ ወይም ፭ የሚሆኑ የመሥራች ኮሚቴ አባላት ከመሥራች አባላት መካከል በቀጥታ የሚመረጡ ይሆናሉ፤ ከሚመረጡት የመሥራች ኮሚቴ አባላት ውስጥ ግማሽ የሚሆኑ ሴቶች እና ወጣቶችን በመሥራች ኮሚቴ አባልነት ሊያካትት ይችላል፤

፫ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል እና ከኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ የሚወከሉ ሁለት አማካሪዎች ከኮሚቴው ጋር የሚሰሩ ይሆናል፤

፬ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ እና ሌሎች አባላት ይኖሩታል፤

፭ የመሥራች ኮሚቴ አባላት የሚሆኑት በኅብረት ሥራ ማህበር መቋቋም ላይ ተነሳሽነት ያላቸው፣ ውሳኔ የመስጠት ብቃት ያላቸው እና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሆኖ የኮሚቴው ሰብሳቢ ከተመሰረተው የመሥራች ኮሚቴ አባላት መካከል የሚመረጥ ወይም የሚወከል ይሆናል፤

፮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚመሰረተው የመሥራች ኮሚቴ ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ ላሉ አደረጃጀቶች በተመሳሳይ መልኩ የሚመሰረት መሥራች ኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፤

f) Any cooperative society that submits a request to be established by the union and federation must be three years since its establishment;

g) After formation, other primary or cooperative society unions with similar interests and willing to accept and fulfill the obligations of the bylaws may be included as members.

9. **<u>Establishing a Founding Committee</u>**

1. A founding committee of 5 or 7 members will be established to facilitate the establishment of cooperative societies;
2. 3 or 5 founding committee members will be directly elected from among the founding members, half of the elected members of the founding committee may include women and youth as members of the founding committee;
3. The committee will be composed of two advisers representing the stakeholder directly concerned and the commission or its office;
4. The committee will have a chairman, deputy chairman, secretary and other members;
5. The members of the founding committee are those who are motivated to establish a cooperative society, have the ability to make decisions and are accepted by the community, and the chairperson of the committee will be chosen or represented from among the members of the founding committee;
6. The founding committee established under sub article (1) of this article shall have the members of the founding committee established in the same manner as for organizations above primary cooperative societies

፯ ከመሠረታዊ የኀብረት ሥራ ማህበራት በላይ ላሉ አደረጃጀቶች የሁሉም መሥራች ኀብረት ሥራ ማህበራት መሥራች ኮሚቴ አባላት ወይም ተወካዮች ያሉበት መሥራች ኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፤

፰ መሥራች ኮሚቴው ለሚያከናውነው የሥራ ወጪ የመሥራች አባላት በሚያዋጡት ገንዘብ የሚሸፈን ሆኖ ከምስረታ በኋላ ለኀብረት ሥራ ማህበሩ በሚቀርብ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ እንዲተካላቸው ይደረጋል፤

፱ መሥራች ኮሚቴው በአካባቢው ጊዜያዊ የመሥሪያ ቦታ ሊያመቻች ይችላል፡፡

**፲. <u>የመሥራች ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

መሥራች ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፦

፩ አባል ለመሆን ጥያቄ ላቀረቡ እና ለሌሎች ግለሰቦች ወይም ኀብረት ሥራ ማህበራት መረጃ ይሰጣል፤ግንዛቤ ይፈጥራል፤

፪ አባል ለመሆን ፍላጎት ያላቸውንና ፈቃደኛ የሆኑትን ግለሰቦች ወይም ኀብረት ሥራ ማህበራት ይመዘግባል፤

፫ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፤

፬ ከ ፫ - ፭ ዓመት ኀብረት ሥራ ማህበሩ የሚመራበት የንግድ ሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ያፀድቃል፤ኮሚሽኑ ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፤

፭ አባል ለመሆን የተመዘገቡ ግለሰቦችን ወይም የኀብረት ሥራ ማህበራት የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ተወካዮችን ለምስረታ ጉባኤ ስብሰባ ይጠራል፤

7. For establishments beyond the primary cooperative societies, there will be a founding committee consisting of founding committee members or representatives of all founding cooperative societies;
8. The expenses of the founding committee will be covered by the funds contributed by the founding members and they will be replaced based on the evidence submitted to the cooperative society after establishment;
9. The Founding Committee may arrange a temporary office in the area.

10. **<u>Duties and Responsibilities of the Founding Committee</u>**

The Founding Committee will have the following duties and responsibilities:

1. Provides information to applicants and other individuals or cooperative societies, creates awareness;
2. Registers individuals or cooperative societies who are interested and willing to become members;
3. Conducts socio-economic feasibility studies;
4. Develops a business plan to guide the cooperative society for 3-5 years, approve, draft bylaws based on the model bylaws prepared by the commission;
5. Calls the executive committee or representatives of individuals or cooperative societies who have registered to be members to a meeting of the founding assembly;

፮ በምስረታ ጉባኤው ላይ ከተገኙት መካከል የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ለመምረጥ ሶስት አባላትን የያዘ አስመራጭ ኮሚቴ ያስመርጣል፤

፯ ለምስረታው የሚውል ፈንድ የማፈላለግ ሥራ ያከናውናል፤

፰ የአዋጭነት ጥናት መነሻ በማድረግ የመመዝገቢያ እና የዕጣ መጠንና ዋጋ በጉባኤ ያፀድቃል፤

፱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አድራሻ መነሻ በማቅረብ በጉባኤው እንዲሰየም በማድረግ ያፀድቃል፤

፲ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ የሚቀመጥበት የሂሳብ አካውንት የሚከፈትበትን ባንክ ያስወስናል፤

፲፩ በእጁ የሚገኙትን የአዋጭነት ጥናት፣ የንግድ ሥራ ዕቅድ፣ በጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ፣ ቃለ-ጉባዔ እና ሌሎች ሰነዶች ለተመረጡ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ያስረክባል፡፡

፲፩ **<u>የምስረታ ጉባኤ ለማካሄድ አባላትን ስለመጥራት</u>**

፩ መሥራች ኮሚቴው የቅድመ ዝግጅት ሥራውን እንዳጠናቀቀ በአምስት የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ በአባልነት የተመዘገቡት ግለሰቦች ወይም ተወካዮች በተገኙበት የምስረታ ጉባኤ ስብሰባ መጥራት አለበት፤

፪ ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የመደራጀት ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦች ቢያንስ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሚካሄደው የመሥራች ስብሰባ ላይ መገኘት አለባቸው፤

6. A selection committee consisting of three members will be selected to select the management committee, control committee and other sub-committees from among those present at the founding meeting;
7. It will carry out the work of finding funds to be used for the establishment;
8. Based on the feasibility study, the amount and price of registration and lots will be approved by the general assembly;
9. It approves the name and address of the cooperative society by presenting it to be named by the assembly;
10. The cooperative society will determine the bank where the bank account will be opened.
11. He submits the feasibility study, business plan, management bylaws approved by the general meeting, meeting minutes and other documents to the elected management committee or board of the cooperative society.

11. **<u>Calling Members to hold a Founding Meeting</u>**

1. As soon as the founding committee has completed its preparatory work, within five working days, it must call a founding assembly meeting attended by the individuals or representatives who have registered as members;
2. At least two-thirds of the individuals who have submitted a request to organize a primary cooperative society must be present at the founding meeting;

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለመመስረት ለአባልነት ጥያቄ ያቀረቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወካዮች ቢያንስ ሁለት ሶስተኛው በሚካሄደው የመሥራች አባላት ስብሰባ ላይ መገኘት አለባቸው፤

፬ በመሥራች ስብሰባው ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎች ቃለ-ጉባዔ በአግባቡ መያዝ አለበት፤

፭ በመሥራች ሰብሰባው ላይ የኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ተወካይ መገኘት አለበት፡፡

## ፲፪ በመሥራች ጉባኤ ላይ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች

በምሥረታ ጉባዔ ላይ ቀርበው በውሳኔ የሚጸድቁ ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

፩ የአዋጭነትጥናት፤
፪ የንግድ ሥራ ዕቅድ፤
፫ የመተዳደሪያ ደንብ፤
፬ ሥራውን የሚያከናውንበት ክልል ወይም ቦታ ወሰንና መግለጫ፤
፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስም ስያሜ እና አርማ፤
፮ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ምርጫ፤
፯ መመዝገቢያ የገንዘብ መጠን ማስወሰን፤
፰ የዕጣ ካፒታል ለሽያጭ የተወሰነ የዕጣ ብዛት፣ የአንድ ዕጣ ዋጋ፣ የተሸጠ ዕጣ መጠን፣ ቃል የተገባ ዕጣ ብዛት እና ዕጣው ተሸጦ የሚያልቅበት ጊዜ ማስወሰን፤
፱ የቁጠባ መጠን
፲ ከሌላ ምንጭ የተገኘ የካፒታል መጠን፡፡

3. At least two-thirds of the representatives of the cooperativesocieties union who have applied for membership to form the union of cooperatives and the federation of cooperativesocieties must attend the meeting of the founding members;
4. The minutes of the decisions passed at the founding meeting must be kept properly;
5. A representative of the commission or the office must be present at the founding meeting.

## 12. Matters to be Decided at the Founding Meeting

Matters to be presented and approved by resolution at the constituent assembly include the following:

1. Feasibility Study;
2. Business Plan;
3. Bylaws;
4. Limitation and Description of the Territory or Place in which the work is to be carried out;
5. Name and Logo of the Cooperative Society;
6. Election of Management Committee, Control Committee and other Sub-Committees;
7. Determination of Registration Amount;
8. Determining the share capital, the number of shares for sale, the price of one share, the amount of shares sold, the number of promised shares and the time when the share will be sold;
9. Savings Rate;
10. Amount of Capital obtained from other sources.

፲፫ **ስለኅብረት ሥራ ማህበራት የአመዘጋገብ ሥርዓት**

የአዋጁ አንቀጽ ፲ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩ ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በኅብረት ሥራ ማህበር ሕጎች፣ መርሆዎች እና ዕሴቶች መሰረት ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች አሟልቶ መቅረብ አለበት፤

፪ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በኅብረት ሥራ ማህበራት ህግ መሰረት ካልተመዘገበ በስተቀር የማህበርን ሰራ ማከናወን አይችልም፤

፫ ማንኛውም መሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪነት የምዝገባ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ፊርማ የተረጋገጠ መተዳደሪያ ደንብ፣

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ስምና አድራሻ፣

ሐ) በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣

መ) በጽሁፍ የተዘጋጀ የአደራጅ ባለሙያ ሙያዊ የምስክርነት ቃል እና አስተያየት፣

ሠ) ለምዝገባ በሚቀርብ የመተዳደሪያ ደንብ ሠነድ ላይ ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ የቴምብር ማስለጠፍ፤

ረ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ለምዝገባ ሠርተፍኬት ለባንክ ገቢ የሆነበትን ደረሰኝ አንድ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ፤

ሰ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

ሸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የአዋጭነት ጥናት፤

13. **Cooperative Societies Registration Procedure**

Subject to the provision of article 10 of the proclamation:

1. Any cooperative society applying for registration must comply with the requirements to be eligible for registration in accordance with the rules, principles and values of the cooperative society;
2. Any cooperative society cannot perform the work of a cooperative society unless it is registered in accordance with the cooperative societies act;
3. Subject to the provisions of sub article (1) and (2) of this article, any primary cooperative society must additionally submit its application for registration along with the following documents:
   a) Bylaws certified by the signatures of the members of the general assembly;
   b) Names and addresses of members of the cooperative society;
   c) Short, medium and long term plan approved by the general assembly;
   d) Written professional testimony and opinion of the organizing expert;
   e) Posting a stamp on a bylaw document submitted for registration to confirm its legality;
   f) Attaching one copy of the receipt to the bank for the registration certificate on behalf of the cooperative society;
   g) A document confirming the amount of initial capital and that it has been collected and deposited into a bank account;
   h) Feasibility study of the cooperative society.

፬ ማንኛውም ከመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ የሆነ የኅብረት ሥራ ማህበር ማህበር ለምዝገባ ሲቀርብ በተጨማሪነት የምዝገባ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ፊርማ የተረጋገጠ መተዳደሪያ ደንብ፣

ለ) የአባል ማህበሩ ስምና አድራሻ፣

ሐ) የመሥራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ቃለ-ጉባኤ፣

መ) የማህበሩ ሀብትና ዕዳ መግለጫ፣

ሠ) በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ዕቅድ፤

ረ) በጽሁፍ የተዘጋጀ የአደራጅ ባለሙያ ሙያዊ የምስክርነት ቃል እና አስተያየት፣

ሰ) ለምዝገባ በሚቀርብ የመተዳደሪያ ደንብ ሠነድ ላይ ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ ቴምብር ማስለጠፍ አለበት፤

ሸ) በማህበሩ ስም ለምዝገባ ሠርተፍኬት ለባንክ ገቢ የሆነበትን ደረሰኝ አንድ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

፭ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ የአገልግሎት በዚሁ ደንብ አንቀጽ ፳፩ ድንጋጌ መሠረት ክፍያ ይከፍላል፤

፮ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ለተገልጋዩ ግልጽ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፤

፯ ማህበራት ከመመዝገባቸው አስቀድሞ በአደራጅ ባለሙያው ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፤

፰ አደራጅ ባለሙያው የመደራጀት ጥያቄውን ተከትሎ ለማደራጀት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ስለመደረጉ እና የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመደራጀቱ ስለሚኖረው ጠቀሜታ በተመለከተ ሙያዊ የምስክርነት ቃሉን እና አስተያየቱን በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፤

4. Any cooperative society which is more than a primary cooperative society, when applying for registration, must also submit the registration application along with the following documents:
   a) Bylaws certified by the signatures of the members of the general assembly;
   b) Name and address of the member society;
   c) Minutes of founding cooperative societies;
   d) Statement of assets and liabilities of the cooperative society;
   e) Short, medium and long term plan approved by the general assembly;
   f) Written professional testimony and opinion of the organizing expert;
   g) A stamp must be affixed to the bylaw document submitted for registration to confirm its legality;
   h) It must submit a copy of the receipt to the bank for the registration certificate on behalf of the cooperative society;
5. Any cooperative society shall pay a fee for the registration service in accordance with the provisions of article 21 of this regulation;
6. The commission or the office shall make clear to the user the requirements for registration of cooperative societies;
7. Cooperative societies should be properly monitored and supported by the organizer before they are registered;
8. The organizing expert must submit his professional testimony and opinion in writing regarding the appropriate support and supervision for organizing following the society request and the importance of the cooperative society being organized;

፱ ለምዝገባ ጥያቄ የሚያቀርብ ማህበር በምዝገባ መገምገሚያ ቅጽ ላይ ሞልቶና ትክክለኛነቱን አረጋግጦ ማቅረብ አለበት

፲ ስለ መረጃው ትክክለኛነት የተሰጠበትን ቀን በማስፈር መዝጋቢው በፊርማ ማረጋገጥ አለበት፤

፲፩. ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የምስክር ወረቀቱን በማዘጋጀት ከመተዳደሪያ ደንቡ ጋር በመሸኛ ደብዳቤ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መስጠት አለበት፡፡

፲፬ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት መዝጋቢ አካላት</u>

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመዘግብ ማንኛውም መዝጋቢ ባለሙያ ለምዝገባ የቀረቡለትን ሠነዶችን መሠረት በማድረግ የሚመዝንበትን ቼክሊስት ማዘጋጀት አለበት፤

፪ የአዋጭነት ጥናት ተዘጋጅቶ አዋጭ መሆኑ እና በሚደራጅበት አካባቢ መሥራት የሚችል መሆኑ የተረጋገጠለት የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ ይመዘገባል፤

፫ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው ሲረጋገጥ በወረዳ፣ በከተማ ወይም በማዕከል ደረጃ ባለው አደራጅ መስሪያ ቤት ቀርበው ይመዘገባሉ፤

፬ የኅብረት ሥራ ሥራ ዩኒየኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው ሲረጋገጥ በከተማ ደረጃ ቀርበው ይመዘገባሉ፤

፭ ከሁለት ወረዳዎች ነዋሪዎች በተውጣጡ አባላት የሚቋቋም መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ቀርበው ይመዘገባሉ፤

9. Cooperative Society that submits a request for registration must fill in the registration evaluation form and confirm its accuracy;
10. The registrar must confirm the accuracy of the information by signing the date on which it was provided;
11. The commission or the office shall prepare the certificate and issue it to the cooperative society in a cover letter along with the bylaws.

14. **<u>Registration Bodies of Cooperative Societies</u>**

1. Any registrar who registers cooperative societies must prepare a checklist to weigh the documents submitted for registration;
2. A feasibility study is prepared and it is confirmed that the cooperative society is viable and able to work in the area where it is being organized, and it is submitted to the appropriate authority and registered;
3. When it is confirmed that primary cooperative societies meet the necessary criteria, they will be registered at the organizing office at the district, city or center level;
4. Cooperative society unions and federations of cooperative societies are registered at the city level when it is confirmed that they meet the necessary criteria;
5. A primary cooperative society established by members from residents of two Districts will be registered at the Sub- City Office;

፮ በሁለት ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች በተውጣጡ አባላት የሚቋቋም ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው ሲረጋገጥ በማዕከል ደረጃ ቀርበው ይመዘገባሉ፤

፯ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ሕጋዊ ህልውናው ይጀምራል፤

፰ የምዝገባ ሠርተፊኬት ከመሰጠቱ በፊት ማንኛውም መዝጋቢ አካል ለመደራጀት የቀረበውን ማህበር በአካል በመገኘት በተዘጋጀው ቼክሊስት መሰረት መገምገምና መመዘን አለበት፤

፱ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መሰረታዊ መረጃ ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ ወይም ፎርማት ተሰብስቦ በመዝገብ ላይ ቢያንስ በየሦስት አመቱ መታደስ አለበት፤

፲ የኅብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው ሲመዘገቡ ቋሚ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፤

፲፩ መዝጋቢው አካል አንድን የኅብረት ሥራ ማህበር የማይመዘግበው መሆኑ ሲታወቅ የማይመዘግብበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፲፭ **<u>የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመመዝገብ መሟላቱን ስለማረጋጥ</u>**

ኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ኅብረት ሥራ አባላት ሆነው የሚመዘገቡ ግለሰቦች አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር ሁኔታዎች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ መቀመጡን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

6. Any cooperative society established by members of two sub districts will be registered at the central level when it is confirmed that they meet the necessary criteria;
7. Any cooperative society begins its legal existence from the date of its registration;
8. Before the registration certificate is issued, any registrar must evaluate and assess the society proposed to be organized in person according to the prepared checklist;
9. The basic information of any cooperative society must be collected in the form or format prepared by the commission and updated on the register at least every three years;
10. Cooperative societies will be issued with a permanent legal personality certificate upon registration that meets the required criteria;
11. When it is known that the registering body will not register a cooperative society, it must inform the applicant in writing of the reasons for not registering it.

15. **<u>Ensuring Compliance to Register Cooperative Societies</u>**

The commission or the office should ensure that the details of the eligibility of individuals who register as members of a cooperative society are clearly stated in the cooperative society's bylaws.

## ፲፮ <u>የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታ</u>

፩ ከአንድ ወረዳ በተዉጣጡ አባላት የሚደራጅ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በወረዳ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጽህፈት ቤት ይመዘገባሉ፤

፪ በአንድ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ካሉ ሁለት እና ከዚያ በላይ ወረዳዎች የተዉጣጡ አባላት የሚደራጅ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በክፍለ ከተማ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጽህፈት ቤት ይመዘገባሉ፤

፫ ከሁለት ክፍለ ከተማ እና ከዚያ በላይ የተዉጣጡ አባላት መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ከሆነ በኮሚሽኑ ይመዘገባሉ፤

፬ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን እና ፌዴሬሽን በኮሚሽኑ ይመዘገባሉ፤

፭ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚሽኑ ዩኒዬኑን በክፍለ ከተማ ደረጃ እንዲመዘገብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፲፯ <u>የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይዘት</u>

የምዝገባ የምስክር ወረቀት በኮሚሽኑ የሚታተም ሆኖ የሚከተሉቱን ያካተተ ይሆናል፡-

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም፣ የምዝገባ ቁጥር፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የተመዘገበበት የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር፣ ቀን እና ዓመተ ምህረት፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመዘገበው የኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ባለሥልጣን ስምና ፊርማ፤

፬ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት፤

፭ የኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ማህተም፤

፮ እንደአስፈላጊነቱም የታደሰበት ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምህረት እና ያደሰው ባለሥልጣን ፊርማ፡፡

## 16. <u>Issuance of Registration Certificate</u>

1. A primary cooperative society organized by members from one district shall be registered at the District Cooperative Societies Office;
2. A primary cooperative society organized by members from two or more Districts in one Sub-City shall be registered at the sub-city cooperatives office;
3. Members from two sub cities and above will be registered with the commission if it is a primary cooperative society;
4. Unions and federations of cooperative societies shall be registered with the commission;
5. Notwithstanding the provisions of sub article (4) of this article, the commission may, where necessary, register the Union at the Sub City level.

## 17. <u>Content of Registration Certificate</u>

The certificate of registration shall be published by the commission and shall include the following:

1. Name of the cooperative society, registration number;
2. Cooperative Societies Proclamation No., date and year in which the cooperative society was registered;
3. The name and signature of the commission or office official who registered the cooperative society;
4. Date, month and year of the certificate of registration;
5. The seal of the commission or its office;
6. Date, month, year of renewal and signature of the renewing authority, as applicable.

፲፰ **ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ**

፩ የምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄ የሚቀርበው የምስክር ወረቀቱ ሲጠፋ፣ ሲበላሽ እና የስም ለውጥ ሲደረግ ይሆናል፤

፪ የምትክ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ሲቀርብ ከዚህ በታች ያሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የጠፋ ስለመሆኑ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ፤

ለ) የምስክር ወረቀቱ የተበላሸ ከሆነ የምስክር ወረቀቱን የሰጠው አካል ጋር ቀርቦ ሲረጋገጥ፤

ሐ) የምትክ ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ያቀረበው የኅብረት ሥራ ማህበር የስም ለውጥ ያደረገ ከሆነ የስም ለውጡ የተፈቀደበት የፍርድ ቤት ማስረጃ ሲያቀርብ፤

መ) የስም ለውጡ ተቀባይነት የሚያገኘው ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ማህተም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ እና ሌሎች የቀድሞ የማህበሩ ስም ያለባቸው ሰነዶች በአዲስ ስም መለወጣቸውን እና መመለሳቸውን ሲያረጋግጥ፤

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው አስፈላጊውን ክፍያ ፈጽሞ ለኮሚሽኑ ደረሰኝ ሲያቀርብ እና ቀደም ሲል በመዝገብ ላይ ባለው የቀድሞ ቁጥር ሲመዘግብ ይሆናል፡፡

፲፱ **ስለጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት**

፩ ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፡-

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ሲያረጋግጥ የሚሰጥ ይሆናል፤

18. **Issuance of Replacement Registration Certificate**
    1. A request for a replacement certificate of registration shall be made when the certificate is lost, damaged or changed in name;
    2. When applying for a replacement registration certificate, the following conditions must be met:
        a) When it is verified by the relevant body that the certificate is lost;
        b) If the certificate is damaged, when it is verified with the party that issued the certificate;
        c) If the cooperative society that has submitted a request for a substitute legal entity certification certificate has changed its name, when it submits court evidence that the name change was approved;
        d) The commission or the office that approves the name change, the seal of the cooperative society bylaws, and other documents bearing the cooperative society's previous name have been changed and returned under a new name;
        e) The cooperative society can obtain a replacement certificate of registration only when it submits a receipt to the commission for the required payment and registers it under the previous registration number.

19. **Temporary Registration Certificate**

1. Temporary registration certificate:
    a) It will be issued when the commission or the office determines that the requirements listed in sub article (2) of article 10 of the proclamation have been met;

ለ) የሚሰጠው ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ይሆናል፤

ሐ) ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ያለው መብት እና ግዴታ ይኖረዋል፤

፪ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቶችን ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ ሲገኝ ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን እንዲመልስ በማድረግ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ አዲስ ቋሚ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤

፫ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መስፈርቶቹን የማያሟላ ከሆነ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የማፍረስ ተግባር ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

፳ <u>**የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሳደስ**</u>

፩ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበትና ህጋዊ ሰውነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ በየሶስት ዓመቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፤

፪ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ቀርቦ መታደስ አለበት፤

፫ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂ፤

ለ) የሦስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን አጠቃላይ አቋም የሚገልፅ ያለፉት ሦስት ዓመታት አጭር የጽሁፍ መግለጫ፤

b) It will be given only for a period of more than one year;

c) A cooperative society that has obtained a temporary registration certificate shall have the same rights and obligations as any cooperative society during the period of registration;

2. When the cooperative society has fully met the requirements within the given time limit, it will be given back the temporary registration certificate and a new permanent registration certificate will be issued to it with the appropriate payment;
3. If the cooperative society does not meet the requirements within the given time limit, the commission or the office will take action to dissolve the cooperative society.

20. <u>**Renewal of Registration Certificate**</u>

1. Every cooperative society must renew its certificate of registration every three years from the date of its registration and legal personality;
2. The certificate of registration must be renewed not later than one month before the expiration date of the certificate of registration;
3. Any cooperative society for renewal of registration certificate must fulfill the following:

a) Three copies of the bylaws of cooperative society or amended bylaws of cooperative society;

b) A three-year strategic plan;

c) A brief written statement of the last three years describing the general position of the cooperative society;

መ) በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የዘመኑ የኦዲት ሪፖርት፤

ሠ) የብቃት ምዘና ዕውቅና ማረጋገጫ ሠርተፊኬት፤

ረ) ለዕድሳት የሚከፈለውን ገንዘብ ገቢ ያደረገበት ደረሰኝ፤

ሰ) የአባላትን ቁጥር የሚገልጽ መረጃ፤

ሸ) በተከታታይ ላለፉት ሦስት አመታት ኪሳራ ያላሳየ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ፣

ቀ) ባላፉት ሦስት አመታት በአማካይ የአባላት የግብይት ተሳትፎ የተሻሻለ መሆኑን የሚሳይ መረጃ፤

፬ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወሰዳል፡-

ሀ) ከመንግስት የሚያገኛቸውን ማናቸውም ድጋፎች ይቋረጣሉ፤

ለ) በምዘገባ ምስክር ወረቀቱ የሚያደርጋቸው ማናቸውም ውሎች እና ስምምነቶች ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ይደረጋል፤

ሐ) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ህጋዊነት የሌለው መሆኑን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያሳውቅ ይችላል፤

፭ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ሕግን ተከትሎ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ በመሰረዝ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

## ፳፩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚደረግ ክፍያ

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ በሚቀርብበት ጊዜ የሚከፈለው የምዝገባ ክፍያ የሚከተሉትን ያካትታል፡-



d) An up-to-date audit report approved by the general assembly;

e) Competency assessment certification certificate;

f) Receipt of payment for renewal;

g) Information on the number of members;

h) Information showing that it has not shown losses for the last three consecutive years;

i) Information showing that members' marketing participation has improved on average over the past three years;

4. The commission or the office shall take the following measures against any cooperative society that does not renew its registration certificate in accordance with sub article (3) of this article:

a) Any support it receives from the government will be terminated;

b) Any terms and conditions entered into by the certificate of registration shall be rendered unenforceable;

c) He may notify the invalidity of the registration certificate using various means of communication;

5. Subject to the provisions of sub article (5) of this article, the commission or the office may cancel the registration certificate and cause the cooperative society to lose its legal personality.

## 21. Payment for Registration Certificate

The registration fee payable at the time of application of any cooperative society for registration shall include:

፩ በአዲስ ለሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ቋሚ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር ፭፻ (አምስት መቶ)፤

፪ ምትክ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር ፭፻ (አምስት መቶ)፤

፫ ጊዜያዊ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር ፭፻ (አምስት መቶ)፤

፬ ለምዝገባ ሠርተፍኬት ዕድሳት ብር ፭፻ (አምስት መቶ)፤

፭ የብቃት ምዘና ሰርተፍኬት ብር ፭፻ (አምስት መቶ)፡፡

**፳፪ ምዝገባ ስለሚከለከልበት ሁኔታ**

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች ምዝገባ ይከለከላል፡-

፩ በአካባቢው አስቀድሞ በተመሳሳይ ስምና አርማ የተመዘገበ ኅብረት ሥራ ማህበር ያለ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

፪ የራሱ የሆነ የአዋጪነት ጥናት የሌለው ከሆነ፤

፫ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ መሰረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ያላሟላ ከሆነ፤

፬ ዓላማው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅን ወይም ሌሎች ህጎችን የሚጻረር ከሆነ፡፡

**፳፫ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማገድ**

፩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ሊታገድ ይችላል፡-

ሀ) አዋጁን እንዲሁም ስለ ኅብረት ሥራ ማህበር የወጡ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ህጎች ሲጻረር፤ እንዲሁም ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተቋቋመለትን ዓላማና መርህ በሚጻረር መልኩ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፤

1. 500.00 (five hundred) Birr to obtain a permanent registration certificate for a newly organized cooperative society;
2. 500.00 (five hundred) Birr to obtain a replacement registration certificate;
3. 500.00 (five hundred) Birr to obtain a temporary registration certificate;
4. 500.00 (five hundred) Birr for registration certificate renewal;
5. Competency assessment certificate 500.00 (five hundred) Birr.

22. **The Situation where Registration is Denied**

Any cooperative society shall be denied registration for the following reasons:

1. If it is confirmed that there is already a cooperative society registered with the same name and logo in the area;
2. If it does not have its own feasibility study;
3. If you do not meet the requirements for registration in accordance with article 13 of this regulation;
4. If the objective is against the cooperative societies proclamation or other laws.

23. **Suspension of Registration Certificate**

1. Any cooperative society issued with a certificate of registration may be suspended under the following circumstances:

   a) Violates the proclamation and other relevant laws on cooperative societies, also, if the cooperative society is found to be acting contrary to the objective and principle for which it was established;

ለ) ቀደም ሲል ያቀረባቸው የመመዘኛ መስፈርቶች የተጭበረበሩ ወይም ያልተሟሉ መሆኑን በክትትል እና ግምገማ ወቅት ከተረጋገጠ፤

ሐ) የሚጠበቅበትን ትክክለኛ የሆነ መረጃ ለመዝጋቢ አካላት ያላቀረበ ከሆነ፣

መ) በአባላት መብትና ጥቅም ላይ እንዲሁም በከተማው ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ተረጋግጦ ሲቀርብ፤

ሠ) የእድሳት ጊዜውን ያሳለፈ ወይም የሚጠበቅበትን ግዴታ ያልተወጣ ሲሆን፤

፪ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ዕገዳ ለተደረገበት የኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በምን ምክንያት እንደታገደ እና የታዩ ጉድለቶችን በመግለጽ በ ፲፭ ቀናት ውስጥ በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፫ ኅብረት ሥራ ማህበሩ የታዩበት ጉድለቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ አገልግሎት ሊሰጥ ስለማይችል በዚህ ጊዜ በምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በመጠቀም የሚደረጉ ማናቸውም ውሎች እና ድርጊቶች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

፬ ዕገዳ የተደረገበት የኅብረት ሥራ ማህበር የታገደበትን ምክንያት የሚገልፅ ደብዳቤ ከደረሰበት ዕለት አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታዩ ጉድለቶችን በማስተካከል ዕገዳው እንዲነሳለት ለመጠየቅ ይችላል፤

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት እግዱ እንዲነሳለት ካልጠየቀ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ማፍረስና የመሰረዝ ሂደቱን ይጀምራል፡፡

## ፳፬ <u>የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከመዝገብ ስለ መሰረዝ</u>

፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ መኖሩ ሲያረጋግጥ ከመዝገብ ሊሰረዝ ይችላል፡-

b) If it is confirmed during the monitoring and evaluation that the qualification criteria he submitted earlier are falsified or not met;

c) If he did not submit the required correct information to the registration bodies;

d) When it is proven that it causes damage to the rights and interests of the members as well as the economy of the city;

e) When he has passed the renewal period or has not fulfilled his obligations.

2. The commission or the office must inform the suspended cooperative society in writing within 15 days stating the reasons for the suspension and the defects found;
3. Since the registration certificate cannot be used until the deficiencies are corrected, the terms and conditions of the registration certificate will not be valid;
4. A suspended cooperative society may request that the suspension be lifted within one month from the date of receipt of the letter stating the reason for the suspension;
5. If the suspension is not requested to be lifted according to sub article (4) of this article, the commission or the office will start the process of dismantling and canceling the cooperative society.

## 24. <u>Cancellation of Registration Certificate</u>

1. Subject to the provisions of article 23 of this regulation, the commission may cancel the registration certificate of any cooperative society upon finding that one of the following conditions exists:

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማታለል ወይም የሃሰት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ፣

ለ) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ከተሰጠው ዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር ሲገለገልበት ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ፣

ሐ) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ካልታደሰ፣

መ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበር አግባብነት ያላቸውን ህጎች ወይም ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተቋቋመለትን ዓላማና መርህ በሚጻረር መልኩ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ህልውናውን ያጣ መሆኑን በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፤

፪ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ከመዝገብ ሲሰረዝ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን፣ የራስጌ እና የግርጌ ማህተሞችን ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ መመለስ ይኖርበታል፤

፫ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲያውቀው አስቀድሞ በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፤

፬ የምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲገለገልባቸና በስሙ የተከፈተ ማንኛውም የባንክ ሂሳብ ቁጥር ማዘጋት አለበት፤ ስለመዘጋቱም ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች፣ ዓላማና ተግባር

### ፳፭ ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምርት ወይም የአገልግሎት መስጠት ወይም የምርትና የአገልግሎት መስጠት ተግባራትን አጣምሮ የሚያከናውን ሆኖ ሊደራጅ ይችላል፡፡

a) When it is known that the cooperative society has obtained the registration certificate by deception or providing false evidence;

b) If it is found that the registration certificate is being used for another objective other than the given objective or has been transferred to another third party;

c) If the certificate of registration is not renewed;

d) If he is found to be acting contrary to the relevant laws about the cooperative society or the objective and principles for which the cooperative society was established;

e) When it is confirmed by the court that the cooperative society has lost its existence;

2. When any cooperative society is deregistered by the commission or the office, it must return the registration certificate, header and footer stamps to the commission or the office;
3. The commission or the office shall notify the cooperative society in advance in writing that the certificate of registration is to be cancelled;
4. Any cooperative society returning the certificate shall close any bank account number opened in its name; it should also provide proof of closure.

## PART THREE

## TYPES OF COOPERATIVE SOCIETIES, OBJECTIVE AND FUNCTION

### 25. Establishment of Cooperative Societies

Any cooperative society may be established to provide products or services or a combination of products and services.

**፳፮ <u>የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች</u>**

የኅብረት ሥራ ማህበራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ይሆናሉ፡-

፩ የሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር፣

፪ የቁጠባና ብድር ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር፣

፫ የመኖርያ ቤቶች ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር፣

፬ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ የሥራ ባህሪያቸው እና ኢኮኖሚያዊ አመዋጭነት እንዲሁም ለከተማው አስተዳደር አስፈላጊነቱ እየተጠና ሌሎች መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲመሰረቱ ሊፈቅድ ይችላል፣

፭ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች፣

፮ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን፡፡

**፳፯ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓላማ</u>**

የአዋጁ አንቀጽ ፬ ድንጋጌ እንደጠበቀ ሆኖ፡-

የመሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓላማ ለኅብረት ሰራ ማህበሩ አባላትና ለአካባቢው

፩ ኅብረተሰብ ምርቶች እና አገልግሎቶችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ በማድርግ ያሉባቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት፣

፪ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የአባላት ተሳትፎ የሚጎለብትበትን የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠትና አዳዲስ ቴክኖሎጅ እንዲጠቀሙ በማድረግ ተወዳዳሪ ምርት በማምረት አግልግሎት በመስጠት ለአባላትና ለአካባቢው ህብረተሰብ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡

26. **<u>Types of Primary Cooperative Societies</u>**

The cooperative societies will be listed below:

1. Consumers Limited Primary Cooperative Society;
2. Savings and Loan Limited Liability Primary Cooperative Society;
3. Primary Cooperative Society of Housing Limited;
4. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) to (3) of this article, the commission may allow the establishment of other primary cooperative societies while studying their work characteristics and economic viability as well as their importance to the city administration;
5. Cooperative Society Unions;
6. Federation of Cooperative Societies.

27. **<u>Objective of Cooperative Societies</u>**

Subject to the provisions of article 4 of the proclamation:

1. The objective of primary cooperative societies is to provide quality and affordable products and services to the members of the cooperative society and to solve their economic and social problems;
2. It is to provide capacity building training to enhance the participation of the members of the cooperative society and make them use new technologies to produce competitive products and provide services for the overall benefit of the members and the local society.

**፳፰ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምርት ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው ማቅረብ፤

፪ በዘርፉ እያጋጠመ ያለውን ችግር ለመፍታት ቀጣይነት ያለው የምርት እና አገልግሎት የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምርት ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ከባለድረሻ ካላት ጋር የተቀናጀ ተግባራትን ማከናወን፤

፬ የሕብረት ሥራ ማህራት አሰራራቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመታገዝ የአባላት ተጠቃሚነት እንዲያድግ መሥራት፤

፭ ለአባላት ዘመናዊ የምርት አመራረት ዘዴዎችን እና የአገልግሎት አሰጣጥ አስመልክቶ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት የሥራ ባህላቸውን ማጎልበት፤

፮ አዳዲስ አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ በዘርፉ ተወዳዳሪ መሆን፤

፯ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ የምርት ውጤቶችን ማምረት እና አገልግሎት ማቅረብ የሚችል አቅም ያለው አባል መፍጠር፤

፰ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው ጋር የሚያደርጉትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአባላት የተሳትፎ ካርድ እና መዝገብ ላይ መመዝገብ፤

፱ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር፣ ለአባላት እና ለቅጥር ሠራተኞች ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ስልጠና መስጠት፤

፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ በትክክትል መፈፀም እንዲችል የተለያዩ የአሰራር ሰነድ ማዘጋጀት፤

፲፩ በየዓመቱ ኅብረት ሥራ ማህበሩን ኦዲት በማስደረግ በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ለአባላት የትርፍ ክፍፍል ማድረግ፤

28. **<u>Duties and Responsibilities of Cooperative Societies</u>**

Cooperative societies shall have the following duties and responsibilities:

1. To provide the cooperative society's products and services to the consumer with quality and reasonable prices;
2. Doing continuous product and service promotion to solve the problem facing the sector;
3. Carry out coordinated activities with stakeholders to promote the cooperative society's products and services;
4. Working with cooperative societies to increase the benefits of their members with the help of modern technology;
5. Strengthening the working culture of members by providing capacity building training on modern production methods and service delivery;
6. To be competitive in the sector by implementing new practices;
7. Creating a capable member who can produce products and provide services using various technologies;
8. To record any activities of the members with their cooperative society in the members participation card and register;
9. Providing continuous education and training to the cooperative society's management, members and employees;
10. To prepare various operating documents so that the cooperative society can fulfill the objective for which it was established;
11. Auditing the cooperative society every year and distributing dividends to members in accordance with their bylaws;

፲፪ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፡-
ሀ) በመተዳደሪያ ደንቡ በተወሰነው መሰረት የተለያዩ የቁጠባ ዓይነቶችን አሰራር በመዘርጋት ከአባላት ቁጠባ መሰብሰብ፤
ለ) በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለማህበር አባላት የተለያዩ ዓይነት የብድር አሰራር በመዘርጋት የብድር አገልግሎት መስጠትና የተሰራጨ ብድርን መሰብሰብ፤
ሐ) አባላት የሚወስዱትን ብድር አዋጭነት ባለው ሥራ እንዲያውሉ የምክር አገልግሎት መስጠት፤
መ) ለአባላትና ለአካባቢው ነዋሪዎችና ተቋማት የአደራን ገንዘብ ተረክቦ የማስቀመጥና የሐዋላ አገልግሎት መስጠት፤
ሠ) በማህበሩ ውስጥ የተለያዩ የብድር አይነቶችን ተግባራዊ በማድረግ ለአባላት የብድር አገልግሎት በስፋት ማቅረብ፤
ረ) የአባላትን የብድር አጠቃቀም ልምድና ባህል ማዳበር፤
ሰ) የብድር አገልግሎት በመስጠት ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ በማሳደግ የአባላትን ገቢ አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ፤

፲፫ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዘመናዊ የሆነ የሂሳብ አሰራር እንዲኖር ማድረግ፤

፲፬ የኅብረት ሥራ ማህበር የምርትና የአግልግሎት ጥራት እና አሰራርን ለማሻሻል ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፤

፲፭ በማምረትና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚደራጁ ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባር እንደአግባብነቱ የኅብረት ሥራ ማህበራቱ በተሰማሩበት ሥራ ዘርፍ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፤

12. Savings and Loan Cooperative Societies:
   a) Collecting savings from members by developing different types of savings as determined by the bylaws;
   b) Providing loan services and collecting disbursed loans by establishing different types of loan systems for members of the cooperative societies in accordance with the bylaws;
   c) Providing advice to members so that they can use their loans in viable business;
   d) Providing deposit and money order services to members and local residents and institutions;
   e) Applying different types of loans in the cooperative society and offering loan services to members on a wide scale;
   f) To develop the loan usage experience and culture of members;
   g) Making the income of members reliable by providing loan services and raising them to a better standard of living;
13. To ensure that the cooperative society has a modern accounting system;
14. Carrying out other activities relevant to improving the quality and operation of the cooperative society's products and services;
15. The activities of multipurpose cooperative societies that are established in production and providing services will be determined according to the field of work in which the cooperative societies are engaged;

፲፮ የኅብረት ሥራ ፌደሬሽኑ ከመሠረታዊ ማህበራት እና ከዩንየን አቅም በላይ የሆኑ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ትስስር መፍጠር፤

፲፯ የኅብረት ሥራ ፌደሬሽኑ በአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ጉዳይ ላይ አባላትን በመወከል መንግስትና ባለድርሻ አካላትን ማግባባት፤

፲፰ በዩኔንም ሆነ በፌዴሬሽን የሚደራጁ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባል ኅብረት ሥራ ማህበራትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ከአባላት አቅም በላይ የሆኑትን ተግባራት ተግባራቸው አድርገው ይሰራሉ፤

፲፱ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሕብረት ሥራ ማህበራት ተግባር በየኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ሊወሰን ይችላል፡፡

**፳፱ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ውህደት</u>**

የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚከተሉት ምክንያቶች በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ውህደትን ሊፈፅሙ ይችላሉ፡-

፩ የአባላት ቁጥር በህግ ከተወሰነው የአባላት መነሻ ቁጥር በታች ሲሆን፤

፪ የካፒታል መጠን ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ለአባላት አገልግሎት መስጠት ሳይቻል ሲቀር፤

፫ አቅም በመፍጠር የጋራ ፕሮጀክቶችን በአንድ ላይ ሆኖ ተግባራዊ ለማድረግ፤

፬ አዋጭነታቸውን በማሳደግ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማጠናከር፤ ደካማ አፈፃፀም ያላቸውን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በማዋህድ ጠንካራ እና ውጤታማ የኅብረት ሥራ ማህበር ለመፍጠር፤

፭ ከመንግስት እና ከሌሎች ባላድረሻ አካላት የተሻለ አገልግሎት እና ሙያዊ ድጋፍ ለማግኘት፤



16. Creating national and international financial links beyond the capacity of the cooperative societies federations and unions;
17. The federation of cooperative societies represents members on the issue of member cooperative societies and lobbies the government and stakeholders;
18. Cooperative societies that are established by the union or the federation, based on the needs of the member cooperative societies, perform tasks that are beyond the capacity of the members;
19. Subject to the provisions of this article, the activities of cooperative societies may be determined by the bylaws of each cooperative society.

29. **<u>Amalgamation of Cooperative Societies</u>**

Subject to the provisions of Article 13 of the proclamation, cooperative societies may amalgamate according to the decision of the general assembly for the following reasons:

1. When the number of members is less than the starting number of members determined by law;
2. When it is not possible to provide services to members due to low capital;
3. Creating capacity to implement joint projects together;
4. To strengthen their economic capacity by increasing their viability, amalgamate underperforming cooperative societies to create a strong and efficient cooperative societies;
5. To get better service and professional support from government and other stakeholders;

፮ በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ የሚኖረውን የሥራ ድግግሞሽ እና እርስ በእርስ በመወዳደር የጥቅም ግጭት ለማስቀረት፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበራት ውህደት መፍጠር የሚችሉት ተመሳሳይ ዓላማ እና ተግባር ሲኖራቸው ይሆናል፡፡

፴ **የኅብረት ሥራ ማህበር መከፈል**

፩ የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚከተሉት ምክንቶች ሊከፈሉ ይችላሉ፡-

ሀ) በሥራ አካባቢ መስፋት የተነሳ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ተግባራት መሳተፍ አለመቻላቸው እና በመከፈሉ የተሻለ አማራጭ መፈጠሩ በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ሲታመንበት፤

ለ) የአባላት ቁጥር ብዙ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በቂ አገልግሎት መስጠት ሳይችል ቀርቶ የአባላት ተሳትፎ ደካማ ሲሆን እና በውክልና መስተናገድ ካልተቻለ፤

ሐ) አባላቱ ልዩ ልዩ ተግባራት ያሏቸው የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማቋቋም ፈልገው መከፈሉ የተሻለ አማራጭ ከሆነ፤

መ) በጂኦግራፊያዊ ወይም በአስተዳደር አከላለል ምክንያት መከፈሉ አሳማኝ ሲሆን፤

፪ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ካላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ለመዋሃድ መጀመሪያ መከፈሉ አግባብነት ያለው ከሆነ፡፡

6. To avoid duplication of work in the same work area and competing interests;
7. Cooperative societies can amalgamate when they have the same objective and function.

30. **Division of Cooperative Societies**

1. Subject to Article 13 of the proclamation, cooperative societies may be divided for the following reasons:
   a) When it is believed by the commission or the office that members cannot participate in the activities of the cooperative society due to the expansion of the working environment and that a better alternative has been created due to the payment;
   b) When the number of members is large and the cooperative society is unable to provide adequate services, and the participation of members is weak and it cannot be handled by delegation;
   c) If the members want to establish cooperative societies with different activities, if it is a better option to be paid;
   d) When it is reasonable to pay due to geographical or administrative demarcation.
2. If it is appropriate to be paid first to merge with other cooperative societies with similar activities;

፫ በማንኛውም የሸማች ህብረት ሥራ ማህበር ስር ሲተዳደሩ የነበሩ የመዝናኛ ክበባትና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት በከተማ አስተዳደሩ የክፍለ ከተማና ወረዳ የአስተዳደር ወሰን ማካለል ምክንያት ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሲከፈሉ ወደሌላ ወረዳ የተካለሉት የመዝናኛ ክበብና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት በተካለሉበት ወረዳ በሚገኝ የሸማች ህብረት ሥራ ማህበር ወይም አዲስ በሚቋቋም የሸማች ህብረት ሥራ ማህበር የሚተዳደሩ ይሆናል::

፴፩ **የውህደት ወይም መከፈል ውሳኔ አፈጻጸም**

፩ የኅብረትሥራ ማህበራት ውህደት ወይም መከፈል ውሳኔ ሲፈጸም ከአባላት ወይም ከዕዳ ጠያቂዎች መካከል ያልተስማማ ወገን ካለ ልዩ ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት መብታቸው የሚጠበቅበት ውሳኔ እና ድርሻቸው መከፈል ወይም መቀመጥ ወይም የክፍያ ዋስትና መሰጠት አለበት፤

፪ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ውሳኔውን የሚቀበለው እና አዲስ ኅብረት ሥራ ማህበሩን የሚመዘግበው የአባላት ወይም የዕዳ ጠያቂዎች መብት መጠበቁን እና ሌሎች ህጋዊ ክፍያዎች መፈጸማቸውን ካረጋገጠ በኋላ ይሆናል፤

፫ ውህደቱም ሆነ መከፋፈሉ በኅብረት ሥራ አዋጁ መሠረት መከናወኑ ከተረጋገጠ በኋላ አዲሱ የተዋሃደው ወይም በመከፈል በአዲስ የተደራጁት ኅብረት ሥራ ማህበራት ይመዘገባሉ፤

፬ ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲዋሀዱ ወይም ሲከፈሉ የቀድሞ ምዝገባቸው ይሠረዛል፤

፭ አዲስ የተቋቋሙት ኅብረት ሥራ ማህበራት በአዲስ ስም እና ቁጥር እንደገና ይመዘገባሉ፤

3. When entertainment clubs and other income-generating institutions that were managed under any consumer cooperative society association are divided into two or more due to the division of the administrative boundaries of the Sub-City and District by the City Administration, the entertainment club and other income-generating institutions that are included in another district are included in a consumer cooperative society association in the district where they were included or a newly established consumer cooperative society.

31. **Implementation of the Decision of Amalgamation or Division**
    1. When the decision to amalgamation or division the cooperative society is made, if there is a disagreeable party among the members or creditors, before the special decision is made, their rights must be protected and their shares must be paid or reserved or a guarantee of payment must be given;
    2. The commission or the office will accept the decision and register the new cooperative society after confirming that the rights of members or creditors are protected and other legal payments are made;
    3. After it is confirmed that the amalgamate or division is carried out in accordance with the cooperative society proclamation, the newly amalgamated or divided cooperative societies will be registered;
    4. When cooperative societies are amalgamated or divided, their previous registration is cancelled;
    5. The newly established cooperative societies will be re-registered with a new name and number;

፮ በመዋሃድ ወይም በመከፈል ህልው ያቱት ኅብረት ሥራ ማህበራት ሲጠቀሙባቸው የነበሩት ሰነዶች አግባበብ ያለው ባለስልጣን በሚያዘው ቦታ ይቀመጣሉ፡፡

፯ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከመከፈሉ ወይም ከመዋሀዱ በፊት ለአበዳሪዎች የሚከፈል ዕዳ ካለበት በመከፈሉም ሆነ በመዋሃዱ የተፈጠሩት ኅብረት ሥራ ማህበራት በሰጡት የክፍያ ዋስትና መሠረት የሚደርስባቸውን የገንዘብ መጠን መደልደል አለበት፤

፰ በዋስትና የሚቀመጠው ገንዘብ ወይም ንብረት በቀጥታ በውህደት ወይም በመከፈል ወደ ተፈጠሩት ኅብረት ሥራ ማህበራት ይተላለፋል፤

፱ ዋስትና የተቀመጠላቸውም አባላት እና ዕዳ ጠያቂዎች ድርሻቸውን እና ሂሳባቸውን በውህደት ወይም በመከፈል የተፈጠረውን ኅብረት ሥራ ማህበር የመጠየቅ መብት አላቸው፤

፲ በውህደት ወይም በመከፈል ህልውናቸውን ወደ አጡት ኅብረት ሥራ ማህበራት ይገባ የነበረ ወይም ይገኝ የነበረ ጥቅም ካለ መብቱ በቀጥታ አዲስ ወደ ተቋቋሙት ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚተላለፍ ይሆናል፤

፲፩ በመከፈል ወይም በመዋሃድ የተፈጠሩት ኅብረት ሥራ ማህበራት የቀድሞውን ኅብረት ሥራ ማህበር መብት እና ግዴታ እንዲሁም ተግባር እና ኃላፊነት እንደ የድርሻቸው ይቀበላሉ፤

፲፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲከፈሉም ሆነ ሲዋሃዱ ቀድሞ የነበሩት ቅጥር ሠራተኞች ጉዳይ በሀገሪቱ አሰሪና ሠራተኛ ህግ እና በውላቸው መሠረት የሚታይ ይሆናል፤

6. The records and documents used by cooperative societies that have ceased to exist due to amalgamation or division shall be kept in a place controlled by the appropriate authority;
7. If any cooperative society has debts to be paid to the creditors before the division or amalgamation, the cooperative societies created due to the division or amalgamation must pay the amount due to them according to the payment guarantee given by them;
8. The fund or asset to be secured shall be transferred directly to the cooperative societies formed by amalgamation or disbursement;
9. Guaranteed members and creditors have the right to claim their shares and accounts from the cooperative society formed by amalgamation or division;
10. If there is any benefit that was or was available to the cooperative societies that lost their existence due to amalgamation or division, the right will be directly transferred to the newly established cooperative societies;
11. The cooperative societies formed by division or amalgamation shall accept the rights and obligations, duties and responsibilities of the former cooperative society as their share;
12. When cooperative societies are divided or amalgamated, the issue of former employees will be considered according to the country's employer-employee law and their contract;

፲፫ የኅብረትሥራ ማህበራት ውህደት ወይም መከፈል ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የውሳኔውን ይዘት መርምሮ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

**፴፪ <u>በውህደቱ ወይም በመከፈሉ በቀረበ ተቃውሞ ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ</u>**

፩ በውህደት ወይም መከፈል ላይ ተቃውሞ ሲቀርብ የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡-

ሀ) ከአባላት ወይም ከዕዳ ጠያቂዎች መካከል ያልተስማማ ወገን ካለ ልዩ ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት መብታቸው የሚጠበቅበት ውሳኔ እና ድርሻቸው መቀመጥ ወይም የክፍያ ዋስትና መሰጠት አለበት፤

ለ) ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የአባላት ወይም የገንዘብ ጠያቂዎች መብት መጠበቁን እና ሌሎች ህጋዊ ክፍያዎች መፈጸማቸውን በማረጋገጥ የውህደት ወይም የመከፈል ውሳኔውን ይቀበላል፤ አዲስ ማህበር ይመዘግባል፤ ዕውቅና ይሰጣል፤

ሐ) በውህደት ወይም በመከፈል ላይ ተቃውሞ ያላቸው አካላት ውህደት ወይም መከፈል ከመደረጉ አስቀድሞ ለማህበሩ እና ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ቅሬታቸውን እንዲያቀርቡና መፍትሄ እንዲሰጠው ማድረግ፤

መ) የመዋሃድ ወይም የመከፈል የአባላትን መብት ወይም የዕዳ ጠያቂዎችን እና የቅጥር ሰራተኞችን መብት ያልጠበቀ ከሆነ ወይም ሥራው ህግን እና ሥርዓትን ያልተከተለ መሆኑ ከተረጋገጠ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የውህደቱን ወይም የመከፈሉን ጥያቄ እዲሰረዝ ወይም እንዲዘገይ ማድረግ፤

13. Cooperative societies can be amalgamated or divided only when the commission or office examines the content of the decision and approves it.

**32. <u>Action to be Taken Against Objections to the Amalgamation or Division</u>**

1. The following steps may be taken in the event of an objection to a amalgamation or division:

a) If there is a dissenting party among the members or creditors, before the execution of the special resolution, their rights must be secured and their shares must be reserved or payment guaranteed;

b) The commission or office accepts the decision of amalgamation or division by ensuring that the rights of members or creditors are protected and other legal payments are made, registers a new cooperative society;

c) To make the parties who have objections to the amalgamation or division to submit their complaints to the cooperative society and the commission or the office before the amalgamation or division is carried out and have it resolved;

d) If the amalgamation or division does not protect the rights of the members or the rights of creditors and employees, or if it is proven that the work does not follow the law and order, the commission or the office to cancel or delay the request for the amalgamation or division;

፪ በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚወሰን የመከፈል ወይም የመዋሃድ ውሳኔ ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ማድረግ፡፡

፴፫ **ስለመነሻ ካፒታል**

የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩ ማንኛውም መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበር ሲቋቋም በሚያቀርበው የስራ እቅድና የአዋጭነት ጥናት መሰረት ቢያንስ የመጀመሪያ ዓመት የስራ ማስኬጃ ወጭዎቹን መሸፈን የሚችል ካፒታል ይዞ መመስረት አለበት፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረት ሥራ ዩኒዬንን ለመመስረት መሥራች መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በአዋጭነት ጥናት መሰረት እቅዳቸውን ለመፈፀም የሚያስችል በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን ሀያ አምስት በመቶ (፳፭%) ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ነው፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ሊመሰረት የሚችለው በተደረገው የአዋጭነት ጥናት መሰረት እቅዳቸውን ለመፈፀም እንዲያስችል በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት አባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ቢያንስ የጠቅላላ ካፒታላቸውን ሰላሰ በመቶ (፴%) ያህል ዕጣ መግዛት ሲችሉ ይሆናል፡፡

፴፬ **የብቃት ምዘናና ደረጃ እውቅና አሰጣጥ**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የመመዘን ጥያቄ በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፤

2. To ensure that the decision of division or amalgamation of any cooperative society is made free from any interference.

33. **Initial Capital**

Subject to the provisions of Article 22 of the proclamation:

1. When any primary cooperative society is established, it must be established with a capital that can cover at least the first year's operating expenses based on the work plan and feasibility study it submits;
2. To establish a cooperative society union, the founding primary cooperative societies can purchase share of at least twenty-five percent (25%) of their total capital based on a special decision of the general assembly to carry out their plans based on a feasibility study;
3. A federation of cooperative societies can be established when the member cooperative society unions are able to purchase at least thirty percent (30%) of their total capital based on a special decision of the general assembly to enable them to carry out their plans based on the feasibility study.

34. **Competency Assessment and Level Recognition**

1. Cooperative societies must submit a request for assessment in writing to the commission or the office;

፪ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ብቃት ምዘና በአዋጁ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በየሶስት ዓመቱ የመመዘን ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ለተመዘኑት ኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ እውቅና የምስክር ወረቀቱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ሆኖ የብቃት ምዘና ውጤቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት የምስክር ወረቀቱን በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ እና ሲጠየቁም የማሳየት ግዴታ አለባቸው፤

፬ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስመዘን ጥያቄ ካላቀረበ እና ካላስመዘነ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ አያድስለትም፤ እንዲሁም ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲታግድ ይደረጋል፤

፭ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ምዘናና ደረጃ ማረጋገጥ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፴፭ የኅብረት ሥራ ማህበር ስም ስያሜ እና አርማ ትርጉም

፩ በአዋጁ አንቀጽ ፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ የምዝገባ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ ስም ሊኖር አይችልም፤

፪ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የሚወሰን አርማ፣ የአርማ ትርጓሜ እና ማህተም ይኖረዋል፤

፫ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ስም፣ አርማና ማህተም ሥራ ላይ መዋል የሚችለው ሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ ያላቀረቡ መሆኑ በህግ ሲረጋጋጥ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ዘንድ ቀርቦ ሲመዘገብ ብቻ ነው፤

2. Regarding the assessment of the competence of the cooperative societies, they are obliged to evaluate it every three years, and the commission or the office will give the certificate of recognition of the competence level to the evaluated cooperative societies within a period of one month;
3. Cooperative societies are obliged to keep the certificate in a visible place and show it when asked;
4. If the cooperative society does not submit a request for certification within the specified time limit and does not certify, the commission or the office will not renew the registration certificate of the cooperative society, also, the cooperative society will be suspended;
5. It will be implemented according to the directive for the evaluation and verification of the level of cooperative societies.

## 35. The Meaning of Name and Logo of the Cooperative Society

1. Subject to the provisions of article 9 of the proclamation, there cannot be more than one name in one registration area;
2. Any cooperative society shall have a logo, interpretation of the logo and a seal determined by a special resolution of the general assembly;
3. The name, logo and seal of any cooperative society can be used only when it is registered with the commission or the office when it is confirmed by law that the third parties have not filed a complaint;

፬. የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ማህተም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አርማ የያዘ ሆኖ ማህተሙ የግርጌው ክብ እና የራስጌው አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሊሆን ይችላል፤

፭. በማህተሙ ላይ የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ እንደ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነትና ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት የሚጠቀሙበትን ሊወስን ይችላል፤

፮. በሥራ ባህሪያቸው በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ የሚሳተፉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማህተም የላይኛው ክፍል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሙሉ ስም በከተማ አስተዳደሩ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ከታች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያለው እና መሀሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አርማ የያዘ ሊሆን ይችላል፤

፯. የኅብረት ሥራ ማህበራት አርማ ግልፅ ትርጉም ያለው ሆኖ ተግባራቸውን የሚገልፅ፣ የአካባቢውን ባህል፣ ታሪክ፣ እሴትና የወደፊት ተስፋን የሚያሳይ ሆኖ መቀረፅ ይኖርበታል፤

፰. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚያመርተው ምርት ላይ ህጋዊነቱ ለማረጋገጥ የሚያገለግል የራሱን አርማና ማህተም መጠቀም አለበት፤

፱. የኅብረት ሥራ ማህበር አርማና ማህተም ተመሳሳይና አሳሳች መሆን የለበትም፤

፲. የኅብረት ሥራ ማህበር አርማና ማህተም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ ሌሎች መግለጫዎችና በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በሚፈረሙ ሰነዶች ላይ ማረፍ አለበት፤

4. The seal of any cooperative society may have the name and logo of the cooperative society and the seal may have a circular shape at the bottom and a rectangular shape at the top;
5. Regarding the use of language on the seal, it may determine what is used in the country and abroad, although it varies according to the type and level of cooperative societies;
6. The upper part of the seal of the cooperative societies involved in international relations may have the full name of the cooperative society in the working language of the city administration, the bottom in English and the center of the cooperative society's logo;
7. The logo of the cooperative societies should have a clear meaning and should be designed to describe their activities and show the local culture, history, values and future hopes;
8. Any cooperative society must use its own logo and stamp on the product it produces to prove its legitimacy;
9. The logo and seal of the cooperative society must not be similar or misleading;
10. The logo and seal of the cooperative society must be placed on the cooperative society's announcements, letters, other statements and documents signed in the name of the cooperative society;

፲፩ የኅብረት ሥራ ማህበር ስም፣ አርማ እና ማህተም መለወጥ የሚቻለው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ሆኖ አዲስ ስም፣ አርማ እና ማህተም ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ዘንድ ቀርቦ ሲመዘገብ ብቻ ነው፤

፲፪ ማንኛውም ሰው ከኮሚሽኑ ወይም ከጽህፈት ቤቱ ፍቃድ ሳያገኝ በስም፣ በአርማ እና በማህተም ላይ "የኅብረት ሥራ ማህበር" የሚለውን ስያሜ መጠቀም አይችልም፡፡

**፴፮ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ክልል</u>**

፩ በአንድ የሥራ ክልል ውስጥ ተመሳሳይ የሥራ መስክ፣ ዓላማ እና ተግባር ያላቸው የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነቶች ሊቋቋሙ አይችሉም፤

፪ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አባላትን ተደራሽ ለማድረግ በሥራ ክልሉ ውስጥ የተለያዩ ቅርንጫፎችን ሊከፍት ይችላል፤

፫ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት የሥራ ክልል ውጪ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዋና ጽህፈት ቤት ወይም ቅርንጫፍ መክፈት አይችልም፤ ሆኖም ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል የዋናው ጽህፈት ቤት የአገልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ሲፈቀድለት ሊከፍት ይችላል፤

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የግብይት ተግባራት ላይ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሥራ ክልላቸው ወጪ የተለያዩ መዳረሻዎች ላይ የገበያ ትስስር ማድረግ የሚያስችል የጉዳይ ማስፈፀሚያ ወይም የአግልግሎት መስጫ ጽህፈት ቤት ወይም ሱቅ መክፈት ይችላሉ፤

11. The name, logo and seal of a cooperative society can be changed only when a new name, logo and seal is submitted and registered to the commission or the office as a special decision of the general assembly;
12. No person may use the designation "cooperative society" in its name, logo or seal without obtaining permission from the commission or its office.

36. **<u>Cooperative Societies Working Area</u>**

1. Types of consumer cooperative societies that have the same field of activity, objective, and function cannot be established in one work area;
2. Any cooperative society may open various branches within its area of operation to provide access to members;
3. Any cooperative society cannot open its head office or branch outside of the working area in which it is registered, however, for the sake of efficiency, the main office may open a service branch when the commission or the office approves;
4. Notwithstanding the provision of sub article (3) of this article, cooperative societies engaged in marketing activities shall establish market linkages in different destinations at the expense of their working area can open a case execution or service office or shop;

፭ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሥራ ክልሉ ውስጥ የአግልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ ወይም ከሥራ ክልሉ ውጪ የጉዳይ ማስፈፀሚያ ወይም የአግልግሎት መስጫ ጽህፈት ቤት እና ሱቅ ሲከፍት፡-

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፤

ለ) በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በሚገባ መካተት ይኖርበታል፤

ሐ) በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ እውቅና ሊኖረው ይገባል፤

፮ ተከፍቶ የነበረን የጉዳይ ማስፈፀሚያ ወይም የአግልግሎት መስጫ ጽህፈት ቤት ወይም ሱቅ ቅርንጫፍ እንዲዘጋ ሲወስን፤

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፣

ለ) የሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ አለመኖሩን በህግ ማረጋገጥ አለበት፣

ሐ) አሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

**፴፯ <u>የመስሪያ ቦታ መግለጫ</u>**

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር፡-

፩ ሲደራጅ ሥራውን የሚያከናውንበት በምደባ፣ በግዥ፣ በኪራይ ወይም በስጦታ ወይም በሌላ ሕጋዊ አግባብ የተገኘ የመስሪያ ቦታ ይኖረዋል፤

፪ ያገኘውን ህጋዊ የሆነ ቦታ መግለጫ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በማቅረብ ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፫ የመስሪያ ቦታ የአድራሻ ለውጥ የሚያደርግ ከሆነ የተደረገውን ለውጥ የሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ አለመኖሩን በህግ ሲረጋገጥ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡



5. When any cooperative society opens a service provision branch in its working area or a case execution or service providing office and shop outside its working area:
   a) Must obtain the approval of the general assembly;
   b) It should be properly included in the bylaws;
   c) Must be recognized by the commission or its office;
6. When we decide to close an open case execution or service office or store branch:
   a) Must obtain the approval of the general assembly;
   b) It must be confirmed by law that there are no complaints from third parties;
   c) He should notify the commission or the office in writing within fifteen days.

**37. <u>Description of Working Area</u>**

Any cooperative society shall:

1. When organized, it will have a place of work obtained by assignment, purchase, rent or gift or other legal means to carry out its work;
2. It must register or notify the commission or the office with a statement of the legal position he finds;
3. If a workplace changes its address, it must notify the commission or the office by letter within thirty days after confirming that there are no complaints from third parties.

፴፰ **የኅብረት ሥራ ማህበራት ግዴታ**

በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሯቸዋል፡-

፩ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት አግባብ ላለው ባለሥልጣን መረጃዎችን የማስተላለፍ ግዴታ፤

፪ አግባብነት ያላቸውን ህጎች፣ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች ልዩ ልዩ ደንቦች ቅጅዎችን በኅብረት ሥራ ማኅበሩ አድራሻ እንዲገኙና በነፃ እንዲታዩ ማድረግ፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም እንደአግባቡ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም በጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር፡-

ሀ) አባላትን በመወከል ከምዝገባ ጀምሮ ያሉትን የባንክ ዝግ ቁጠባ ሂሳብ፣ የመሬት፣ የግብዓትና ሌሎችም እንዲሟሉ የማድረግ፤

ለ) ህገ-ወጥነትና ያልተገባ ተጠቃሚነትን ለመከላከል የሚደረገውን ሂደት የመደገፍና የመተባበር፤

ሐ) የከተማውን ፕላን መሠረት ባደረገ መልኩ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም በጋራ ህንጻ ባለቤቶች ኅብረት ሥራ ማህበር ሊገነቡ የሚችሉትን በጥናት ላይ ተመስርቶ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ የተለያዩ የህንፃ ዲዛይኖች የማዘጋጀት፤ ጠቅላላ ጉባኤ ለምርጫ በማቅረብ ውሳኔ ያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግ፤

መ) አባላቱ የሚፈለግባቸውን የቤት መስሪያ ዋጋ ክፍያ በተቀመጠው የአንድ ቤት ግንባታ ዋጋ ግምት መሠረት በተከፈተው የባንክ አካውንት ገቢ የማስደረግ፣ መረጃዎችንም በአግባቡ አደራጅቶ የመያዝ፤

38. **Obligations of Cooperative Societies**

Subject to Article 18 of the proclamation, cooperative societies shall have the following obligations:

1. Obligation to transmit information about the activities they perform to the appropriate authority;
2. Make copies of relevant laws, bylaws and other miscellaneous internal rules available at the address of the cooperative society and be viewed free of charge;
3. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) and (2) of this article, a housing cooperative society or a condominium owners' society, as the case may be:
   a. To fulfill the bank's closed savings account, land, resources and others since registration on behalf of the members;
   b. To support and cooperate in the process of preventing illegality and improper use;
   c. To prepare various building designs that meet their standards based on the study of what can be built by housing cooperative societies or condominium owners' cooperative societies based on the city plan, to make the decision of the general assembly to be put into effect;
   d. The members are required to pay the cost of construction of a house based on the estimated cost of building a house, to make income in the bank account opened, and to keep the information properly organized;

ረ) ግንባታው በተቀመጠው ዲዛይንና በውሉ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን የመከታተልና የመቆጣጠር፤

ሰ) የግንባታ መጠናቀቁን በማረጋገጥ ለአባላት ቤታቸውን አግባብ ያለው ባለስልጣን በተገኘበት በእጣ የማስረከብ፤

ሸ) ለልማት የሚሰበሰቡ መዋጮዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ የማስደረግ፤

በ) ልማት ለማሻሻል በሚደረግ ሂደት የሚፈጸም ማነኛውም ግዥ ወይም ሽያጭ በኅብረት ሥራ ማህበራት የግዥና ሽያጭ ሕግ መሰረት የመፈጸም፤ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል አራት

## የኅብረት ሥራ ማህበር አባልነት መስፈርቶች፣ መብትና ግዴታ

### ፴፱ ለአባልነት የሚያበቁ መስፈርቶች እና መተካካት

፩ በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባልነት መስፈርት በተጨማሪነት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ክልል የሚኖር ወይም የሚሰራ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበር ካዘጋጀው ዕጣ መግዛት የሚችል እና የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈል የሚችል፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጠ ደንብ፣ ልዩ ልዩ የአፈጻጸም መመሪያዎችን እና በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቁ ውሳኔዎች ለመፈፀም ፍቃደኛ የሆነ፤

መ) በሌላ ተመሳሳይ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ያልሆነ፤

ሠ) አባልነቱ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ከመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ ከሆነ በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ተመዝግቦ ህጋዊ ሰውነት ያገኘ መሆን አለበት፤

e. To monitor and control that the construction is being carried out according to the set design and contract;

f. Confirming the completion of construction and handing over their houses to the members by lot where the appropriate authority is present;

g. To ensure that contributions collected for development are used properly;

h. They have an obligation to carry out any purchase or sale in accordance with the Law on Purchase and Sale of Cooperative Societies.

## PART FOUR

## COOPERATIVE SOCIETY MEMBERSHIP REQUIREMENTS, RIGHTS AND DUTIES

### 39. Qualification for Membership and Replacement

1. Subject to the provisions of the proclamation, the membership criteria for cooperative societies shall additionally include:

a) living or working in the working area of the cooperative society;

b) Able to purchase from the shares prepared by the cooperative society and able to pay the registration fee;

c) Who is willing to comply with the cooperative society's bylaws, internal rules, various implementation directives and resolutions approved by the general assembly;

d) Not a member of any other cooperative society;

e) If the membership is primary cooperative societies and above primary cooperative societies, it must be registered by the commission or the office and obtained legal personality;

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሀ) ለተቀመጠው መስፈርት አግባብ ካለው አስፈጻሚ አካል ደጋፊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር የተደራጀ ወይም የሚደራጅ አገልግሎት ፈላጊ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) በመደራጀት ቤት ለመሥራት የሚፈልጉ አባላት ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ አግባብ ካለው አካል ተረጋግጦ ሲመጣ፤

ለ) ተደራጅተው ቤት የሚሰሩበት ቦታ ከሦስተኛ ወገን ነጻ ስለመሆኑ እና የግንባታ ዲዛይኑን ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማረጋገጫ ሲቀርብ፤

ሐ) የሚገነባበት ቦታ የከተማው ማስተር ፕላን በሚፈቅደው መሰረት እና የአካባበውን ደህንነትና ልማት ከግምት ያስገባ ስለመሆኑ ከሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ማቅረብ ሲችል፤

መ) እንደ አግባብነቱ የካርታ፣ የፕላን፣ የግንባታ ፍቃድ፣ የሊዝ እና የሚያስፈልጉ ሰነዶችን አሟላቶ ሲቀርብ ነው፤

፫ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (መ) ድረስ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት ሠራተኞች በቤቶች ኅብረት ሥራ ማህበር ለማደራጀት በወጣው ደንብ ላይ የተገለጸውን መስፈርት በተጨማሪ አሟልተው መገኘት አለባቸው፤

f) He must provide supporting evidence from the appropriate executive body for the requirements set forth in sub article (1) of this article;

2. Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this article, a service seeker who is organized or organized by any housing cooperative societies or condominium owners' association must meet the following requirements:
   a) When the full name, address and signature of the members who want to work in the organization house is confirmed by the relevant body;
   b) When a confirmation is provided from the relevant government offices about the location of the organized house being independent from a third party and the construction design;
   c) When he can submit from the relevant government office that the place to be built is in accordance with the city's master plan and takes into account the safety and development of the surrounding area;
   d) When the relevant documents such as maps, plans, construction permits, leases and documents are submitted;
3. Subject to the provision of sub article (2) of this article from letters (a) to (d), government employees must also meet the requirements stated in the regulation for organizing housing cooperative societies;

፬ በግል አልሚዎች ወይም በሪል ስቴት ደረጃ ተገንብተው የተጠናቀቁ እና በግለሰብ ደረጃ የተያዙ ቤቶቸን በጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር የሚደራጁት ህጋዊ መረጃዎችን ከሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ይዘው ሲቀርቡ ብቻ ይሆናል፣

፭ በመንግስት የቤቶች ልማት ፕሮግራም የሚደራጁ የመንግስት ሠራተኞችን ከዚህ በፊት በተለያየ መንገድ ቤት ማግኘታቸውን እያወቀ መረጃ የሰጠ ወይም ያደራጀ አካል አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

፮ የማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር አባላት የመተካካት ሁኔታ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) በመንግስት የተደራጁ ከሆነ የመኖሪያ ቤት ኅበረት ሥራ ማህበሩ አባል በተለያየ ምክንያት ሲጓደል በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅና በዚህ ደንብ መሠረት እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንባቸው ተመሳሳይ መብት ያለውን ምትክ አባል የሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት በሚልከው መሰረት የሚተካ ይሆናል፣

ለ) የጋራ ህንጻ ማህበሩ አባል በተለያየ ምክንያት ሲጓደል በኅብረት ሥራ የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ተመሳሳይ መብት ያለውን ምትክ አባል በሥራ አመራር ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ሲጸድቅ የሚተካ ይሆናል፡፡ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ያሳውቃል፣

4. Houses built and completed by private developers or real estate and owned by individuals will be organized by condominium owners' association only when they are presented with legal information from the relevant government office;
5. A party that provides information or organizes government employees organized by the government's housing development program, knowing that they have previously obtained housing in different ways, will be held responsible according to the relevant law;
6. The replacement of members of any housing cooperative societies or condominium owners association shall be as follows:
   a) If they are organized by the government, when a member of the housing cooperative society dies due to various reasons, he will be replaced by a replacement member who has the same rights according to the proclamation and this regulation of the cooperative societies and as sent by the relevant government office;
   b) When a member of the condominium owners association dies due to various reasons, he will be replaced by a replacement member who has the same rights in accordance with the proclamation and regulations issued to implement the condominium owners association's declaration and bylaws. Notifies the commission or its office;

ሐ) በተለያየ ሞዳሊቲ በግል አልሚዎች በመኖሪያ ቤት ኅበረት ሥራ ማህበሩ አባል በተለያየ ምክንያት ሲጓደል በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ በዚህ ደንብ እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ተመሳሳይ መብት ያለውን ምትክ አባል በሥራ አመራር ኮሚቴው ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ የሚተካ ይሆናል፤

መ) መንግስት በሚያመቻቸው የቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ኅበረት ሥራ ማህበር በመሥራት ላይ ያሉ አባላት ከአምስት ዓመት በፊት መተካካት አይችሉም፤

ሠ) አባላት በራሳቸው ቦታ ላይ በመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ወይም በጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር የተደራጁ ወይም የሚደራጁ አባላት በማንኛውም የግንባታ ደረጃ ላይ መተካካት ይችላሉ፤

ረ) መንግስት በሚያመቻቸው የቤት ልማት ፕሮግራም ፴ በመቶ ቁጠባ ፸ በመቶ ከባንክ ብድር የተደራጁ የመተካካት ሂደት የሚፈጸመው ከቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ በሚመጡ ተተኪዎች መሰረት የሚተኩ ሲሆን እና የአተካክ ሂደቱ እየተሰራ ያለውን ህንጻ የግንባታ ደረጃ መሰረት ያደረገ ሆኖ ለተኪው ተተኪው የሚከፍለው ገንዘብ በወቅቱ ግንባታው የደረሰበትን ደረጃ መሰረት ያደረገ ከሆነ ነው፤

፯. የግል አልሚዎችና በራሳቸው ቦታ ላይ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር የመተካካት ሂደቱ በመተዳደሪያ ደንባቸው የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በተተኪና በተኪ ግለሰብ አባላት የጋራ ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ሲሆን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

c) When a member of the cooperative society housing association absent for various reasons by private developers in different modalities, a replaced member who has the same rights according to this regulation and their bylaws will be replaced when presented by the management committee and approved by the general assembly;

d) Members who are working in housing cooperative societies organized in the government facilitated housing development program cannot be replaced before five years;

e) Members who are or will be organized in a housing cooperative society or condominium owners association in their own place can be replaced at any stage of construction;

f) In the housing development program facilitated by the government, 30 percent savings and 70 percent from bank loans, the replacement process will be carried out based on replacements from the Housing Development and Management Office, and the replacement process will be based on the construction level of the building under construction, if the money paid to the replacement is based on the level of construction at the time.

7. The process of replacement of private developers and housing cooperative societies or condominium owners' associations on their own land shall be carried out according to the mutual agreement of the individual members of the successor and representative, and must meet the following:

ሀ) አባሉ ሌላ አባል ለመተካት ፈቃደኛ መሆኑን በአካል ወይም በህጋዊ ተወካዩ በማመልከቻ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ወይም ለጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ማቅረብ አለበት፤

ለ) ተኪው አባል ባለትዳር ከሆነ የሚቀርበው ማመልከቻ የሚስትን ወይም የባልን በፊርማ ፈቃደኝነት የተረጋገጠ እና የታደሰ መታወቂያ ፎቶ ኮፒ ያካተተ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

ሐ) ተተኪው የኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር አባል ሆኖ ለመቀጠል ማመልከቻ እና የታደሰ መታወቂያ እና ሌሎች መረጃዎችን ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ማቅረብ አለበት፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የመተካካት ሂደቱን ሲያጸድቅ በተኪው ቦታ የገባውን ተተኪው መረጃ እንዲሁም የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በፊርማ ተረጋግጦ ለአደረጀ መሰሪያ ቤቱ መላክ ይገባል፤ የስም ማስተካከያ ለውጥም ያደርጋል፤

ሠ) በየቤት ግንባታ ደረጃው የደረሰበትን ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት በተተኪውና በተኪው መካከል ክፍያን በተመለከተ መግባባት ላይ ስለ መድረሳቸው በፊርማቸው እና በሶስት ምስክር የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፤

ረ) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው አባሉ በሞት የተለየ ከሆነ ህጋዊ ወራሽነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበና እንዲሁም በሽያጭ የቤቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ ካቀረበ በጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ ሊተካ ይችላል፤

a) The member must submit to the management committee of the cooperative society or the owners of the condominium, in person or by his legal representative, that he is willing to replace another member;

b) If the proxy member is married, the application submitted must include information including a photocopy of the wife's or husband's signed and renewed ID;

c) The successor must submit an application and renewed identification and other information to the cooperative society to continue as a member of the cooperative society or condominium owners' association;

d) When the general assembly of the cooperative approves the process of replacement, the information of the successor entered in the place of proxy and the decision of the general assembly should be confirmed with a signature and sent to the executive office, a name adjustment will also make a change;

e) Taking into account the status of the construction stage of each house, they must provide proof of their signature and three witnesses confirming that they have reached an agreement regarding payment between the successor and the proxy;

f) In the case of the death of the member, in the case of sub article (7) of this article, letters (a) to (e) are preserved, if the member submits proof of his legal inheritance and also if he submits a legal document confirming that he is the owner of the house in the sale, he can be approved and replaced by the general assembly;

፰ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፯ ተራ ፊደል ከ(ሀ) እስከ (ረ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመተካካት ሂደት ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር እዳ ያለበት ከሆነ በአዲስ የሚተካው አባል ሙሉ ኃላፊነት የሚወስድ ይሆናል፡፡

፵ **አባል ለመሆን የሚቀርብ ማመልከቻ**

፩ አባል ለመሆን የሚፈልግ ግለሰብ ወይም የኅብረት ሥራ ማህበር የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ያዘጋጀውን የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያቀርባል፤

፪ የሥራ አመራር ኮሚቴው የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ መቀበሉን ወይም አለመቀበሉን በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ መሰረት ለአመልካቹ ያሳውቃል፤

፫ አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው ለጠቅላላ ጉባዔ በፅሑፍ ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፵፩ **የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት መብት**

በአዋጁ አንቀፅ ፳፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል የሚከተሉትን መብቶች ይኖሩታል፡-

፩ ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው አስፈላጊውን መረጃ የማግኘት፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ማንኛውም ጥያቄ፣ ቅሬታና አስተያየት የማቅረብና መልስ የማግኘት፤

፫ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ላይ ያለ ልዩነት የመሳተፍ፣

፬ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተወካይ የመወከል፤

8. Subject to the provisions of sub article 7 of this article from (a) to (f), in the process of replacement, if any housing cooperative society or condominium owners' association is in debt, the new member will be fully responsible.

40. **Application to become a Membership**

1. An individual or a cooperative society wishing to become a member shall fill out the membership application form prepared by the cooperative society;
2. The management committee will examine the application submitted to it and inform the applicant whether it has been accepted or not, according to the time limit determined by the bylaws;
3. If the applicant is dissatisfied with the decision, he may appeal in writing to the general assembly.

41. **Rights of Cooperative Societies Members**

Subject to Article 25 of the proclamation, any member shall have the following rights:

1. Obtaining necessary information from their cooperative societies;
2. Submitting and receiving answers to any questions, complaints and comments on issues concerning the cooperative society;
3. To participate in the training provided by the cooperative society without discrimination;
4. To act as a representative when necessary;

፭ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተደነገገው ቢኖርም የማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር አባል:-

ሀ) ድርሻውን የማከራየት ፣ የመሸጥ፣ በስጦታ መስጠት፣ የመለወጥ እና የማውረስ፤

ለ) ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር አባሉ በተሰናበተ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጥቅምና ድርሻውን ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፵፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ግዴታ

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችንና የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን የማክበር፤

፪ የሚሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት እና በጋራ የሚሰሩ ሥራዎችን የማከናወን፤

፫ ማንኛውም አባል በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚሰጠውን ሥራዎችን የመሥራት፤

፬ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ፤

፭ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ግብይት ተሳትፎ የማድረግ፤

፮ ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት እንዲሸጥ የታወጀው የዕጣ መጠን ተሸጦ ሲጠናቀቅ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተጨማሪ ካፒታል ካስፈለገው አባሉ የመግዛት ግዴታ አለበት፤

፯ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) የተደነገገው ቢኖርም የማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር አባል፡-

ሀ) በተረከበው የቤት ክፍል ውስጥ በሌሎች ነዋሪዎች ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር የሚችል ተግባርን አለመፈፀም፤

5. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) to (4) of this article, a member of any housing cooperative society or condominium owners' association shall:
   a) Renting, selling, gifting, exchanging and bequeathing the shares;
   b) Unless there is a force majeure problem, the member should get the benefit and share within two months of dismissal.

42. **Duties of Cooperative Society Members**
   1. To comply with the cooperative society's bylaws, internal rules and decisions of the general assembly;
   2. To carry out the assigned responsibilities properly and to carry out joint tasks;
   3. Any member to carry out the tasks assigned to him according to the bylaws of the cooperative society;
   4. To protect and take care of the cooperative society's asset;
   5. To participate in the marketing of the cooperative society;
   6. Any member is obliged to purchase the additional capital of the cooperative society when the amount of lots declared to be sold based on the decision of the general assembly is sold;
   7. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) to (6) of this article, a member of any housing cooperative society or condominium owners' association shall:
      a) Not to carry out activities that may affect other residents in the rented house;

ለ) የመኖሪያ ቤት ኅበረት ሥራ ማህበሩን እና የጋራ ሕንጻ ማህበሩን ኪሣራ በጋራ የመካፈል፤

ሐ) ግንባታ ሲጠናቀቅ በአካል ወይም በተወካዩ አማካኝነት በቦታው በመገኘት የመረከብ ግዴታ፤

መ) በመረጠው ቤት ዲዛይን አማካኝነት የሚጠበቅበትን የቤቱን ወጪ ወደ ተዘጋጀው የሂሳብ አካውንት ገቢ የማድረግ አለበት፡፡

**፵፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከአባልነት ስለመሰናበት**

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ሁኔታዎች አባል ከኅብረት ሥራ ሊሰናበት ይችላል፡-

፩ በሞት ሲለይ፤

፪ አባሉ በተደጋጋሚ የሚጠበቅበትን ግዴታ አለመወጣት፤

፫ ለሦስት ተከታታይ መደበኛ ስብሰባ ያለ በቂ ምክንያት አለመሳተፍ፤

፬ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማና ተግባር ጋር የሚፃረር ተግባር መፈጸም፤

፭ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ንብረቶችን የግል ጥቅም ለማግኘት ሲል ከገበያ ዋጋ በታች መሸጥ ወይም ከገበያ ዋጋ በላይ መግዛት ወይም እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ማድረግ፤

፮ በተለያየ ምክንያት በእጁ የገባውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት ለግል ጥቅሙ ያዋለ ወይም እንዲውል ማድረግ፤

፯ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ጉቦ ወይም መደለያ የሰጠ ወይም መቀበል፤

፰ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ሆን ብሎ ማጉደል ወይም እንዲጎድል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

b) To commonly share the losses of the housing association and the condominium association;

c) Obligation to take over by being present at the site in person or through a representative upon completion of construction;

d) He should deposit the cost of the house, which is expected to be averaged by the design of the house he has chosen, to the account set up.

43. **Dismissal of Members of Cooperative Societies**

Subject to the provisions of the proclamation, a member may be dismissed from the cooperative society under the following circumstances:

1. When he died;
2. The member repeatedly fails to fulfill his obligations;
3. Failure to attend three consecutive regular meetings without sufficient reason;
4. Doing actions that goes against the objectives and activities of the cooperative society;
5. Selling or buying from cooperative society or selling below market value or buying above market value or causing it to be sold or bought for the purpose of personal gain.
6. For different reasons, he spends the asset of the cooperative society for his personal benefit or causes it to be spent;
7. Gives or accepts bribes or kickbacks on behalf of the cooperative society;
8. Deliberately misappropriating or facilitating the misappropriation of the cooperative society's funds;

፱ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያቀርበውን ምርት ወይም የአገልግሎት ዋጋ በማይገባው ሁኔታ ለማግኘት ጥራቱን ያጓደለ ወይም መጠኑን የቀነሰ፤

፲ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፱) የተደነገገው ቢኖርም የማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት አባል በባንክ የቆጠበውን የገንዘብ ድርሻ ከግንባታ በፊት ወጪ አድርጎ ከወሰደ፡፡

## ፵፬ የቀድሞ ወይም አዲስ አባላትን ስለመቀበል

፩ የቀድሞ አባል ዳግም ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለመመለስ በተዘጋጀው የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሠረት ለሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ጥያቄውን ሊያቀርብ ይችላል፤

፪ በአዋጁ አንቀጽ ፳፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ጥያቄ የቀረበለት የማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ ለመስጠት የሚከተሉት ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባል፡-

ሀ) የአባልነት ጥያቄ አቀራቢው በኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ክልል ውስጥ ስለመገኘቱ፤

ለ) በሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር የሥነ-ምግባር ችግር እንደሌለበትና እና ግዴታውን ስለመወጣቱ፤

፫ አባሉ ቀደም ሲል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የተሰናበተበትንና ዳግም የሚመለስበትን ምክንያት በተዘጋጀው ፎርም መሠረት ዝርዝር መረጃ መያዝ አለበት፤

9. Reduces the quality or quantity of the products or services provided to the cooperative society in order to obtain an unreasonable price;
10. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) to (9) of this article, if a member of any housing cooperative society takes the share of fund saved in the bank as an expense before construction.

## 44. Accepting Former or New Members

1. A former member can submit his request to the members of the management committee according to the membership application form prepared to return to the cooperative society;
2. Subject to the provisions of article 26 of the proclamation, the management committee of the cooperative society, which is asked according to sub article (1) of this article, will take into account the following conditions to make a decision:
   a) The presence of the applicant for membership in the working area of the cooperative society;
   b) that there is no ethical problem in another cooperative society and that it fulfills his obligations;
3. According to the form, the member must have detailed information about the reason for his dismissal from the cooperative society and the reason for his return;

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተቀመጡትን ሁኔታዎች በመመርመር የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የአባልነት ጥያቄው ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭ የቀድሞ አባላት ዳግም እንዲመለሱ በሥራ አመራር ኮሚቴ ሲፈቀድ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነውን መመዝገቢያ እና ዝቅተኛውን የዕጣ ዋጋ ክፍያ መፈጸም አለባቸው፤

፮ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ወይም ዳግም የተመለሰ የቀድሞ አባል የሚከፍለው የመመዝገቢያ ክፍያ ቀድሞ በጠቅላላ ጉባዔ የተወሰነውን ብቻ ይሆናል፤

፯ በአዋጁ አንቀጽ ፳፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኅብረት ሥራ ማህበሩ በአዲስ አባልነት ተቀባይነት ካገኘበትና ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ መብትና ግዴታዎቹ ተጠብቀው እንደ ማንኛውም አባል ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎት መጠቀም ይችላል፡፡

፮ <u>የአባላት መዝገብ ስለ ማደራጀት</u>

፩ በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአባላት መዝገብ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ መደበኛ ሥራ እና አባሉ የገዛው ዕጣ በገንዘብ ይይዛል፤

፪ የአባላት መዝገብ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ሲሆን የአባል ኅብረት ሥራ ማህበር ስም፣ የግለሰብ አባላት ብዛት፣ ፆታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ ካፒታል፣ ቁጠባ፣ የተቋቋመበት እና የፈረሰበት ቀንና ዓመት ምህረትን ይይዛል፡፡

4. The management committee of the cooperative society will make a decision on the membership request by examining the conditions set forth in sub article (2) of this article;
5. When former members are allowed to return by the management committee, they must pay the registration and the minimum share price determined by the cooperative society's bylaws;
6. Subject to the provisions of sub article (5) of this article, the registration fee paid by a new or reinstated former member shall be only the amount previously determined by the general assembly;
7. Subject to the provisions of article 26 of the proclamation, from the day he is accepted and registered as a new member by the cooperative society, his rights and obligations are protected and he can use the services provided by the cooperative society like any other member.

45. **<u>Organizing Register of Members</u>**

1. Subject to the provisions of article 28 of the proclamation, the register of members shall contain the marital status, number of families, regular occupation and the share purchased by the member;
2. The register of members is more than a primary cooperative society and contains the name of the member cooperative society, number of individual members, gender, family size, capital, savings, date and year of establishment and dissolution.

## ክፍል አምስት
## ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጭነት ጥናት፣ የንግድ ሥራ ዕቅድ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የኃላፊነት ደረጃ ፣ ምዝገባ፣ እጣ እና መመዝገቢያ

### ፵፮ የአዋጭነት ጥናት ስለ ማካሄድ

፩ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱን በጥናት ማረጋገጥ አለበት፤

፪ የአዋጭነት ጥናት በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ በሚቋቋመው የመሥራች ኮሚቴ አባላት የሚጠና ይሆናል፤

፫ ጥናቱ በአካባቢው ማህበራትን በማደራጀት ሊያስገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም፣ የህብረተሰቡን አኗኗር እና ምቹ ሁኔታዎች የሚያሳይ መሆን አለበት፤

፬ ሊደራጅ የታሰበው የኅብረት ሥራ ማህበር አዋጭነቱ በጥናት በማረጋገጥ እንዲደራጅ ወይም እንዳይደራጅ በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት፤

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፪) የሚካሄደው የኅብረት ሥራ ማህበሩን ለማደራጀት የሚደረገው የአዋጭነት ጥናት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት አለበት፡-

ሀ) የአባላትን ሁኔታ፣
ለ) ወደ ፊት አባል ስለሚሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት፣
ሐ) የአካባቢው ሀብት፣
መ) የማህበሩን ሀብት፣
ሠ) ተንቀሳቃሽ፣ ቋሚ ንብረት፣ ዕዳና ካፒታል፣
ረ) ማህበሩ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት፣
ሰ) የኢኮኖሚ አዋጭነት ሁኔታ፣
ሸ) የአገልግሎት ሁኔታ፣
ቀ) የአባል ማህበራት ምርትና አገልግሎት ሁኔታ፣

## PART FIVE
## COOPERATIVE SOCIETIES FEASIBILITY STUDY, BUSINESS PLAN, BYLAWS, LIABILITY, REGISTRATION, SHARE AND REGISTER

### 46. Conducting a Feasibility Study

1. Any cooperative society must verify its economic viability through research;
2. The feasibility study will be studied by the founding committee members established by the commission or the office;
3. The study should show the economic and social benefits that can be achieved by organizing cooperative societies in the area, the way of life and the favorable conditions of the community;
4. The cooperative society that is intended to be organized should be decided by the general meeting to confirm its feasibility or not to be organized;
5. The feasibility study for the organization of the cooperative society, which is conducted under sub article (2) of this article, must include the following conditions:
   a) Status of members;
   b) Cooperative societies that will become members in the future;
   c) Local wealth;
   d) The assets of the cooperative society;
   e) Movable, fixed properties, debt and capital;
   f) The main activities performed by the cooperative society;
   g) Economic viability status;
   h) Condition of service;
   i) Product and service status of member cooperative societies;

በ) የፍላጎት እና አቅርቦት ሁኔታ፣
ተ) የቴክኒክ አዋጭነት፣
ቸ) የፋይናንስ አዋጭነት ትንበያ፣
ነ) የማህበራዊ ተጽዕኖ፡፡

**፵፯ የንግድ ሥራ ዕቅድ ስለ ማዘጋጀት**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የንግድ ሥራ ዕቅድ በመሥራች ኮሚቴ አማካኝነት መዘጋጀት አለበት፤

፪ የንግድ ሥራ ዕቅድ ማህበሩ በቀጣይ ለሚያደርገው የሥራ እንቅስቃሴ እንደ ፍኖተ ካርታ ሊጠቀምበት ይችላል፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት የሚዘጋጀው የንግድ ሥራ ዕቅድ የሚከተሉት ይዘቶች ይኖሩታል፤

ሀ) የማህበሩ ራዕይ እና ተልዕኮ
ለ) የማህበሩ ዓላማ እና ተግባር
ሐ) የሁኔታዎች ትንተና
መ) የአገልግሎት ዕቅድ
ሠ) የገበያ ትንተና
ረ) የቁጠባና ብድር ዕቅድ
ሰ) የሰው ሀይል ዕቅድ
ሸ) የፋይናንስ ዕቅድ፡፡

**፵፰ የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ስለማዘጋጀት**

የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩ የመሥራች ኮሚቴ ኮሚሽኑ በሚሰጠው መነሻ ረቂቅ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ለሚደራጀው ኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ማዘጋጀት አለበት፤

፪ የመሥራች ኮሚቴው መተዳደሪያ ደንብ ሲያዘጋጅ የአዋጭነት ጥናትን እንደ ግብዓት ሊጠቀም ይችላል፤

፫ በመሥራች ኮሚቴው የተዘጋጀውን ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ በመሥራቾች ጉባዔ በማፀደቅ አዲስ ለሚመረጠው የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚተላለፍ ይሆናል፤

፬ የፀደቀ የመተዳደሪያ ደንብ በአባላት ላይ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት አለው፤

j) Demand and supply situation;
k) Technical feasibility;
l) Financial viability forecast;
m) Social influence.

**47. Preparing a Business Plan**

1. A cooperative society business plan should be prepared through a founding committee;
2. A business plan can be used by the cooperative society as a roadmap for its future activities;
3. The business plan prepared in accordance with the provisions of sub article (1) of this article shall have the following contents:
   a) Vision and mission of the cooperative society;
   b) The objective and function of the cooperative society;
   c) Situation analysis;
   d) Service plan;
   e) Market analysis;
   f) Savings and loan plan;
   g) Human resource planning;
   h) Financial planning.

**48. Preparation of Bylaws of the Cooperative Society**

Subject to the provisions of article 12 of the proclamation:

1. The Founding Committee shall prepare bylaws for the cooperative society to be organized according to the initial draft model bylaws provided by the commission;
2. The founding committee may use the feasibility study as input when drafting the bylaws;
3. The draft bylaws prepared by the founding committee will be passed on to the newly elected management committee after approval by the founding assembly.
4. Approved bylaws are binding and enforceable on members;

፭ የመተዳዳሪያ ደንቡ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የበላይ ህግ በመሆን ለተለያዩ የሥራና የአሰራር መመሪያዎች፣ ልዩ ልዩ መዋቅራዊ አደረጃጀቶች፣ ውሰጠ ደንቦች እና አፈፃፀሞች መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

**፵፱ <u>የመተዳደሪያ ደንብ ይዘት</u>**

በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን፡-

፩ ሥም፣ አርማ፣ አድራሻ እና የሥራ ክልል፤

፪ ራዕይ፣ ተልዕኮ፤ ዓላማና ተግባር፤

፫ መርሆዎችና ዕሴቶች፤

፬ የመመዝገቢያ እና የዕጣ ክፍያ፤

፭ የአባልነት ማመልከቻ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ፤

፮ ስብሰባ አጠራር፣ ምርጫና ድምፅ አሰጣጥ፤

፯ ኮሚቴ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች፤

፰ ጠቅላላ ጉባኤ ሁኔታ፤

፱ የገንዘብ ምንጭ፤

፲ የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፤

፲፩ የቁጠባ መጠንና አይነቶች

፲፪ የብድር ወሰንና አተገባበር፤

፲፫ የሚከፋፈል እና የማይከፋፈል ገንዘብ፤

፲፬ የሂሣብ አያያዝ፤

፲፭ ልዩ ልዩ መዛግብትና ሰነዶች፡፡

**፶ <u>መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል</u>**

፩ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር፡-

ሀ) የስም ወይም አርማ ለውጥ ሲያደርግ፤

ለ) አዳዲስ ተግባራትን ሲጨምር፤

ሐ) ህጎች በመቀየራቸው ወይም በመሻራቸው ምክንያት መተዳደሪያ ደንቡ መሻሻል ሲኖርበት የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊያደርግ ይችላል፤

5. The management bylaw serves as the supreme law of the cooperative and serves as a starting point for various work and operational directives, various structural arrangements, internal rules and executions.

49. **<u>Contents of Bylaws</u>**

Subject to the provision of article 12 of the proclamation, the bylaws of the cooperative society provide that the cooperative society:

1. Name, logo, address and area of work;
2. Vision, mission, objective and function;
3. Principles and values;
4. Registration and share fees;
5. Submission of membership applications and decision-making;
6. Convening of meetings, elections and voting;
7. Qualifications for becoming a committee member;
8. General assembly situations;
9. Source of funds;
10. Management and use of funds;
11. Amount and types of savings;
12. Loan scope and application;
13. Divisible and indivisible funds;
14. Accounting;
15. Miscellaneous records and documents.

50. **<u>Amending Bylaws</u>**

1. Any cooperative society shall:
   a) When making a name or logo change;
   b) Adding new functions;
   c) May amend the bylaws when the bylaws need to be amended due to changes or repeal of laws;

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ አግባብነት ያላቸውን ህጎች የጠበቀ መሆኑ ተረጋግጦ ይመዘገባል፤

፫ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ማንኛውንም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ የማይመዘግብ ከሆነ አለመመዝገቡን በአዋጁ መሠረት በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፬ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ በሚመዘግብበት ጊዜ የተረጋገጠውን ማሻሻያ ቅጅ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መስጠት አለበት፤

፭ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ካልፀደቀና ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ ካልተመዘገበ ተቀባይነት የለውም፡፡

**፶፩ ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ኃላፊነት**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኃላፊነታቸው የተወሰነ ነው፤

፪ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራቸው ውስጥ ካላቸው ድርሻ በላይ ተጠያቂ አይሆኑም፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገዉ ቢኖርም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበርን አይመለከትም፡፡

## ክፍል ስድስት
## የኅብረት ሥራ ማህበራት የስብሰባ ፣ የምርጫ እና የድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት

**፶፪ የስብሰባ ሥርዓት**

፩ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ በሥራ አመራር ኮሚቴ እንዲጠራ ይደረጋል፤

2. Bylaws amended pursuant to sub article (1) of this article shall be certified and recorded as conforming to relevant laws;
3. If the commission or office fails to register any amendment to the bylaws, it shall notify the non-registration in writing in accordance with the ordinance;
4. When the commission or the office registers an amendment to the bylaws of the cooperative society, it must give a certified copy of the amendment to the cooperative society;
5. Any amended bylaws of any cooperative society shall not be accepted unless approved by the general assembly and submitted to the registrar for registration.

**51. Liability of Cooperative Societies**

1. Cooperative societies have limited liability;
2. Members are not liable for more than their share in the cooperative society;
3. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) and (2) of this article, it shall not apply to a condominium owners' association.

## PART SIX
## MEETING, ELECTION AND VOATING PROCEDURE OF COOPERATIVE SOCIETIES

**52. Meeting Procedure**

1. The general assembly meeting will be held at least twice a year and will be called by the management committee.

፪. የጠቅላላ ጉባዔ ማስታወቂያ ስብሰባው የሚካሄድበትን ቀን ፣ ቦታና አጀንዳዎች ተጠቅሰው ከ ስብሰባው ፲፭ ቀናት በፊት ጥሪ ይደረጋል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በሥራ አመራር ኮሚቴ ሲወሰን ወይም ከጠቅላላ አባላት በአንድ ሶስተኛው ወይም በቁጥጥር ኮሚቴ ሲወሰን አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ሰብሰባ ጥሪ ሊደረግ ይችላል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት አባላቱ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ጠይቀው ሥራ አመራር ኮሚቴ ጥሪ ያላደረገ እንደሆነ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ጉባኤውን ይጠራል፣

፭. መደበኛ የጠቅላላ ጉባዔ ከጠቅላላ አባላት ከግማሽ በላይ ከተሟሉ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፤

፮. በመጀመሪያው ጥሪ ምልዐተ ጉባዔ ካልተሟላ በ ፲፭ ቀናት ውስጥ በድጋሚ ጥሪ ይተላለፋል፤ በድጋሚ ጥሪ ተደርጎ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ብቻ ስብሰባው ይካሄዳል፤ ስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት የተላፈው ውሳኔ በሁሉም አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

፯. ልዩ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ከጠቅላላው አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተሟሉ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፤ በመጀመሪያ የስብሰባ ጥሪ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በሚቀጥለው ፲፭ ቀናት ውስጥ እንዲደረግ ድጋሚ የስብሰባ ጥሪ ተደርጎ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ብቻ ስብሰባው ይካሄዳል ፤ ውሳኔውም የፀና ይሆናል፤

2. Notice of the general assembly will be called 15 days before the date, place and agenda of the meeting;
3. Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this article, an urgent general assembly meeting may be called when decided by the management committee or by one-third of the total members or by the control committee;
4. According to sub article (3) of this article, the commission or the office will call the meeting if the members have requested to call an urgent general meeting and the management committee has not called;
5. A regular general assembly will be a plenary assembly if more than half of the total members are present;
6. If the quorum is not met in the first call, a second call will be sent within 15 days; If the meeting is called again and the quorum is not met, the meeting will be held only by the members present; the decision passed by the members present at the meeting shall be binding on all members;
7. If two-thirds of the total members are present, a plenary session will be held for matters requiring a special resolution, if the quorum is not met in the first meeting call, a new meeting will be called to be held within the next 15 days. The decision will be final;

፰ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ላይ በመገኘት የስብሰባውን ሂደት ይታዘባል፤ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**፶፫ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርጫ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩ በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ማንኛውም ዓይነት የኮሚቴ አባላት ምርጫ የሚያካሂደው ፫ አባላት ባሉት አስመራጭ ኮሚቴ ይሆናል፤

፪ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ለመምረጥ ቢያንስ ፭ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መኖር አለባቸው፤

፫ የአስመራጭ ኮሚቴ ከኮሚሽኑ ወይም ከጽህፈት ቤቱ በሚወከሉ ባለሙያዎች እና በቀድሞ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ አስተባባሪነት በኅብረት ሥራ ማኅበሩ በጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣሉ፤

፬ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በአብላጫ ድምፅ ከተመረጡ በኋላ በኮሚቴው ውስጥ የሚኖራቸው የሥራ ክፍፍል እና ኃላፊነት ተመካክረው በመደላደል በጉባዔ እንዲፀድቅ ይደረጋል፤

፭ አስመራጭ ኮሚቴው በተሻሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት አዲስ በተመረጡት መካከል በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ህጋዊ የሥራ ርክክብ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

፮ ኅብረት ሥራ ማህበሩን ሲመሩ የነበሩ ነባር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የምርጫውን ሥነ-ሥርዓት እንዲያከናውኑ ስልጣናቸውን ለአስመራጭ ኮሚቴ ያስረክባሉ፤

፯ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በምርጫው ሂደት ላይ ጥርጣሬ ካለው አስመራጭ ኮሚቴውን ድጋሚ ሊያስመርጥ ይችላል፤

፰ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው፤ በድጋሚ ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ፤

፱ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) ድንጋጌ ቢኖርም ከአንድ የስራ ዘመን በኋላ ሊመረጡ ይችላሉ፤

8. The commission or the office shall attend any general assembly meeting of the cooperative societies and observe the proceedings of the meeting, provides professional support.

**53. <u>Election Procedure of Cooperative Societies</u>**

1. In cooperative societies, any kind of committee member election will be conducted by a 3-member selection committee;
2. There must be at least 5 candidates to elect members of the selection committee;
3. The selection committee will be elected by the general assembly of the cooperative society by experts represented by the commission or the office and coordinated by the chairman of the former management committee;
4. After the selection committee members are elected by majority vote, the division of work and responsibilities in the committee will be discussed and approved by the general assembly;
5. The selection committee shall make a legal handover of work among the newly elected members of the management committee within five working days;
6. The existing management committee members who were leading the cooperative society hand over their powers to the selection committee to carry out the election ceremony;
7. If the commission or office has doubts about the selection process, it may re-select the selection committee;
8. The term of office of the members of the management committee is three years. It may be re-elected for one additional term;
9. Notwithstanding the provisions of sub article (8) of this article, they may be elected after one term of office;

፲ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ብዛት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ውስጥ የሚወሰን ሆኖ ቁጥሩ የሚቋቋሙ የንዑሳን ኮሚቴ ዓይነትና ብዛት ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፤

፲፩ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀ-መንበር ውጭ ሌሎቹ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የንዑሳን ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ፤

፲፪ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከ፭ የሚያንስ ወይም ከ፱ የሚበልጥ መሆን የለበትም፤

፲፫ ጠቅላላ ጉባዔ ምርጫ ሲያካሄድ ሁለት ተጠባባቂ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የኮሚቴ አባላት በሚጓደልበት ወቅት የሚተኩ ይሆናል፤

፲፬ ጠቅላላ ጉባኤው በየዓመቱ በሚያካሂደው የጉባዔ ስብሰባ የሥራ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተጓደሉ የኮሚቴ አባላትን ይተካል፤

፲፭ የቀድሞ የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት ከተመረጡበት ከሁለተኛ የሥራ ዘመን ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ ዓመት ጀምሮ ቢያንስ አንድ ሦስተኛ የአመራር ኮሚቴ አባላት በአዲስ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ይተካሉ፤

፲፮ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፰) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የኅብረት ሥራ አመራር አካላት የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሚጻረር ማንኛውንም ድርጊት ፈጽሞ ከተገኘ በማንኛውም ጊዜ የሥራ ዘመኑ ሣይደርስ በጠቅላላ ጉባዔ ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፤

10. The number of members of the management committee shall be determined in the bylaws of the cooperative society, and the number shall take into account the type and number of sub-committees to be established;
11. Other than the chairman of the cooperative society, the other members of the management committee can work as sub-committee conveners;
12. The number of members of the management committee should not be less than 5 or more than 9;
13. When the general assembly conducts elections, two acting members of the management committee will be elected and will replace them when the committee members are absent due to force majeure;
14. The general assembly shall replace the members of the committee who have completed their term of office or left at the annual general meeting;
15. At least one-third of the members of the management committee shall be replaced by new members of the management committee, starting from the first year of the second term of office of the former members of the management committee;
16. Notwithstanding the provisions of sub article (8) of the this article, any member of the management of the cooperative society may be removed from his position at the general assembly at any time before his term of office is reached, if any action against the cooperative society is found;

፲፯ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የባንክ አካውንቱ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ በተሻሩና በተመረጡ ኮሚቴዎች መካከል የስልጣን ርክክብ ከአምስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

፲፰ ነባሩና አዲስ የተመረጠው የሥራ አመራር ኮሚቴ የኮሚሽኑ ወይም የጽህፈት ቤቱ ቅጥር ሠራተኞች እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በታዛቢነት በተገኙበት የሥራ ርክክብ መፈጸሙን ሊያረጋግጥ ይችላል፤

፲፱ ነባር የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት ለተተኪ የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት ሥራዎች ያሉበትን ዝርዝር መረጃ የመስጠት እና ለአንድ ወር ሥራውን የማለማመድ ግዴታ አለባቸው፡፡

፶፬ **ለኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርነት ለመመረጥ የሚያበቁ መስፈርቶች**

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ለምርጫ የሚከተሉት መስፈርቶች ከግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል፡-

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆነና ቢያስን ለስድስት ወራት በአባልነት የቆየ፤

፪ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ውሰጥ የተጠቀሱትን የአባልነት ግዴታዎች በብቃት የተወጣ፤

፫ የሚሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት የሚችል፤

፬ ሰዎችን ለመርዳት ፅኑ ፍላጎትና ተቆርቋሪነት ያለው፤

፭ ቀደም ሲል በምግባረ ብልሹነት ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ያልተፈረደበት፤

፮ ታማኝነቱ በአባላት የተመሰከረለት፤

17. The commission or the office will ensure that the transfer of power between the abolished and elected committees takes place within a period of not more than five working days by keeping the bank account from moving;
18. The existing and newly elected management committee can confirm that the handover of work has been done in the presence of the staff of the commission or the office and the members of the selection committee as observers;
19. Existing management committee members are obliged to provide detailed information about the work of the replacement management committee members and practice the work for one month.

54. **Requirements for being Elected to the Management of Cooperative Societies**

Subject to the provisions of the proclamation, the following criteria should be taken into consideration for the selection of the members of the management committee:

1. who is a member of the cooperative society and has been a member for at least six months;
2. Effectively fulfilled the membership obligations mentioned in the cooperative society's bylaws;
3. Able to carry out the responsibilities given properly;
4. Has a strong desire and concern to help people;
5. Has not been previously convicted of immorality or perjury;
6. His faithfulness is witnessed by the members;

፯ የሚሰጠውን ትምህርትና ስልጠና ለመውሰድ ፈቃደኛ የሆነ እና አዳዲስ ቴክኖሎጅን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፤

፰ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ውሳኔ በመስጠት ሂደት ያለበትን ተጠያቂነት በአግባቡ የተረዳ፤

፱ የሚሰጠውን ተግባር ተቀብሎ ለመፈጸም ዝግጁ የሆነ፤

፲ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩንና ፌዴሬሽን የሥራ አመራር የኮሚቴ አባል ለመሆን አባል ከሆነበት መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ውክልና ያለው መሆን አለበት፤

፲፩ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ የተያዩ ቡድንተኝነት በመፍጠር የኅብረት ሥራ ማህበሩን አሰራር የማያውክ፤

፲፪ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅጥር ሰራተኛ ያልሆነ፤

፲፫ ቼክ ፈራሚዎች የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት እና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የትምህርት ደረጃ ዲግሪና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

፶፭ **<u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ድምፅ አሰጣጥ</u>**

፩ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም አባል ያለው የዕጣ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ አንድ አባል አንድ ድምፅ ይኖረዋል፤

፪ አባላት ኅብረት ሥራ ማኅበራቸውን በሚመለከት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን የመግለፅ፣ የመከራከር፣ የመደገፍና የመቃወም መብት ይኖራቸዋል፤

፫ የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ቁጥር ከ ፭፻ በላይ ከሆነ ድምጽ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበር የሚወከለው ሰው ብዛት ከ፪፻፶ ያነስ እና ከ ፭፻ የበለጠ መሆን የለበትም፤



7. Willing to take the education and training offered and ready to embrace new technologies;
8. A member of the management committee who properly understands the responsibility of the decision-making process;
9. Ready to accept and perform the task given;
10. To be a member of the management committee for cooperative society unions and federations, he must be a representative of the primary cooperative society or cooperative society union of which he is a member;
11. Does not disrupt the operation of the cooperative society by creating factionalism within the cooperative society;
12. who is not an employee of the cooperative society;
13. Check signatories, management committee members and control committee members must have a bachelor's degree or higher.

55. **<u>Voting of Cooperative Societies</u>**

1. A member shall have one vote, regardless of the amount of share held by any member, as determined by the bylaws of the cooperative society;
2. Members shall have the right to express, argue, support and oppose their opinions in a democratic manner regarding their cooperative society;
3. If the number of members of the primary cooperative is more than 500, voting can be done by representation;
4. Subject to the provisions of sub article (3) of this article, the number of persons represented by the primary cooperative society shall not be less than 250 and not more than 500;

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር የሚወከለው ሰው ብዛት ከ፻፶ ያነስ እና ከ ፭፻ የበለጠ መሆን የለበትም፤

፮ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አባል ስንት አባላትን እንደሚወክል እና የውክልና ጊዜውን በተመለከተ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

፯ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) የተደነገገው ቢኖርም የማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የጋራ ህንጻ ባለቤቶች ማህበር አባል በህጋዊ መንገድ በውክልና የመደራጀት እና የመምረጥ መብት ቢኖራቸውም የመመረጥ መብት ግን የላቸውም፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ ሥራ አስኪያጅ እና ተቀጣሪ ባለሙያዎች

### ፶፮ ጠቅላላ ጉባዔ

ጠቅላላ ጉባዔ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚሰበሰብ ሆኖ እያንዳንዱ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባል የሚገኝበት የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የበላይ አመራር አካል ነው፡፡

### ፶፯ የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን እና ተግባር

ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተለው ሥልጣን እና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን አጠቃላይ ይሥራ እንቅስቃሴ እየገመገመ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፤

፪ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ፣ ውስጠ ደንብ ፣ ፖሊሲዎች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች ያወጣል፤ ያሻሽላል፤

5. Subject to the provision of sub article (3) of this article, the number of persons represented for a savings and loan cooperative society shall not be less than 150 and not more than 500;
6. Subject to the provisions of sub articles (4) and (5) of the this article, how many members a member represents and the period of representation will be determined by the cooperative society's bylaws;
7. Notwithstanding the provisions of sub articles (1) to (6) of this article, members of any housing cooperative societies or condominium owners' association have the right to legally organize and vote through representation, but they do not have the right to be elected.

## PART SEVEN

## GENERAL ASSEMBLY OF COOPERATIVE SOCIETY, MANAGEMENT COMMITTEE, MANAGER AND EMPLOYED PROFESSIONALS

### 56. General Assembly

The general assembly meets at least twice a year and is the governing body of the cooperative, where every member of the cooperative society is present.

### 57. Power and Duties of General Assembly

The general assembly shall have the following powers and duties:

1. Evaluates the overall activities of the cooperative society and makes decisions;
2. Formulates the cooperative society's bylaws, internal rules, policies and operational directives and amend.

፫. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ እና የንዑሳን ኮሚቴዎች አባላትንም ይመርጣል፤ ይሽራል፤

፬. በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አመራር ኮሚቴ ውስጥ እንደ አግባቡ ቢያንስ አንድ የአካል ጉዳተኛ እንዲካተት ማድረግ፤

፭. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የመነሻ ዕጣ መጠን ፣ ዋጋን እና የአከፋፈል ሁኔታ ይወሰናል፤

፮. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ከሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር ጋር እንዲዋሃድ ፣ እንዲከፈል ወይም እንዲፈርስ ይወስናል፤

፯. በሥራ አመራር ኮሚቴው እና በቁጥጥር ኮሚቴው የሚቀርቡ ሪፖርቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፰. የአባልነት መቀበልንና ከአባልነት መሰናበትን የተመለከተ የሥራ አመራር ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ ሲቀርብለት ምርምሮ ያጸድቃል፤

፱. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የተጣራ ትርፍ አመዳደብ ይወስናል፤

፲. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የኢንስፔክሽን፣ ኦዲት ፣ የብቃት ምዘናና ደረጃ ማረጋገጥ፣ ውጤት እና ዕቅድን መርምሮ ያጸድቃል፤

፲፩. በሥራ አመራር ኮሚቴና በሌሎች ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ጉዳዮች በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይወስናል፤

፲፪. የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የጋራ ህንጻ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ ከሆነ የሚቀርብለትን የዲዛይን ማሻሻያ ያጸድቃል፡፡

3. It also elects the members of the management committee, control committee and sub-committees of the cooperative society; it will be canceled;
4. To include at least one disabled person in the management committee of any cooperative society as appropriate;
5. Determines the size, value and distribution of the cooperative society's initial share;
6. The cooperative society decides to amalgamate with another cooperative, society division or amalgamation;
7. Examines and makes decisions on reports submitted by the management committee and the control committee;
8. When a decision proposal is submitted to the management committee regarding acceptance of membership and resignation from membership, it investigates and approves;
9. Determines the distribution of net profits of the cooperative society;
10. Examines and approves the cooperative society's inspection, audit, competency assessment and level verification, results and plans;
11. It decides the issues presented to him by the management committee and other committees according to the authority given in the bylaws;
12. If it is a general assembly of a housing cooperative society or a condominium association, it approves the proposed design amendment.

**፶፰ የሥራ አመራር ኮሚቴ አወቃቀር**

፩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ ቁጥራቸው ከ ፭ - ፱ የሚሆኑ አባላት ይኖሩታል፤

፪ የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር ፣ ፀሐፊ ፣ ገንዘብ ያዥ፣ ሂሳብ ሹምና ሌሎች አባላት ይኖሩታል፤

፫ ከኅብረት ሥራ አመራሩ ውስጥ አባል በተለያየ ምክንያት ኃላፊነቱት ሲለቅ አመራር ለማሟላት ከተጠባባቂዎች በመጥራት ማሟላት ይቻላል፤

፬ የኮሚቴ አባሉን ለማሟላት የሚጠራው ተጠባባቂው በሥራ አመራር ኮሚቴ ውስጥ ካሉት ኃላፊነቶች ውስጥ የሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር ፣ የፀሐፊ ሂሳብ ሹም እና የገንዘብ ያዥ ኃላፊነቶች ላይ የተተኩ ከሆነ ስለተተኩበት ሁኔታ በቀጣይ በሚኖር ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ቀርቦ ውሳኔ ሊያርፍበት ይገባል፤

፭ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር አመራር ሲመርጡ በአመራር ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ፴% እና የወጣቶች ተሳትፎ ፴% እንዲሆን ሊደረግ ይችላል፡፡

**፶፱ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**

የሥራ አመራር ኮሚቴ ዝርዝር ሥልጣን በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት ያካትታል፡-

፩ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችን ያስፈፅማል፤

፪ በማንኛውም ጊዜ ኅብረት ሥራ ማኅበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ኅብረት ሥራ ማኅበሩን ወክሎ ይቆማል፣ ውሎችን ይዋዋላል፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ፣ በጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬ የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎች በፅሑፍ ይይዛል፤መዛግብትንም ያደራጃል፤



**58. The Structure of Management Committee**

1. The management committee is responsible to the general assembly and will have 5-9 members;
2. The management committee will have a chairman, vice chairman, secretary, treasurer, accountant and other members;
3. When a member of the cooperative society's management resigns due to various reasons, it can be filled by calling the standby members to fill the management position;
4. If the alternate who is called to fulfill the committee member has been replaced in the responsibilities of the chairman, vice chairman, secretary, accountant and treasurer among the responsibilities in the management committee, a report on the status of their replacement should be submitted to the next general assembly and a decision should be made.
5. When electing the management of any cooperative society, the participation of women in the management can be made 30% and the participation of youth 30%.

**59. Powers and Duties of Management Committee**

The detailed powers of the management committee are determined by the bylaws of the cooperative society and include the following:

1. It implements the decisions of the general assembly;
2. At any time, the cooperative society stands on behalf of the cooperative society in matters concerning the cooperative society, negotiates contracts;
3. Prepares the cooperative society's plan and budget, and implements it when approved by the general assembly;
4. Keeps meeting minutes in writing and organizes records;

፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ አያያዝ ሥራ በተገቢው መንገድ እንዲፈፀምና ሰነዶችና መዛግብቶች በአግባቡ ተይዘው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፮ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤን ይጠራል፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፤ይገመግማል፤ዓመታዊ የሥራ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

፰ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች የአሰራር መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤

፱ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመመዝገቢያ ክፍያ ይሰበስባል፤ እንዲሁም እንዲሸጥ የተወሰነውን ዕጣ እና በተጨማሪ የታወጀን ዕጣ ይሸጣል፤

፲ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ መሰረት ያበድራል፤ይበደራል፤

፲፩ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የተሰጣቸውን የተሻሻሉ መተዳደሪያ ደንብ፤ውስጠ ደንብ እና ሌሎች እንዲመዘገቡ የሚጠየቁ ሰነዶችን አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ያስመዘግባል፤

፲፪ በጠቅላላ ጉባኤ በፀደቀው የኦዲት ሪፖርት መሰረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የትርፍ ክፍፍል ያደርጋል፤

፲፫ በኅብረት ሥራ ማህበሩ እና በአባላት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ወደ ሽምግልና ዳኝነት ከመሄዱ በፊት የሚያግባባ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፤

፲፬ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በፍቃዱ ከአባልነት ለመሰናበት ጥያቄ የሚያቀርብ አባል ጥያቄን ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፤ ግዴታውን ባለመወጣትና በጥፋት ለሚሰናበት አባል ውሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

፲፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፤ያሰናብታል፤

5. It ensures that the accounting work of the cooperative society is carried out in an appropriate manner and that documents and records are properly kept and used;
6. In accordance with the bylaws of the cooperative society, it calls the general assembly;
7. It directs and evaluates the work activities of the cooperative society and submits an annual work report to the general assembly;
8. Prepares the bylaws and other operating guidelines of the cooperative society;
9. Collects the cooperative society's registration fee, he shall also sell the lots designated for sale and the lots declared in addition;
10. According to the bylaws and internal rules of the cooperative society, it lends and borrows;
11. Registers the revised by-laws, internal rules and other documents that are required to be registered to the relevant authority;
12. According to the audit report approved by the general assembly, it will distribute dividends in the fiscal year;
13. When there is a dispute between the cooperative society and its members, it proposes an amicable solution before going to arbitration;
14. A member who submits a request to resign from the cooperative society voluntarily accepts the request and makes a decision; it submits to the general assembly to give a decision to the member who is dismissed for not fulfilling his duty;
15. It hires and dismisses the manager of the cooperative society;

፲፮ ከሥራ አመራር ኮሚቴው አቅም በላይ የሆኑ ውሳኔዎችን የሚጠይቁ ጉዳዮችን ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

፲፯ ሌሎች ተጨማሪ በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፷ **የቁጥጥር ኮሚቴ**

፩ የቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ የአባላቱ ቁጥር ሶስት ይሆናል፣

፪ አባላቱ ሰብሳቢ ፣ ፀሐፊና አንድ አባል ሆነው ያገለግላሉ፣

፫ የኮሚቴው የሥራ ዘመን ፫ ዓመት ይሆናል፣

፬ የኮሚቴ አባላት ከታመነባቸው ለሁለተኛ የምርጫ ዘመን በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፣ ሆኖም ግን ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፣

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ የኮሚቴ የስራ ዘመን በኋላ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፣

፮ ከሁለተኛው ምርጫ ዘመን ጀምሮ በየዓመቱ ቢያንስ አንድ ሶስተኛውን የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በአዲስ ይተካሉ፣

፯ ከቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ውስጥ አንድ አባል በተለያየ ምክንያት ሥራ ቢያቋርጥ ለተጠባባቂ ከተመረጡ የቁጥጥር ኮሚቴ አባል ውስጥ ይተካል፣

፰ የኮሚቴ አባላቱ በግል ወይም በቡድን ጥፋት ከተገኘባቸውና ከተረጋገጠ የሥራ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ እንደአግባብነቱ በማንኛውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡

16. Submits issues that require decisions beyond the capacity of the management committee to the general assembly;
17. Performs other duties assigned by the general assembly.

60. **Control Committee**

1. The Control Committee will be accountable to the general assembly and its members will be three;
2. The members shall serve as chairperson, secretary and one member;
3. The term of office of the committee shall be 3 years;
4. Committee members may be re-elected for a second term if they are trusted; however, they may not be elected for more than two consecutive terms;
5. Notwithstanding the provisions of sub article (4) of this article, the members of the control committee may be re-elected after one term of office of the committee;
6. Starting from the second election period, at least one-third of the members of the control committee shall be replaced by new ones every year;
7. If one of the members of the control committee resigns for various reasons, he will be replaced by one of the members of the control committee selected as a standby;
8. If the members of the committee are found and proven guilty of individual or collective misconduct, they may be dismissed by the general assembly at any time without completing their term of office.

፷፩ **የቁጥጥር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**

፩ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችን በትክክል በተግባር መተርጎማቸውን ይከታተላል፤ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

፪ የሥራ አመራር ኮሚቴ ኃላፊነቱን በትክክል መወጣቱን ይከታተላል፤

፫ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ በኦዲት ሪፖርት የተገኙ ጉድለቶች እና ግድፈቶች መታረማቸውን ያረጋግጣል፤

፬ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፤

፭ በአሠራር ላይ ችግሮች ሲከሰቱ ከሥራ አመራር ኮሚቴው ጋር በመሆን ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፣ ከአቅም በላይ ከሆነ የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ እንዲደረግና ውሳኔ እንዲሰጥበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል ወይም ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

፮ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አመታዊ ሪፖርት እና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

፯ በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናል፡፡

፷፪ **ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች**

የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ስፋትና ባህሪ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ንዑስ ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

፷፫ **የብድር ንዑስ ኮሚቴ**

፩ ኮሚቴው በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል፤

61. **Powers and Duties of the Control Committee**
    1. Monitors the correct implementation of the resolutions of the general assembly; It confirms that it is done;
    2. The management committee monitors the proper discharge of its responsibilities;
    3. Controls the proper use of funds and assets of the cooperative society; ensures that deficiencies and omissions found in the audit report are corrected;
    4. Monitors the various activities of the cooperative society in accordance with the bylaws and directives of the cooperative society;
    5. When there are problems in operation, he works together with the management committee to solve the problems, if it is beyond his capacity, he facilitates the conditions for the general assembly to be called and a decision is made, or it informs the concerned party;
    6. Prepares the cooperative society's annual report and work plan and submits it to the general assembly;
    7. Performs other similar duties assigned by the general assembly.

62. **Other Sub-Committees**

    Cooperative societies may have sub-committees elected by the general assembly according to the scope and nature of the cooperative society's work, the listing performance is determined by the cooperative society's bylaws.

63. **Loan Sub-Committee**
    1. The committee will be elected by the general assembly and will be accountable to the management committee.

፪ ኮሚቴው ሰብሳቢ ፣ ፀሐፊና አንድ አባል ይኖረዋል፤

፫ የኮሚቴው የሥራ ዘመን ፫ ዓመት ይሆናል፡፡

፬ የኮሚቴ አባላት ከታመነባቸው በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤

፭ በግል ወይም በቡድን ጥፋት ከተገኘባቸውና ከተረጋገጠ የሥራ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ በጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡

**፷፬ <u>የብድር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩ የብድር ጥያቄ ማመልከቻ ይቀበላል በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና የብድር መመሪያ መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ብድሩ እንዲፈቀድ ለሥራ አመመራር ከአስተያየት ጋር ለውሳኔ ያቀርባል፤

፪ የተፈቀደውን ብድር አጠቃቀምና አመላለስ ይከታተላል፤

፫ የማኅበሩን ደንብና የብድር መመሪያ መሠረት በማድረግ የራሱን የአፈፃፀም መመሪያ ያዘጋጃል፤

፬ በብድር የወጣ ገንዘብ በአግባቡ የሚመለሰበትን ሁኔታ በማጥናት ከሥራ አመራር ኮሚቴው ጋር ተግባራዊ የሚሆንበትን መፍትሄ ያፈላልጋል፤

፭ የማህበሩን የብድር እንቅስቃሴ በየሩብ አመቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፤

፮ የብድር መክፈያ ጊዜን ማራዘምን ተጨማሪ ብድር የተጠየቀባቸው ብድሮች መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፤

2. The committee will have a chairman, secretary and one member;
3. The term of office of the committee will be 3 years;
4. Committee members may be re-elected if they are trusted; however, they may not be elected for more than two consecutive terms;
5. If they are found guilty of personal or group misconduct, they may be revoked by the general assembly before completing their term of office.

**64. <u>Duties and Responsibilities of Loan Committee</u>**

1. Receives a loan application and makes sure that it is in accordance with the cooperative society's bylaws and loan directive, and submits a proposal to the management for approval of the loan;
2. Monitors the use and disbursement of approved loans;
3. It prepares its own implementation directive based on the society's regulations and loan directive;
4. It studies the situation of the proper return of borrowed money and finds a solution that can be implemented with the management committee;
5. It submits a quarterly report of the society's loan situation to the management committee;
6. It examines the extension of the loan repayment period for loans for which additional loans are requested and submits it to the management committee to make a decision;

፯ አዳዲስ የብድር አሰራር ሃሳብ ያፈልቃል ፤ለሥራ አመራር ኮሚቴ በማቅረብ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰ ከሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፷፭ የትምህርት ስልጠና ቅስቀሳ ኮሚቴ**

፩ ኮሚቴው በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ይሆናል፤

፪ ኮሚቴው ሰብሳቢ ፣ ፀሐፊና አንድ አባል ይኖረዋል፤

፫ የኮሚቴው የሥራ ዘመን ፫ ዓመት ይሆናል፡፡

፬ የኮሚቴ አባላት ከታመነባቸው በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤

፭ በግል ወይም በቡድን ጥፋት ከተገኘባቸውና ከተረጋገጠ የሥራ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ በጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡

**፷፮ የትምህርት ስልጠና ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

፩ ህብረተሰቡ በተሻለ የጥራት ደረጃ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለፍጆታ የሚሆን ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ያስተምራል፤

፪ አባላት ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራቸው እንዲያውቁና ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለበትን ችግር በመረዳት የጋራ መፍትሔ እንዲፈልጉ ጥረት ያደርጋል፤

፫ የሌሎችን አካባቢ ኅብረት ሥራ ማህበራት ልምድ ለመቅሰም እንዲቻል ትምህረታዊ ጉብኝት በአመራር አካላት፣ አባላትና በቅጥር ሠራተኞች እንዲደረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

7. It comes up with new ideas for credit systems and implements them when approved by the management committee;
8. Performs other duties assigned by the management committee.

65. **Educational Training Campaign Committee**

1. The committee will be elected by the general assembly and will be accountable to the management committee;
2. The committee will have a chairman, secretary and one member;
3. The term of office of the committee will be 3 years;
4. Committee members may be re-elected if they are trusted; however, they may not be elected for more than two consecutive terms;
5. If they are found guilty of personal or group misconduct, they may be revoked by the general assembly before completing their term of office.

66. **Duties and Responsibilities of Educational Training Committee**

1. Educates the society to benefit from products and services for consumption with better quality and reasonable prices;
2. It makes efforts for members to know about their cooperative society and to understand the problem of the cooperative society and find a common solution;
3. Facilitates conditions for educational visits to be conducted by management bodies, members and employees in order to learn from the experience of other local cooperative societies;

፬ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላትና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

፭ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ለሥራ አመራሩ ያቀርባል፤

፮ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፷፯ የግዥ እና ትመና ኮሚቴ

የግዥና ትመና ኮሚቴ፡-

፩ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ሆኖ ፫ ዓመት የሥራ ዘመን ይኖረዋል፤

፪ ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ እና አንድ አባል ይኖረዋል፤

፫ የኮሚቴ አባላት ከታመነባቸው በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤

፬ በግል ወይም በቡድን ጥፋት ከተገኘባቸውና ከተረጋገጠ የሥራ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ በጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሩ ይችላሉ፤

## ፷፰ የግዥና ትመና ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

፩ በአባላት ዘንድ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራታቸው ተጠብቆ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

፪ የተገዙ ምርቶች ጥራታቸው ተጠብቆና ተተምነው ለሽያጭ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፫ የምርት የግዥ ዋጋን፣ የማጓጓዣ ወጭን እና ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዕድገት የሚያስፈልገውን ትርፍ ግምት ውስጥ በማስገባት በሚሰጠው የውክልና ኃላፊነት መሠረት የመሸጫ ዋጋን ይወስናል ፣ ከኃላፊነቱ በላይ የሆነውን ለሥራ አመራር ኮሚቴው አቅርቦ ያስወስናል፤

4. Creates awareness of cooperative societies among members and the public using various methods;
5. Submits a current work report to the work management;
6. Performs other duties assigned by the management committee of the cooperative society.

## 67. Procurement and Appraisal Committee

Procurement and appraisal committee:

1. Members will be elected by the general assembly and will have a 3-year term of office.
2. It will be accountable to the work management committee chairperson, secretary and one member;
3. Committee members may be re-elected if they are trusted; however, they may not be elected for more than two consecutive terms;
4. If they are found guilty of personal or group misconduct, they may be revoked by the general assembly before completing their term of office.

## 68. Powers and Duties of Procurement and Appraisal Committee

1. It ensures that the quality of products and services that are in demand by members are maintained and provided at reasonable prices;
2. Ensures that the quality of purchased products is maintained and sealed for sale;
3. Determines the selling price according to the representative responsibility, taking into account the purchase price of the product, shipping cost and the profit needed for the development of the cooperative society, and decides what is beyond his responsibility to the management committee;

፬ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ተጠቃሚዎች ክፍት ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፤

፭ የምርት ወይም የአገልግሎት መሸጫ ዋጋ በምርት ወይም አገልግሎት ዓይነቱ እና በጥራት ደረጃው በመለየት በመለጠፍ ተጠቃሚዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

፮ በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ትክክለኛ መለኪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ባቀደው እቅድ መሰረት ምርቱን ይገዛል፤ እንዲገዛ ያደርጋል፤ ይተምናል፤ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

፰ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡትን ልዩ ልዩ ምርቶችን በግዥ መመሪያ መሰረት ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፤ ይከታተላል፤

፱ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ለሥራ አመራሩ ያቀርባል፤

፲ ከሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፷፱ **ከአመራርነት ስለ ማገድ፣ ስለ መሰናበት እና ስለ መተካት**

፩ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የኮሚቴ ተመራጭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ደንብ የሚፃረር ተግባር ውስጥ ገብቶ ሲገኝ ከኮሚቴ አባልነት ይታገዳል፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበር የኮሚቴ አባላት በጋራ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና አዋጁን የሚቃረን ተግባር ውስጥ ገብተው ከተገኙ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ አባላቱን አግዶ ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፤

4. Prepares a time table for the users of various service facilities to be open and provide services;
5. The selling price of a product or service will be posted separately according to the type and quality of the product or service, and will let users know about it;
6. Ensures that proper parameters are met by service providers; controls;
7. The cooperative society buys the produce according to the plan, it makes him buy. It trusts. It makes it sell;
8. Procures the various products offered by cooperative societies in accordance with procurement directive; it will do it. Follows up.
9. Submits a current work report to the work management;
10. Performs other similar duties as assigned by the management committee.

69. **Suspension, Replacement and Dismissal from Management**

1. Any member of the cooperative society elected by the committee will be suspended from committee membership if found to be in violation of the rules of the cooperative society;
2. If the committee members of the cooperative society are found to have engaged in activities that are against the cooperative society's bylaws and the proclamation, the commission or the office will suspend the members and call a general assembly to take action against them;

፫. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር፣ የቁጥጥርና ንዑሳን ኮሚቴ ተመራጭ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ምክንያት ከኮሚቴ አባልነት ለመሰናበት ከፈለገ ተጠሪ ለሆነበት ኮሚቴ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፤

፬. ጥያቄ ላቀረበው የሥራ አመራር ፣ የቁጥጥር ወይም የንዑስ ኮሚቴ አባል ጥያቄ ባቀረበ በ15 ቀናት ውስጥ በፅሁፍ መልስ መሰጠት ይኖርበታል፤

፭. የተጓደለ የኮሚቴ አባል ሲኖር የተጓደለበትን ምክንያትና በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በተጠባባቂነት የቆዩትን የኮሚቴ አባላት በመተካት ኮሚሽኑ እንዲያውቅ ይደረጋል፤

፮. አንድ የኮሚቴ አባል ካለበቂ ምክንያት ለ3 ጊዜ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራዎችና ስብሰባዎች እንዲገኝ ጥሪ ተደርጎለት ካልተገኘና አለመገኘቱ በቃለጉባኤ ከተያዘ በኋላ ከኮሚቴ አባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደተሰናበተ ተቆጥሮ በቦታው በተጠባባቂነት ቀድሞ በጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ የሚተካ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## ፸ የኅብረት ሥራ ማህበራት የቅጥር ሠራተኞች

በአዋጁ አንቀጽ ፴፱ መሠረት፡-

፩. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ ስፋትና ዕድገት መሰረት በማድረግ ልዩ ልዩ ሙያን በሚጠይቁ የሥራ መስኮች ላይ ሠራተኞችን ቀጥሮ ማሰራት ይችላሉ፤

፪. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከሰራተኛው ጋር የሚኖረው የቅጥር ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሰረት ይሆናል፤

3. If any member of the management, control and sub-committee of a cooperative society wants to resign from the committee due to force majeure, he must submit an application to the committee he is responsible for;
4. A written answer must be given to the management, control or sub-committee member who made the request within 15 days of making the request;
5. When there is an absent committee member, the commission will be notified of the reason for absenteeism and the replacement of the committee members who have been standing by the decision of the general assembly;
6. If a committee member fails to attend the activities and meetings of the cooperative society for 3 times due to insufficient reasons, and after the non-attendance is recorded in the minutes, he/she will be considered to have resigned from the committee membership on his/her own accord and will be replaced by someone previously elected by the general meeting.

## 70. Employees of Cooperative Societies

According to article 39 of the proclamation:

1. Cooperative societies can employ workers in fields that require different skills based on the scope and growth of their work;
2. The cooperative society's employment relationship with the employee shall be in accordance with the Labor and Employment Law;

፫ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት የዕለት ከዕለት ሥራውን የሚከታተል እና ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ የሆነ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀጥር ይችላል፤

፬ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መሰረታዊ የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበር የገቢ ማስገኛ ተቋማትን የሚመራ እንደአስፈላጊነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆነ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ወይም አስተባባሪ ወይም ተወካይ ቀጥሮ ሊያሰራ ይችላል፤

፭ ማህበሩ ሌሎች የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ባለሙያዎችን መቅጠር ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በኮሚሽኑ ለኅብረት ሥራ ማህበር ባወጣው የሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያው እና በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደረያ ደንብ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፸፩ ስለኮሚቴ አባላት ክፍያ

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው እና ለአባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ምንም ዓይነት ክፍያ አይከፈሉም፤

፪ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የኮሚቴ አባላት ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ተንቀሳቅሰው ሥራን በሚሰሩበት ጊዜ ላወጡት ወጪ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሰረት የሚሸፈን ይሆናል፤

፫ የልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳይ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ መቀመጫ ከአምስት ኪሎ ሜትር በላይ ሲሄዱ በውስጠ ደንባቸው በሚወስኑት መሠረት የውሎ አበል ይከፈላቸዋል፤ የትራንስፖርት ወጪም በሚያቀርቡት ህጋዊ ደረሰኝ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

3. Any cooperative society may employ a general manager who oversees its day-to-day operations and is accountable to the management committee;
4. Subject to the provisions of sub article (3) of this article, a primary consumer cooperative society may employ a branch manager or coordinator or representative who is accountable to the general manager as necessary to manage income generating institutions;
5. The cooperative society may hire other department heads and professionals, the detailed performance will be implemented according to the human resource management directive issued by the commission for the cooperative society and the cooperative society's bylaws;

## 71. Payment of Committee Members

1. Members of the special committee of cooperative societies shall not be remunerated for their services to the cooperative society and its members;
2. Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this article, the expenses incurred by the members of the committee while working for the cooperative society will be covered as determined by the bylaws of the cooperative society;
3. When the members of the various committees go more than five kilometers from the seat of the cooperative society for the affairs of the cooperative society, they will be paid a travel allowance according to their internal rules, the cost of transportation will be covered according to the legal invoice they provide.

## ክፍል ስምንት

## ካፒታል ፣ የፋይናንስ ምንጭ፣ ገንዘብና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም

### ፸፪ ስለ መመዝገቢያ ክፍያ

፩ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲመሰረት የአዋጭነት ጥናቱን መሰረት በማድረግ በመተዳደሪያ ደንቡ የመመዝገቢያ ክፍያ መጠን ይወስናል፤

፪ ማንኛውም አባል ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲገባ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የተወሰነውን የመመዝገቢያ ክፍያን በአንድ ጊዜ መክፈል አለበት፤

፫ የመመዝገቢያ ክፍያ መሰብሰብ የሚጀመረው የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምስረታ ጉባኤ ከተካሄደ በኋላ ነው፤

፬ ከመመዝገቢያ ክፍያ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ምስረታ፣ ምዝገባ ሂደት እንዲሁም ለልዩ ልዩ ወጪዎች መሸፈኛ ይውላል፤

፭ ለመመዝገቢያ የተከፈለ ገንዘብ አይመለስም፤ ጥቅም ሊጠይቅበትም አይችልም፤

፮ መተዳደሪያ ደንብ በማሻሻል የክፍያ መጠኑ እስካልተለወጠ ድረስ አዲስ ገቢ አባላት በነበረው የመመዝገቢያ ክፍያ መሰረት ክፍያ ፈጽመው ይመዘገባሉ፡፡

፯ የመመዝገቢያ ክፍያው ተጨማሪ ጥቅም አያስገኝም፤ በማንኛውም ሁኔታ ወጪ ተደርጎም ለአባላት አይከፈልም፡፡

### ፸፫ ስለ ዕጣ

በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

## PART EGHIT

## CAPITAL, SOURCE OF FINANCE, MANAGEMENT AND USE OF FUND AND ASSET

### 72. Registration Fee

1. When any cooperative society is established, it determines the amount of registration fee based on the feasibility study;
2. When any member joins the cooperative society, he/she has to pay the fixed registration fee according to the by-laws;
3. The collection of registration fee starts after the founding meeting of the cooperative society.
4. The money collected from the registration fee will be used to cover the formation, registration process and miscellaneous expenses of the cooperative society;
5. Registration fees are non-refundable. It cannot claim benefit from it;
6. New members will be registered according to the existing registration fee unless the payment amount is changed by amending the bylaws;
7. The registration fee does not provide additional benefits; in no event shall expenses be paid to members.

### 73. Share

Subject to the provisions of article 27 of the proclamation:

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዋነኛ የካፒታል ምንጭ ለአባላት ከሚሸጡት ዕጣ የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው፤

፪ የአንድ ዕጣ ዋጋ አንድ አባል መግዛት የሚገባው ዝቅተኛ የዕጣ ብዛት ሲሆን በአንድ ጊዜ ለሽያጭ የሚዘጋጀው ጠቅላላ የዕጣ መጠን የሚወሰነው በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፤ደረጃ በደረጃ ደግሞ በተሳትፎው መሠረት ተጨማሪ ዕጣ በመግዛት ካፒታላቸውን ያሳድጋሉ፤

፫ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለሽያጭ የሚዘጋጀው ዕጣ የአባላት የመግዛት አቅምን ያገናዘበ መሆን አለበት፤

፬ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በወሰነው መሠረት አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው የሚገዙት ዕጣ በገንዘብ ወይም በዓይነት ሊፈፀም ይችላል፤

፭ በዓይነት ስለሚገዛው የዕጣ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ሊገልፁት ይችላሉ፤

፮ በምስረታ ጉባኤው እንዲሸጡ የታወጁ ዕጣዎችን የተከፈለ ዕጣ፤ ቃል የተገባ ዕጣ እና የሚሸጥ ዕጣ በሚል ይደለደላሉ፤

፯ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በዕቅዱ መሰረት ሥራውን ለማስጀመር የሚያስችል መነሻ ካፒታል ከመሥራች አባላት በተከፈለ ዕጣ በምስረታ ወቅት ከእያንዳንዱ አባል ዝቅተኛውን ወይም ቢያንስ አንድ አምስተኛው ከአባላት ይሰበሰባል፤

፰ ለመሸጥ ከታወጀው ቀሪውን ዕጣ ወዲያውኑ ለመግዛት የገንዘብ እጥረት ያለባቸው መሥራች አባላት በአራት ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ቃል የተገባ ዕጣ እንዲገዙ ስምምነት ማድረግ ይቻላል፤

1. Cooperative societies' main source of capital is money collected from the sale of shares to members;
2. The price of one share is the minimum number of shares that a member must buy, and the total amount of shares to be sold at one time is determined by the general assembly of the cooperative society;
3. Any share to be prepared for sale by any cooperative society should take into account the purchasing power of the members;
4. As determined in the management rules of any cooperative society, the share purchased by members from their cooperative society can be done in cash or in kind;
5. Cooperative societies may specify in their by-laws the nature of the share purchased in kind;
6. Divided shares of shares announced for sale at the general assembly; they are classified as promised shares and sold shares;
7. The cooperative society collects the minimum or at least one-fifth from each member at the time of establishment of the starting capital to start the business according to the plan by share paid by the founding members;
8. An agreement can be made for founding members who are short of funds to purchase the remaining share immediately if it is announced for sale, to purchase the promised share within a four-year time frame;

፱ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፯) መሰረት የተከፈለውን ዕጣ ገንዘብ ለዚሁ ተግባር ታስቦ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ በማድረግ የገቢ ደረሰኞቻቸውን ይዘው ለምዝገባ መቅረብ ይችላሉ፤

፲ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ቃል ገብተው በስምምነታቸው መሰረት የዕጣ ገንዘቡን ላልከፈሉ አባላት የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ ስድስት ወር በፊት በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ማሳወቅ ይኖርበታል፤ ገንዘቡን ሳይከፍሉ የጊዜ ገደቡ የተጠናቀቀ እንደሆን በስምምነታቸው መሰረት ተጠያቂ ይደረጋሉ፤

፲፩ ከምስረታ በኋላ ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሚገቡ አዲስ አባላት እና ነባር መሥራች አባላት ቃል ከገቡት ውጭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ካፒታል አቅም ለማጎልበት እንዲቻል ክፍት የተደረገ የሚሸጥ ዕጣ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

፲፪ በአዋጁ አንቀፅ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ (፯) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት እንዲሸጡ ተደልድለው በአባላት አቅም ማነስ ያልተሸጡ ዕጣዎች በጠቅላላ ጉባኤ እንደገና እንዲሸጡ ይወሰናል፤

፲፫ በአዋጁ አንቀፅ ፳፯ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቀድሞ የታወጀውን ዕጣ ሸጠው ከጨረሱ አዲስ ዕጣ በጠቅላላ ጉባዔ በማስወሰን እኩል ዋጋና መጠን ያላቸው ዕጣዎች መሸጥ ይችላሉ፤

፲፬ አዲስ ለአባላት የሚሸጥ ተጨማሪ ዕጣ ሙሉ በሙሉ አዋጁ ውስጥ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ተሸጦ ማጠናቀቅ አለበት፤

9. According to sub article (7) of this article, they can deposit the share money paid for this purpose in the bank account number opened in the name of the cooperative society and bring their receipts for registration;
10. The cooperative society must notify the members who have not paid the share according to their agreement six months before the deadline; if the time limit has expired without paying the money, they will be held liable according to their agreement;
11. For new members entering the cooperative society after formation and existing founding members, an open sale share should be prepared in order to enhance the capital capacity of the cooperative society;
12. Subject to the provisions of sub article (7) of article 27 of the proclamation, the shares allocated to be sold by the cooperative society to the members and not sold due to the incapacity of the members shall be decided to be resold by the general assembly;
13. Subject to the provisions of article 27 sub article (3) of the proclamation, if the cooperative societies finish selling the previously announced shares, they can sell shares of equal value and size by deciding a new share at the general assembly;
14. Additional shares sold to new members must be fully sold within the time limit set out in the proclamation;

፲፭ በአዋጁ አንቀፅ ፵፫ ንዑስ አንቀፅ (፫) በተደነገገው መሠረት አባላት ከተጣራ ትርፍ የሚያገኙትን ገንዘብ ለተጨማሪ ዕጣ ግዥ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሊገዙ ይችላሉ፤

፲፮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ተጨማሪ ዕጣ ለመሸጥ የሚታወጅባቸው የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ነው፡-

ሀ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሚያዘጋጃቸው ፕሮጀክቶች የካፒታል እጥረት ሲያጋጥመው፣

ለ) ከውጭ የፋይናንስ ወይም የገንዘብ ተቋማት ብድር ከማፈላለግ በፊት የውስጥ የገንዘብ አቅም ማሳደጉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣

ሐ) ቀደም ሲል በአባላት ተይዘው የነበሩ ዕጣዎች በአራት አመታት ውስጥ ተሸጠው በማለቃቸው ወይም በሌላ ልዩ ምክንያት ያልተሸጡ በጠቅላላ ጉባኤ እንደገና እንዲሸጡ ሲወሰን፤

፲፯ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከዓላማቸው ውጭ በኢንቨስትመንት ስም ከተለያዩ ባንኮች ውስጥ አክስዮን እየገዙ ባለቤት መሆን የለባቸውም፡፡

፸፬ <u>**የመጠባበቂያ ሂሳብ አቀማመጥ እና አጠቃቀም**</u>

፩ የመጠባበቂያ ገንዘብ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም የቁጠባ ሂሳብ ተከፍቶለት የሚቀመጥ ካፒታል በመሆን ለአበዳሪ ተቋማት እንደብድር ዋስትና ሆኖ ያገለግላል፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሥራ ላይ እንዲውል ለተወሰነ የመጠባበቂያ ገንዘብ መጠን የመድን ዋስትና እንዲገባለት በማድረግ ለሚከተሉት ተግባራት መጠቀም ይችላሉ፡-

15. According to the provisions of sub article (3) of article 43 of the proclamation, members can purchase the money they get from the net profit according to their request for the purchase of additional shares;
16. According to sub article 12 of this article, additional shares are announced for sale when there are the following reasons:
    a) When the cooperative society faces a lack of capital for the projects it prepares;
    b) When he finds it necessary to increase internal financial capacity before seeking loans from foreign financial or financial institutions;
    c) When it is decided by the general assembly to resell the shares previously held by the members because they were sold out within four years or were not sold for other special reasons;
17. Cooperative societies should not own and buy shares from various banks in the name of investment against their objective.

74. <u>**Keeping and Use of Reserve Account**</u>

1. Reserve money is used as a loan guarantee for lending institutions as a capital that is kept in a savings account in the name of the cooperative society.
2. Cooperative societies can be insured for a certain reserve amount to be used for the following activities:

ሀ) አባላት የአጭር ጊዜ ብድር ወይም ለአንድ ምርት ዘመን ለግብዓት ግዢ፣ ለምርት ማምረቻ እና ማሰባሰቢያ ወጪዎች፤

ለ) ለአባላት ለአነስተኛ የንግድ እና የኢንቨስትመንት፤

ሐ) ለሚቀርቡ የጥሬ ዕቃዎች፣ የሸቀጥ ግዢ እና ከአባላት የምርት መሰብሰቢያ ቅድሚያ ክፍያ፤

፫ የመጠባበቂያ ገንዘቡ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ህልውና በማይነካ መልኩ የጠቅላላ ጉባኤው በየዓመቱ በሚቀርብለት የኦዲት ሪፖርት መሠረት ይወስናል፤

፬ በመጠባበቂያ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ በጥናት ላይ ተመሥርቶ ሥራ ላይ እንዲውል ሊወስን ይችላል፤ ሆኖም ከ75 በመቶ በላይ ከመጠባበቂያ ሂሳብ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

፸፭ **<u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ ማቋቋም እና አስተዳደር</u>**

በአዋጁ አንቀፅ ፵፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወዳዳሪ በማድረግ አባላትን ያሳተፈ እና ተጠቃሚ የሚያደርግ የኅብረት ሥራ ፈንድ ይቋቋማል፤ የፈንዱ መቋቋምና አስተዳደር እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩ በአዋጁ አንቀጽ ፵፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ለአባላት ከሚከፋፈለው ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ውስጥ እስከ ሶስት በመቶ በየደረጃው ከተቋቋሙት ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚዘጋጀው የኦዲት ሪፖርት በግልጽ ተሰልቶ ሊቀመጥ ይገባል፤

፪ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የቀነሰውን ፈንድ ሃምሳ ከመቶ አባል ወደ ሆነበት ኅብረት ሥራ ዩኒዬን ይልካል፤

a) Members short-term loans or for one production period for the purchase of inputs, production and assembly costs;

b) For members for small business and investment;

c) Advance payment for supplies of raw materials, purchase of goods and collection of produce from members;

3. The reserve fund will be determined based on the annual audit report submitted to the general assembly without affecting the existence of the cooperative society;

4. It may decide to use the reserve account based on studies, however, more than 75 percent of the reserve account cannot be used.

75. **<u>Cooperative Societies Fund Establishment and Administration</u>**

Subject to the provisions of article 46 of the proclamation, a cooperative society fund will be established to involve and benefit members by making cooperative societies competitive, the establishment and administration of the fund will be as follows:

1. According to article 45 sub article (2) of the proclamation, up to three percent of the annual net profit distributed to the members should be clearly calculated in the audit report prepared by the cooperative societies established at each level;

2. According to sub article (1) of this article, the primary cooperative society will send fifty percent of the reduced fund to the cooperative society union of which it is a member;

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ከመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የተቀበለውንና ከራሱ የቀነሰውን ሃምሳ ከመቶ በማጠቃለል ለተቋቋመው አባል ለሆነበት ፌዴሬሽን ወይም ፈንድ ይልካል፤

፬ በየደረጃው ካሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቀነሰው የሶስት በመቶ ፈንድ በኦዲት ምርመራ ወቅት እራሱን የቻለ የሂሳብ ርዕስ እና መግለጫ ሊኖረው ይገባል፤

፭ በየደረጃው ባሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከኦዲት በኋላ ተቀንሶ የቀረው ሃምሳ በመቶ የኅብረት ሥራ ፈንድ በኅብረት ሥራ ማህበራት ፋይናንስ እና የሂሳብ አስተዳደር ህግ መሠረት የሚተዳደር ሆኖ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በሚወስነው መሰረት ሂሣቡም በተለየ ሁኔታ ለብቻው የሚያዝ ይሆናል፤

፮ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር እስከ ዩኒዬን ተሰባስቦ የመጣውን የኅብረት ሥራ ማህበራት ፈንድ የሚተዳደረው በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት ሆኖ ሂሣቡም በተለየ ሁኔታ ለብቻው የሚያዝ ይሆናል፤

፯ ህልውናቸውን ከሚያጡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከማይከፋፈል የጋራ ገንዘብና ንብረት የሚሰበሰብ ገቢ እና ከመንግስት እና ከልማት አጋር አካላት በስጦታ፣ ድጋፍ እና ከመሳሰሉት የሚገኝ ገቢ የፈንዱ አካል ይሆናል፤

፰ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው በሂደት ራሳቸውን ችለው በራሳቸው አቅም የኦዲት፣ የሕግ አገልግሎት፣ የአቅም ግንባታ፣ የጥናት እና ምርምር፣ የፕሮሞሽንና ኮሚኒኬሽን እና የመሳሰሉትን ወጪዎችን ለመሸፈን የሚረዳ የኅብረት ሥራ ፈንድ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

3. The Union of Cooperative societies sums up fifty percent of what it receives from the primary cooperative societies and deducts from itself, and sends it to the federation or fund of which it is a member;
4. The three percent fund deducted from cooperative societies at all levels should have a self-contained title and statement of accounts at the time of auditing;
5. The remaining fifty percent of the cooperative society fund deducted after the audit by the cooperative societies at all levels will be managed according to the Cooperativesociety Finance and Accounting Administration Law and the account will be kept separately as determined by the bylaws;
6. At the city government level, the cooperative societies fund that has been assembled from the primary cooperative society to the union is administered according to the financial administration system of the cooperative societies federation, and the account will be kept separately;
7. Income collected from non-distributable common funds and assets of cooperative societies that cease to exist and income from government and development partners through gifts, support, etc. will be part of the fund;
8. Cooperative societies at each stage should implement a cooperative society fund to help cover the costs of audit, legal services, capacity building, research and development, promotion and communication, etc. independently within their own capacity.

፸፮. **የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ምንጭ**

የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደየሥራ ባህያቸው ከሚከተሉት ዋና ዋና የፋይናንስ ምንጮች ገቢ ሊሰበስቡ ይችላሉ፡-

፩ ከመመዝገቢያ ክፍያ፤

፪ ከዕጣ ሽያጭ፤

፫ ከብድር፤

፬ ከቁጠባ፤

፭ ከብድር ወለድ፤

፮ ስጦታና ዕርዳታ፤

፯ ሽልማት፤

፰ ምርትና አገልግሎት መሰረት አድረገው ከሚሰሩት ሥራ፡፡

፸፯. **ከፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ የፋይናንስ ምንጭ**

፩ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በጥናት ለቀረቡ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚሆን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የሚያደርጉት የብድር ስምምነት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወስኑት እና አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፤

፪ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ከሆነበት የኅብረት ሥራ ማህበር ውጭ ባሉ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶች ወይም የአክሲዮን ገበያዎች በአክሲዮን ግዥ መሳተፍ አይችልም፡፡

፸፰. **ከአባላት ውጭ ስለሚገኝ ፋይናንስ**

የኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት መሠረት ተዘዋዋሪ ብድሮችን ለማስተዳደርና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከአባላት ውጭ ለሚሰጡት አገልግሎት ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

76. **Source of Financing of Cooperative Societies**

Cooperative societies can raise income from the following main sources of finance depending on their mode of operation:

1. From the registration fee;
2. From the sale of shares;
3. From a loan;
4. From savings;
5. From loan interest;
6. Gifts and grants;
7. Reward;
8. From the work they do based on products and services.

77. **Source of Finance Available from Financial Institutions**

1. Any loan agreements with financial institutions for the implementation of projects presented by a cooperative society shall be carried out in accordance with the bylaws of the cooperative society and the relevant laws;
2. Any savings and loan cooperative society may not participate in the purchase of shares in various investments or stock markets outside the cooperative society of which it is a member.

78. **Financing from Outside Members**

Cooperative societies may charge a reasonable service fee for the services provided outside the members for managing revolving loans and other similar activities as determined by their bylaws.

## ፸፱ ስለፋይናንስ ግብይት ትስስር

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር ያደርጋሉ፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማህበራት አባላትንና የኅብረት ሥራ ማህበሩን ጥቅም መሰረት በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ ከሌላ ዓይነት ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የፋይናንስ ግብይት ትስስር ያደርጋሉ፤

፫ ማህበራት ላለባቸው የገንዘብ እጥረት ችግር ለመቅረፍ ከባንኮች፤ ከአነስተኛ ብድር ተቋማት፤ ከአባላት እንዲሁም ከሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ጋር ለአባላት ጥቅም ሲባል የፋይናንስ ግብይትና ትስስር ማድረግ ይችላሉ፤

፬ በየትኛውም ደረጃ ያሉ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የሌሎች ፋይናንስ ሰጪ ተቋማት ወኪል በመሆን ገንዘብ ክፍያና ማስተላለፍ ተግባር ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

## ፹ የኅብረት ሥራ ማህበር ገንዘብ ገቢ ስለሚደረግበት

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ማንኛውም ገቢ በሙሉ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በትክክል ተመዝግቦና ተፈርሞበት ለኅብረት ሥራ በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ያዥ ገቢ ይሆናል፣

፪ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዋና ገንዘብ ያዥ በየጊዜው ሊሰበሰብ የማይችል የዕለት ሽያጭና ሌሎች ገቢዎች በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የባንክ ሂሰብ ቁጥር ገቢ በማድረግ በካርኒዎች ላይ የሰፈረው ገንዘብ መጠን ተደምሮ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የጥሬ ገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ተመዝግቦና ተፈርሞ ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዋና ገንዘብ ያዥ ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 79. Connection of Financial Transactions

1. Cooperative societies make financial transactions with similar cooperative societies;
2. Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this article, cooperative societies shall, based on the interests of the members and the cooperative society, enter into financial transactions with other types of cooperative societies as necessary;
3. From banks to solve the problem of lack of funds for unions. From small credit institutions, they can make financial transactions and connections with members and other capacity building bodies for the benefit of members;
4. Savings and Loan cooperative societies at any level can act as agents of other financial institutions to make payments and transfers.

## 80. Deposition of Cooperative Societies Fund

1. Any income of the cooperative society shall be credited to the cooperative society by the general treasurer of the cooperative society, duly registered and signed by the cooperative society's receipt;
2. Daily sales and other incomes that cannot be collected regularly by the general treasurer of the cooperative society are deposited in the bank accounts of the cooperative society.

**፹፩ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ገንዘብ ወጪ ስለሚደረግበት</u>**

፩ ማንኛውም ወጪ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ወጪ ማዘዣ ወይም በቼክ ላይ የሰፈሩ መግለጫዎችና የፊርማ ቦታዎች በሚመለከታቸው ሰዎች በትክክል ተዘጋጅተውና ተፈርመው በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ገንዘብ ያዥ በኩል ብቻ ገንዘብ ወጪ ይደረጋል፣

፪ ለተወሰነ የሥራ ጉዳይ ወይም ግዥ በቼክ ገንዘብ ወጪ ያደረገ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ተወካይ የመጀመሪያውን ሂሳብ ሳያወራርድ ተጨማሪ ገንዘብ ወጪ ማድረግ አይችልም፡፡

**፹፪ <u>ንብረት ገቢ ስለማድረግ</u>**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኃላፊ ወይም ሥራውን እንዲመራ የተሰየመው ኃላፊ በግዥ መጠየቂያው እና በግዥ መመሪያው፣ መሠረት ንብረቱ መግዛቱን በማረጋገጥ ገቢ እንዲሆን ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፪ አስፈላጊ የሆኑ የግዥ ሰነዶች ከንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ጋር በማያያዝ ንብረቱ ገቢ ይደረጋል፤

፫ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ንብረት ወደ ንብረት ክፍል ሲገባ የንብረቱ አጠቃላይ የህይወት ታሪክ በትክክል ተመዝግቦ መግባት አለበት፤

፬ በተገቢው የንብረት መረከቢያ ደረሰኝ ላይ አስረካቢና ተረካቢ ፊርማቸውን እንዲያሰፍሩ ይደረጋል፡፡

81. **<u>Expending of Cooperative Societies Fund</u>**

1. The total amount of fund will be registered and signed by the cooperative society's cash income receipt and will be credited to the chief treasurer of the cooperative society;
2. Cooperative societies fund is spent any expenditure shall be paid only through the treasurer of the cooperative society, with statements and signature spaces on the cooperative society's expense order or check duly prepared and signed by the concerned persons.

82. **<u>Incoming of Property</u>**

1. The head of the cooperative society or the head appointed to manage the work shall give an order to make it revenue by confirming that the property has been purchased in accordance with the purchase requisition and the purchase instructions;
2. The property will be registered along with necessary purchase documents along with the property registration receipt;
3. When the property of any cooperative society is entered into the property department, the entire life history of the property must be properly recorded;
4. Consignor and consignee will be required to affix their signatures on the appropriate property delivery receipt.

**፹፫ ንብረት ወጪ ስለማድረግ**

፩ ማንኛውም አላቂና ቋሚ ንብረት የወጪ ትዕዛዝ ለመስጠት ኃላፊነት ባለው አካል በተዘጋጀው ቅፅ ተሞልቶና ተፈርሞ ከመተላለፉ በፊት ከንብረት ክፍል ወጪ አይደረግም፣

፪ በሚመለከተው ኃላፊ በትክክል ተዘጋጅቶና ተፈርሞ የሚወጣ ቋሚም ሆነ አላቂ ንብረት ለማን ወጪ እንደሚሆን በተዘጋጀው ቅፅ ላይ በንብረት ክፍል ይመዘገባል፣ ተረካቢም ስለመረከቡ ይፈርማል፣

፫ ንብረት ክፍሉም በየጊዜው ገቢ የሆኑትንና ወጪ የተደረጉትን ንብረቶች በመመዝገብና በየጊዜው ስቶክ ካርድ በመሙላት ወጪና ቀሪውን ያመዛዝናል፡፡

**ክፍል ዘጠኝ**

**የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጠባ እና የብድር አስተዳደር**

**፹፬ ስለቁጠባ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም**

አንድ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር፡-

፩ መደበኛ ቁጠባ መሰብሰብ አለበት፤

፪ የመደበኛ ቁጠባ አሰባሰብ እና አስተዳደር ሥርዓት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል፡-

ሀ) ከአባላት የሚሰበስው መደበኛ ቁጠባ መጠን እና ጊዜው በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

ለ) አዲስ አባል ሲቀበል በማመልከቻ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የመደበኛ ቁጠባ መጠን መሰብሰብ አለበት፤

ሐ) አባል በራሱ ፍላጎት መሰረት የራሱን የመደበኛ ቁጠባውን ከፍ ወይም ዝቅ እንዲያደርግ በየስድስት ወሩ ሊፈቅድለት ይችላል፤

83. **Outgoing of Property**

1. Any movable and immovable property shall not be expensed from the property department before it is transferred in the form prepared and signed by the person responsible for issuing the expense order;
2. Properly prepared and signed by the relevant officer, fixed or transitory property will be registered in the property department on the form prepared for whom it will be spent;
3. The property department regularly registers the income and expenses of the property and balances the expenses and the balance by regularly filling the stock card.

**PART NINE**

**ADMINISTRATION OF SAVING AND LOAN OF COOPERATIVE SOCIETIES**

84. **Savings Collection, Administration and Use**

A savings and loan of cooperative society:

1. Must accumulate regular savings;
2. The regular savings collection and management system is as follows:
   a) The amount and duration of regular savings collected from members shall be determined by the cooperative societies' bylaws;
   b) When a new member is admitted, a regular savings amount must be collected as per the application request;
   c) A member may allow himself to increase or decrease his regular savings every six months according to his wishes;

መ) አባላት በመደበኛ ቁጠባ ለመቁጠብ በወሰኑት የገንዘብ መጠን መሰረት ከመደበኛ ያልሆነ ቁጠባ ተቀናሽ በማድረግ ወደ መደበኛ ቁጠባ እንዲዘዋወር ሊያደርግ ይችላል፤

ሠ) የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሰበሰብ ገንዘብ ወቅቱን ጠብቆ አስፈላጊ የሆኑ የሂሳብ ሰነዶች በግል ደብተርና ቋት መመዝገብ አለበት፤

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) በተራ ፊደል (ለ) እና (ሐ) ላይ የተደነገገው የመደበኛ ቁጠባ መጠን በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የመደበኛ ቁጠባ መጠን በታች ሊሆን አይችልም፤

፬. የመደበኛ ቁጠባን አባሉ በገባው ቃል መሠረት ያለማቋረጥ መቆጠብ ይኖርበታል፤

፭. የመኖሪያ አካባቢን መሰረት አድርጎ የተቋቋመ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚሰበስበው ቁጠባ የአባሉን ገቢ መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፤

፮. የመስሪያ ቦታን መሰረት አድርጎ የሚቋቋም ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ቁጠባ የሚሰበስበው ቁጠባ ከአባሉ ደመወዝ በመቶኛ ወይም በገንዘብ መጠን ተቀንሶ በሚወሰን መጠን መሆን አለበት፡፡

## ፹፭. መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ አሰባሰብና አስተዳደር

፩. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ መሰብሰብ ይችላል፤

፪. መደበኛ ያልሆነ ቁጠባ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት አሰራሩን በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ተዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ አለበት፤



d) According to the amount of money members decide to save in regular savings, it can be transferred from informal savings to regular savings;

e) The money collected by the savings and loan cooperative society must be recorded in a personal book and database in a timely manner with necessary accounting documents;

3. The amount of regular savings stipulated in sub article (2) ordinary letters (b) and (c) of this article cannot be lower than the minimum amount of regular savings set in the bylaws of the savings and credit cooperative society;
4. Regular savings member should save continuously as per the promise;
5. Any savings and loan cooperative society established on the basis of residential area must collect savings based on the member's income;
6. Any savings and loan cooperative society established on the basis of workplace shall collect savings as a percentage of the member's salary or a fixed amount.

## 85. **Collection and Administration of Informal Savings**

1. Any savings and loan cooperative society may collect informal savings;
2. Before starting to provide informal savings services, the procedure must be prepared in the savings and loan cooperative society's bylaws and approved by the general meeting;

፫. አዳዲስ የተቀረፁ መደበኛ ያልሆኑ የቁጠባ አገልግሎቶች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡

**፹፮. ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር**

፩. የማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት የሚቻለው በኅብረት ሥራ ፌዴሬሽን አማካኝነት ብቻ ይሆናል፤

፪. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ፌዴሬሽን የአባላትን የፋይናንስ አገልግሎት ፍላጎትን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በመቅረጽ አገልግሎት መስጠት አለበት፤

፫. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ፌዴሬሽን ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የውስጥ የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቶና በጠቅላላ ጉባኤ አጸድቆ መጠቀም አለበት፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የተቀረፀው ማዕከላዊ የፋይናንስ አገልግሎት በሥራ ላይ የሚውለው በኮሚሽኑ ከተመዘገበ በኋላ ይሆናል፡፡

**፹፯. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ ምንጭ**

አባላት፡-

፩. በመደበኛነት የሚቆጥቡት ገንዘብ፤

፪. በፍላጎት የሚቆጥቡት የቁጠባ ገንዘብ፤

፫. ለልጆቻቸው የሚቆጥቡት የቁጠባ ገንዘብ፤

፬. ለቤት የሚቆጥቡት ገንዘብ፤

፭. ለመኪና የሚቆጥቡት ገንዘብ፤

፮. ለንግድና ለተለያዩ ወጪዎች የሚቆጥቡት ገንዘብ፤

፯. በጊዜ ገደብ የሚያስቀምጡት ገንዘብ፤

፰. ለትምህርት፣ ለህክምና፣ ለጡረታ፣ ለጋብቻ፣ ለክብረ በዓል፣ ለእርጅና ጊዜ እና ለሌሎች መሰል ጉዳዮች ከሚቆጥቡት የሚገኝ ገንዘብ ነው፡፡

3. Newly designed informal savings services must be submitted and registered with the commission or its office before they become operational.

**86. Central Financial Services Delivery and Administration**

1. Centralized financial services can only be provided through cooperative society federations;
2. Any federation of savings and loan Cooperative societies should provide services by designing new centralized financial services based on the financial service needs of its members;
3. Any federation of savings and credit cooperative society associations must prepare and use an internal financial service provision guideline to provide central financial services and use it approved by the general assembly;
4. The central financial service formulated pursuant to sub article (3) of this article shall come into force upon registration with the commission.

**87. Saving Source of Savings and Loan Cooperative Society**

Members:

1. Money you save on a regular basis;
2. Desired savings;
3. Savings for their children;
4. Money you save for your home;
5. Money you save for a car;
6. Savings for business and miscellaneous expenses;
7. Money you save for a time limit;
8. It is the money you save for education, medical care, retirement, marriage, anniversaries, old age and other such things.

፹፰ **የቁጠባ መጠን**

፩ የማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጠባ መጠን እንደቁጠባ አይነቱ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወስነው መነሻ መጠን መሠረት አባላት ከወር ገቢ.ያቸው ላይ እየቀነሱ በመደበኛነት የሚቆጠብ ነው፤

፪ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት የሚቆጥቡት መደበኛ የቁጠባ መጠን የወር ደመወዝተኞች ከሆኑ ከወር ገቢ.ያቸው በመቶኛ ወይም በገንዘብ የሚቀነስ ሲሆን የወር ደሞዝተኛ ያልሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ በመተዳደርያ ደንባቸው ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የእያንዳንዱን አባል ፍላጎት መሰረት በማድረግ የሚከናወን ይሆናል፡፡

፹፱ **የቁጠባ ሂሳብ አያያዝ**

ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር፡-

፩ የአባላትን የቁጠባ ሂሳብ አያያዝን የሚገልጽ የቁጠባ ሂሳብ መግለጫ ወይም የቁጠባ ደብተር በማዘጋጀት ለአባላት መስጠት አለበት፤

፪ የቁጠባ ሂሳብ እንቅስቃሴውን በየወሩ የባንክ ማስታረቅ ሥራ መሰራት አለበት፤

፫ የቁጠባ ሂሳብ አያያዙ ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፤

፬ ለአባላቱ ለሚሰጠው የቁጠባ አገልግሎት የቁጠባ ደብተርና ሌሎች መሰል የገንዘብ ልውውጥ ማድረጊ.ያ የሂሳብ ሰነዶችን በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት በማዘጋጀት ሥራ ላይ ማዋል አለበት፤

፭ የቁጠባ ገንዘብ በአግባቡ እንዲያዝ ሠራተኛ ቀጥሮ ማሰራት አለበት፤

፮ የቁጠባ እንቅስቃሴ በየወሩ በሂሳብ ሰራተኛ እየተዘጋጀ እና በሥራ አመራር እየተገመገመ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

88. **Savings Rate**

1. The amount of savings of any savings and loan cooperative society is based on the basic amount determined by the bylaws according to the type of savings, which is regularly saved by members deducting from their monthly income;
2. Savings and loan cooperative society members' normal amount of savings is a percentage of their monthly income or money if they are monthly wage earners, while non-monthly wage earners will be based on the needs of each member according to the bylaws.

89. **Savings Account Management**

Any savings and loan cooperative society shall:

1. It must prepare a savings account statement or a savings book and give it to the members;
2. A monthly bank reconciliation of the savings account activity should be done;
3. Savings accounts must be based on a modern accounting system;
4. For the savings service provided to the members, the savings book and other similar money transfer accounting documents should be prepared in accordance with the bylaws of the savings and loan cooperative society;
5. It must employ an employee to manage the savings properly;
6. Savings activity should be prepared and reviewed by management on a monthly basis and reported to the commission or office.

**፺ <u>የቁጠባ ዓይነት</u>**

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚወሰን መደበኛ ቁጠባ፣ የፍላጎት ቁጠባ፣ የጊዜ ገደብ ቁጠባ፣ ወለድ የማይታሰብበት ቁጠባ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ቁጠባዎች ይኖሯቸዋል፡፡

**፺፩ <u>መደበኛ ቁጠባ</u>**

፩ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በተወሰነው መሰረት መደበኛ ቁጠባን በተከታታይ መቆጠብ አለበት፤

፪ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የአንድ አባል ዝቅተኛ የመደበኛ ቁጠባ መጠን መወሰን አለበት፤

፫ የመደበኛ ቁጠባ መጠን የአባሉን የመቆጠብ አቅም ያገናዘበ፣ በአባሉ ማመልከቻ ላይ የሰፈረና በኅብረት ሥራ ማህበሩ የተፈቀደ መሆን ይኖርበታል፤

፬ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሰረት አባሉ ለመደበኛ ቁጠባ ወለድ የማግኘት መብት አለው፤

፭ አባላት ከቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ እስካልተሰናበቱ ድረስ የመደበኛ ቁጠባቸው በማንኛውም ጊዜ ወጭ ሆኖ አይከፈላቸውም፤

፮ መደበኛ ቁጠባ ለብድር ዋስትና በመሆን ያገለግላል፤

፯ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የመደበኛ ቁጠባ መጠን ማሳደግ ይችላል፡፡

**፺፪ <u>የፍላጎት ቁጠባ</u>**

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ከመደበኛ ቁጠባ በተጨማሪ በፍቃደኝነት የፍላጎት ቁጠባ መቆጠብ ይችላል፤

90. **<u>Type of Savings</u>**

1. Savings and loan cooperative societies have regular savings, interest savings, term savings, non-interest bearing savings and other miscellaneous savings as defined in their bylaws.

91. **<u>Regular Savings</u>**

1. Every member of a savings and loan cooperative society shall regularly maintain regular savings as determined in the bylaws;
2. The savings and loan cooperative society's bylaws must specify a minimum standard savings amount for a member;
3. The amount of regular savings should be based on the member's ability to save, settled on the member's application and approved by the cooperative society;
4. The member has the right to earn interest on regular savings as determined by the bylaws of the savings and loan cooperative society;
5. Members shall not be disbursed of their regular savings at any time until they are dismissed from the savings and loan cooperative society;
6. Regular savings serve as collateral for loans;
7. The savings and loan cooperative society may increase the regular savings rate based on the decision of the general assembly.

92. **<u>Voluntarily Savings</u>**

1. In addition to regular savings, a member of a savings and loan cooperative society may voluntarily save for demand savings;

፪ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሰረት አባሉ ለፍላጎት ቁጠባ ወለድ የማግኘት መብት አለው፣

፫ የፍላጎት ቁጠባን አባሉ በማንኛውም ጊዜ ወጪ ሊያደርገው ይችላል፣ ሆኖም ግን የፍላጎት ቁጠባ ወጪ ሊሆን የሚችለው ገንዘቡ ለብድር ዋስትና ካልተያዘ ብቻ ነው፣

፬ የፍላጎት ቁጠባን አባሉ ለብድር ዋስትና ማቅረብ ይችላል፣

፭ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የፍላጎት ቁጠባን ለማበረታታት የሚከፈለውን የወለድ መጠን በአካባቢው ያሉ የፋይናንስ ተቋማት ከሚከፍሉት የወለድ መጠን ጋር ተወዳዳሪ ማድረግ ይችላል፣

፮ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የፍላጎት ቁጠባን ሊያበረታታ የሚችለው የፍላጎት ቁጠባውን የመጠቀም አቅም ከፍተኛ ሲሆን ብቻ ነው፣

፯ የፍላጎት ቁጠባ ብድር ለመውሰድ የማባዣ ስሌት ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፣

፰ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) የተደነገገው ቢኖርም አባላት ብድር ከመውሰዳቸው በፊት ለተከታታይ ሶሰት ወራት የፍላጎት ቁጠባ ከቆጠቡና ብድር ወስደው፣ ብድሩን ከፍለው ሲጨርሱ እስከ ሶስት ወራት ሳያወጡ ከቆዩ የፍላጎት ቁጠባ የብድር የማባዣ ስሌት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣

፱ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) እና (፰) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ዝርዝር አፈጻጸሙን በሚመለከት በመተዳደሪያ ደንቡና በብድር መመሪያው በማካተት በጠቅላላ ጉባኤ በማጸደቅ መተግበር አለበት፡፡

2. The member is entitled to voluntary on demand savings as determined by the bylaws of the savings and loan cooperative society;
3. Voluntarily Savings may be spent by the member at any time, however, discretionary savings can only be an expense if the money is not held as collateral;
4. The voluntary savings member may provide collateral for the loan;
5. The savings and loan cooperative society may make interest rates competitive with local financial institutions to encourage interest savings;
6. Savings and loan cooperative societies can encourage demand savings only when the capacity to use the demand savings is high;
7. Voluntary Savings cannot be used as a multiplier to take out a loan;
8. Notwithstanding the provisions of sub article (7) of this article, if members save voluntarily savings for three consecutive months before taking a loan, voluntarily savings can be used as a loan multiplier calculation if you haven't spent up to three months after paying off the loan;
9. Subject to the provisions of sub article (7) and (8) of this article, any savings and loan cooperative society must include the details of its performance in its bylaws and loan directives and be approved by the general assembly.

፺፫ የጊዜ ገደብ ቁጠባ

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ከቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በገባው ውል መሰረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ማስቀመጥና በተጠየቀ ጊዜ መክፈል ይችላል፤

፪ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የጊዜ ገደብ ቁጠባ ሊቀመጥ የሚችልበት ጊዜ ከስድስት ወር ማነስ የለበትም፤

፫ አባሉ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለውን የጊዜ ገደብ ቁጠባ ለብድር ዋስትና ማቅረብ ይችላል፤

፬ ለብድር ዋስትና የዋለ የጊዜ ገደብ ቁጠባ ለአባሉ ወጪ ሆኖ አይከፈልም፤

፭ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሰረት አባሉ ለጊዜ ገደብ ቁጠባ ወለድ የማግኘት መብት አለው፤

፮ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የጊዜ ገደብ ቁጠባን ሊያበረታታ የሚችለው ቁጠባውን የመጠቀም አቅሙ ከፍተኛ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

፺፬ ወለድ አልባ ቁጠባ

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ወለድ የማይታሰብበት ቁጠባ ከአባላት ሊሰበስቡ ይችላሉ፤

፪ ወለድ የማይታሰብበት ቁጠባ አባሉ በማንኛውም ሁኔታ ወለድ መጠየቅ መብት አይኖረውም፤

፫ አባሉ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለውን ወለድ የማይታሰብበት ቁጠባ ለብድር ዋስትና ማቅረብ ይችላል፤

፬ አባሉ በቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለውን ወለድ የማይታሰብበት ቁጠባ ወጪ ሊያደርግ የሚችለው ገንዘቡ በዋስትና ካልተያዘ ብቻ ነው፡፡

93. **Time Limit Savings**

1. According to the contract entered into with the savings and loan cooperative society, the member of the savings and loan cooperative society can deposit in the cooperative society for a certain period of time and pay on demand;
2. In the case of savings and loan cooperative societies, the time limit for which savings can be deposited should not be less than six months;
3. The member can provide savings and loan guarantee for the time limit of the savings and loan cooperative society;
4. Term savings for loan guarantees are not paid as an expense to the member;
5. The member has the right to receive interest on time-limited savings as determined by the bylaws of the savings and loan cooperative society;
6. The savings and loan cooperative society can encourage time limit savings only when the capacity to use the savings is high.

94. **Interest-Free Savings**

1. Savings and loan cooperative societies may collect interest-free savings from members;
2. A non-interest bearing savings member shall not be entitled to claim interest under any circumstances;
3. The member can provide a guarantee for the loan of savings and loan which does not take into account the interest of the savings and loan cooperative society;
4. The member can spend the interest of the savings and loan cooperative society on unaccounted savings only if the funds are not secured.

## ፺፭ የልጆች ቁጠባ

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድሜያቸው ከ ፲፰ ዓመት በታች የሚገኙ ልጆች በቤተሰባቸው በኩል ማስቆጠብ ይችላሉ፤

፪ የልጆች ቁጠባ የቁጠባው ምንጭ ወላጆቻቸው ወይም ልጆቹ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመሰማራት በሚያገኟቸው ገቢዎች መሠረት የሚቆጥቡት ይሆናል፤

፫ ልጆች የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ሆነው ለቁጠባ ሲመዘገቡ የመመዝገቢያ ወይም የዕጣ ገንዘብ አይከፍሉም፤

፬ የልጆች የቁጠባ ሂሳብ ሲከፈት የቁጠባ ሂሳብ መክፈቻ መጠን በማህበሩ መተደዳሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ለመጀመሪያ ከከፈቱ በኋላ ግን በማንኛውም ሰዓትና ጊዜ የሚፈልጉትን መጠን ሊቆጥቡ ይችላሉ፤

፭ ለልጆች ቁጠባ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚያስቀምጠው መሰረት የቁጠባ ወለድ ይከፍላል፤

፮ ለልጆች ቁጠባ የተቆጠበው ገንዘብ ለብድር ዋስትና ሊያዝ አይችልም፤

፯ ልጆች ከሁለት ዓመት ያላነሰ ጊዜ ሲቆጥቡ የቆዩ ከሆነ ፲፰ ዓመት ሲሞላቸውና አባል መሆን ከፈለጉ የኅብረት ሥራ ማህበሩን እጣ ገዝተው ያለምንም መመዝገቢያ ክፍያ አባል ይሆናሉ፤

፰ የልጆች ቁጠባ ወጪ የሚሆነው ሕጻኑ ፲፰ ዓመት ሲሞላው በራሱ ይሆናል፤ ዕድሜው ፲፰ ዓመት ከመድረሱ በፊት ለሕጻኑ ጥቅም አሳማኝ በሆነ ምክንያት ገንዘብ ሊወጣ የሚችለው በወላጆች ወይም በሕጋዊ ሞግዚቶች በኩል በሚቀርብ የወላጅነት ወይም የሞግዚትነት ማስረጃ ነው፡፡

## 95. Children's Savings

1. Savings and loan cooperative societies children under the age of 18 can save through their families;
2. Children's savings, the source of the savings will be what the parents or the children save according to the income they get from engaging in various income-generating activities;
3. Children do not pay registration or share fees when they register for savings as members of the cooperative society.
4. When opening a children's savings account, the opening amount of the savings account is determined by the bylaws of the cooperative society, but after the first opening, you can save the amount you want at any time;
5. The savings and loan cooperative society for children's savings shall pay interest on savings as determined by its bylaws;
6. Savings for children cannot be used to secure loans;
7. If children have been saving for less than two years, when they turn 18 and want to become a member, they can buy the lot of the cooperative society and become a member without registration fee;
8. Children's savings are spent on their own when the child turns 18, before the age of 18, funds may be withdrawn for compelling reasons in the best interests of the child upon proof of parentage or guardianship provided by the parents or legal guardians.

፺፮ ሌሎች ቁጠባ ዓይነቶች

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በሚኖራቸው የዕድገት ደረጃና የመጠቀም አቅም መሰረት በመተዳደሪያ ደንባቸው ሌሎች ልዩ ልዩ የቁጠባ ዓይነቶችን በሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ፤

፪ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሌሎች ልዩ ልዩ የቁጠባ ዓይነቶች ስለ ወለድና ለብድር ዋስትና መያዣነትን በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

፺፯ የቁጠባ አገልግሎት ተግባር

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ከቁጠባ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሰጣቸውን የቁጠባ ዓይነቶች በሚገባ መለየትና መያዝ፤

፪ የተለያዩ ቁጠባ ዓይነቶችን ለመገልገል የሚመጡ ቆጣቢዎችን ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ቀድመው እንዲያውቁ ማድረግ፤

፫ በአባላት ላይ የቁጠባ ባህል እንዲዳብር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

፬ የቁጠባ ወለድ በወቅቱና በአግባቡ እንዲሰራ ክትትል ማድረግ፤

፭ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ስለሚሰጠው የቁጠባ አገልግሎት ለአባላት፣ ለአቻ ማህበራት እና ለኅብረተሰቡ ትምህርት፣ ስልጠናና መረጃ መስጠት፤

፮ የተለያዩ የቁጠባ አማራጮችን በማጥናትና በማስጠናት፤ የቀረቡትን በመገምገም የአባላትን የቁጠባና መዋለ ንዋይ አቅም ማሳደግ፤

፯ በቁጠባ የተሰበሰበ ገንዘብ ብድር ላይ የሚውልበትን አሰራር መንደፍና አባላትን የተሻለ የትርፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤

96. **Other Types of Savings**

1. Savings and loan cooperative societies may use other different types of savings in accordance with their bylaws according to their development level and capacity;
2. The savings and loan cooperative society should set the bylaws regarding interest and loan guarantee for other different types of savings.

97. **Savings Service Duties**

Savings and credit cooperative societies will have the following functions in relation to savings services:

1. Identify and manage the types of savings provided by the savings and loan cooperative society;
2. To inform savers who come to serve different types of savings in advance of the conditions they must meet;
3. Provide support and monitoring to develop a culture of saving among members;
4. Overseeing the timely and proper operation of savings interest;
5. Providing education, training and information to members, peer cooperative societies and the community about the savings services provided by the savings and loan cooperative society;
6. Studying and researching different savings options, to increase the savings and investment capacity of members by evaluating the proposals;
7. Designing a system for the use of money collected through savings and enabling members to be better beneficiaries of profits;

፰ የአባላትን የመቆጠብ አቅም በማሳደግ ለአባላቶቻቸው እርካታ የሚፈጥር አገልግሎት መስጠት፤
፱ አባላት በመኖሪያና በሥራ ቦታቸው በገንዘብ እንዲቆጥቡ በማበረታታት የፋይናንስ አቅማቸውን በተገቢው ሁኔታ ማጠናከርና ለብድር የሚውል ፋይናንስ አቅርቦት ማሳደግ፡፡

**፺፰ በቁጠባ መር አነስተኛ መድን ዋስትና**

ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር፡-
፩ አንድ አባል ያጠራቀመውን የመደበኛ ቁጠባ መጠን መሰረት በማድረግ የቁጠባ የህይወት መድን ዋስትና ሊሰጥ ይችላል፤
፪ የሚሰጣቸው የቁጠባ መር አነስተኛ መድን ዋስትና አይነቶች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚጠቀስ ሆኖ አነስተኛ የህይወት መድን ዋስትና፣ አነስተኛ የጤና መድን ዋስትና፣ አነስተኛ የወሊድ መድን ዋስትና እና ሌሎችን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

**፺፱ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ አባላት**

በቁጠባ መር አነስተኛ የመድን አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ አባላት፡-
፩ ቁጠባን መሰረት ያደረገ አነስተኛ የመድን ሽፋን ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎት ያላቸው፤
፪ አባላት የቁጠባ መር የህይወት መድን ውል ከገዙበት ጊዜ በፊት በተዘጋው የበጀት ዓመት የመጨረሻ ቀን ለነበራቸው እና ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት ለተዛወረው የቁጠባ ሚዛን የመድን ሽፋን ያገኙ ፤
፫ አነስተኛ የጤና እና የወሊድ መድን ዋስትና የሚገቡ አባላት አረቦኑ ከአባሉ ወርሀዊው የቁጠባ መጠን ላይ ተሰልቶ የሚሰራ መሆኑን እና ከበጀት አመቱ መጨረሻ በኋላ የማይዞር ስለመሆኑ የተረዱ፤

8. Provide services that create satisfaction for their members by increasing their savings capacity;
9. Encouraging members to save money in their homes and workplaces strengthen their financial capacity in appropriate conditions and increase the availability of financing for loans.

**98. Mini Insurance Through Savings**

Any savings and loan cooperative society shall:

1. A savings life insurance policy can be taken out based on the amount of regular savings a member has accumulated;
2. The types of savings policy mini insurance to be provided will be based on mini life insurance, mini health insurance, mini maternity insurance and others as mentioned in the bylaws of the society.

**99. Members who will Benefit**

Members who will benefit from savings-based minimum insurance services:

1. Those interested in availing savings based minimum insurance coverage;
2. Members get insurance coverage for the savings balance that they had on the last day of the fiscal year before the time they purchased the savings plan life insurance policy and which were carried over to the next fiscal year;
3. Members who subscribe to small health and maternity insurance understand that the premium is calculated based on the member's monthly savings amount and that it does not change after the end of the fiscal year;

፬ አረቦን በመክፈል አገልግሎቱን ለማግኘት ፈቃደኛ የሆኑ እና የአነስተኛ መድን አገልግሎቱን ለማግኘት በኅብረት ሥራ ማህበሩ የተረጋገጠ የጤና ችግር የሌለባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**፻ ስለቁጠባና ዕጣ ምጥጥን**

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት፡-

፩ ጠንካራ የካፒታል መሰረት እንዲኖራቸው እና ከተቋቋሙለት ዓላማ አንጻር የአባላትን የፋይናንስ ፍላጎት ለማርካትና ውጤታማ ለመሆን በየጊዜው ቁጠባና እጣን ማመጣጠን አለባቸው፤

፪ ከአባላት ተሰባሰቦ በአደራ የተቀመጠ ገንዘብ ሊጠብቅ የሚችል የዕጣ መጠን በማህበሩ ዘንድ የ፫.፭ እጅ ቁጠባ በ ፩ እጅ ዕጣ ምጥጥን መሆን አለበት፤

፫ አባላት የመደበኛ ቁጠባ በሚቆጥቡበት ወቅት በምጥጥኑ መሰረት የዕጣ መጠናቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ማድረግ አለባቸው፤

፬ የቁጠባና ዕጣ ምጥጥን ወደ ገንዘብ በቀላሉ የመቀየር ምጣኔ፣ ብድር ከቁጠባ ያለው ምጣኔ፣ የተንቀሳቃሽ ሀብት ከዘመኑ ብድር ወይም ዕዳ ያላቸው ምጣኔ ፣ ከጠቅላለ ሀብት የተገኘ ትርፍ እና የዕድገት ምጣኔ መጠበቅ አለበት ፡፡

**፻፩ የቁጠባ ወለድ ስሌት**

ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር፡-

፩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለቆጣቢዎች ወለድ ያስባል፤ የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት ለመስጠት ከወሰኑ የብድር ወለድ አይከፍልም፤

፪ የቁጠባ ወለድ ስሌት በብሔራዊ ባንክ ከተቀመጠው የወለድ መጠን በታች መሆን አይችልም፤

4. Those who are willing to get the service by paying a premium and must have no health problems certified by the cooperative society to get the small insurance service.

100. **Savings and Share Ratio**

Savings and loan cooperative societies:

1. In order to have a strong capital base and to satisfy the financial needs of members in terms of the objective for which they were established, they must regularly balance savings and incense;
2. The amount of the share that can protect the money collected from the members and kept in trust should be a ratio of 3.5 hand savings to 1 hand share;
3. Members should be able to increase their shared proportionately as they accumulate regular savings;
4. The ratio of savings to equity, the ratio of easy conversion to money, the ratio of loan to savings, the ratio of mobile assets to current loans or debts, the ratio of profit to total assets and the growth rate should be maintained.

101. **Savings Interest Calculation**

Any savings and loan cooperative society shall:

1. It shall charge interest to the depositors in accordance with the by-laws, if you decide to provide an interest-free loan service, you will not pay interest on the loan;
2. Savings interest calculation cannot be lower than the interest rate set by the National Bank;

፫ እንደ ቁጠባ አይነቱና ጊዜ የተለያየ ዓይነት የወለድ ተመን ይኖረዋል፤ ይህንንም በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልፅ ማስቀመጥ፣ በጠቅላላ ጉባኤ በማፀድቅና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፤

፬ የቁጠባ ወለድ በማህበሩ የሚመለከተው የስራ ክፍል ኃላፊ እና ባለሙያ አማካኝነት እየተጠና በሥራ አመራር ኮሚቴ ከታየ በኋላ በጠቅላላ ጉባዔ ሲፀድቅ ሥራ ላይ ይውላል፤

፭ በብሔራዊ ባንክ የሚደረግ የወለድ ለውጥን ተከትሎ የቁጠባ ወለድ መጠን ለውጥ ያደርጋል፤

፮ የቁጠባ ወለድ ተመን ለማውጣት የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል፡-

ሀ) የብሄራዊ ባንክ የወለድ ምጣኔ፤

ለ) ብሩን የመጠቀም አቅምና ወቅታዊነት፤

፯ የቁጠባ ወለድ ማስላት የሚጀምረው ቁጠባው ከተሰበሰበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

፰ የቁጠባ ወለድ መጠን ለውጥ ሲያደርግ ቀደም ሲል ለቆጠቡትም ሆነ ለአዲስ ቆጣቢዎች የቁጠባ ወለድ ማስተካከያ ማድረግ አለበት፤

፱ በመተዳደረያ ደንብ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የወለድ መሥሪያ ጊዜው በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ወይም በየወሩ ሊሆን ይችላል፤

፲ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) በተደነገገው መሰረት የመደበኛ ቁጠባ ወለድ እየተሰራ በአባሉ ደብተር ላይ የሚቀመጥ ሲሆን አባልነቱ ካልተቋረጠ በስተቀር ገንዘቡ ወጪ አይሆንም፤ የፍላጎት ቁጠባ ወለድ ገንዘብ አባሉ በፈለገበት ጊዜ ውጪ አድርጎ መውስድ ይችላል፡፡

3. Depending on the type of savings and duration, there will be different interest rates. This should be clearly stated in the bylaws, approved and implemented by the general assembly;
4. Savings interest will be studied by the head of the working department and an expert of the society and will be used after being approved by the general assembly after being reviewed by the management committee
5. Following the interest rate change by the National Bank, the savings interest rate will change;
6. The following points should be taken into consideration to calculate the interest rate on savings:
   a) National Bank interest rate;
   b) Ability and timeliness to use the money;
7. Calculation of interest on savings starts from the date of collection of savings;
8. When making a change in the savings interest rate, the savings interest must be adjusted for both existing and new savers;
9. Subject to the bylaws, the interest period may be once or twice a year or monthly;
10. According to the provisions of sub article (9) of this article, regular savings interest will be earned and deposited in the member's bank account, and the money will not be spent unless the membership is terminated; interest on interest savings can be withdrawn by the member whenever he wants.

**፻፪ <u>በቁጠባ አሰባሰብ የአባላት መብት እና ግዴታ</u>**

፩ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል በቁጠባ አሰባሰብ ላይ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው መሰረት ቁጠባውን ለብድር ዋስትና ማስያዝ፤

ለ) የሚቆጥበውን የመደበኛ ቁጠባ የገንዘብ መጠን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ከፍ ወይም ዝቅ የማድረግ፤

ሐ) ቁጠባን በተመለከተ መረጃ ጠይቆ የማግኘት እንዲሁም ቅሬታ ሲኖር የማቅረብና መልስ የማግኘት፤

መ) በማህበሩ የወለድ አሰላል መሰረት ለቆጠበው ገንዘብ ተመጣጣኝና ወቅቱን የጠበቀ ወለድ የማግኘት፤

ሠ) በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የቁጠባ መመሪያ መሰረት የፍላጎት ቁጠባ ወይም መደበኛ ያልሆነ ቁጠባን እና ወለድ ወጪ ማድረግ፤

፪ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማህበሩ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

ሀ) መደበኛ ቁጠባን ያለማቋረጥ የመቆጠብ፤

ለ) የመደበኛ ቁጠባንና ዕጣን በየጊዜው የማመጣጠን፤

ሐ) በመደበኛነት የሚቆጥበውን የገንዘብ መጠን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ ሲፈልግ በማመልከቻ የማሳወቅ፤

መ) በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያሉ ከቁጠባ ጋር የተያያዙ ህጎችን የማክበርና ተግባራዊ የማድረግ፡፡

**102. <u>The Rights and Duties of members in Savings Collection</u>**

1. Every member of the savings and loan cooperative society shall have the following rights in relation to the collection of savings:
   a) Reserve the savings for loan guarantee as stipulated in the cooperative society's bylaws;
   b) To increase or decrease the amount of regular savings to be saved according to the set time limit;
   c) Asking for information about savings and submitting complaints and getting answers;
   d) To get reasonable and timely interest for the money saved according to the cooperative society's interest calculation;
   e) To make interest savings or irregular savings and interest expense in accordance with the society's bylaws or savings directive;
2. Subject to the provisions of sub article(1) of this article, any member of the society has the following obligations:
   a) Regular saving on a regular basis;
   b) Periodic balancing of regular savings and loans;
   c) To notify by application when he wants to increase or decrease the amount of money he regularly saves;
   d) Related to savings according to the society's bylaws Compliance and enforcement of laws.

## ፻፫ ቁጠባ ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች

፩ ቁጠባ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) በየቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ያለው አባልነት ሲቋረጥ፤ ወይም

ለ) በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጊዜውን ጠብቆ መቆጠብ ሳይችል ሲቀር፤

፪ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ የሚያስቀምጠው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አባል ለተከታታይ አራት ጊዜ መደበኛ ቁጠባውን ካለበቂ ምክንያት ካቋረጠ ከአባልት ይሰናበታል፡፡

## ፻፬ የብድር አገልግሎት

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት እና አቻ ኅብረት ሥራ ማህበራት በመተዳዳሪያ ደንባቸው በሚወስኑትና በሚገቡት የብድር ውል መሠረት በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ የሚመለስ የገንዘብ ብድር አገልግሎት ሊሰጡ ወይም ሊወስዱ ይችላሉ፤

፪ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚያቀርቧቸው የብድር ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው እና የአባላትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ በወለድ ወይም ወለድ አልባ ሊሆን ይችላል፤

፫ ለአባላት የሚቀርብ ብድር እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ዓይነት፣ የብድር ዋስትና እና የብድር አመላለስ አሰራሮችን በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ አፀድቀው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፤

፬ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሰጡትን ብድር በገቡት ውል መሰረት በወቅቱ ሙሉ በሙሉ የማስመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 103. Reasons for Terminating Savings

1. Savings may be terminated for the following reasons:
   a) Upon termination of membership in the savings and loan cooperative society; or
   b) When he is unable to save time according to the cooperative society's bylaws;
2. Subject to the provisions of the bylaws of any savings and loan cooperative society, if a member ceases regular savings for four consecutive times without sufficient reason, he shall be dismissed from membership.

## 104. Loan Service

1. Savings and loan cooperative societies can provide or receive short, medium and long-term repayable financial loans to members and equivalent cooperative societies according to the loan contracts determined and entered into by their management regulations;
2. The types of loans offered by savings and loan cooperative societies to members may be interest-free or interest-free based on their bylaws and members' needs;
3. Loans offered to members should be approved and implemented by the general assembly according to the cooperative society's type of loan, loan guarantee and loan transfer procedures in accordance with their bylaws;
4. Savings and loan cooperative societies are obliged to pay back the loans given to their members in full on time.

**፻፭ ስለብድር**

፩ አንድ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለአባላትና በአዋጅ ለተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ብድር ይሰጣል፣

፪ የኅብረት ሥራ ማህበር የሚያበድረው የብድር ጣራ፣ የብድር ወለድ እና የብድር ዘመን የሚወሰነው በጠቅላላ ጉባኤ ነው፤

፫ ጠቅላላ ጉባኤው በሚሰጠው ውክልና መሰረት የሥራ አመራር ኮሚቴው የሚፈቅደው የብድር መጠን በመቶኛ ወይም በገንዘብ በግልጽ ተለይቶ መቀመጥ አለበት፡፡

**፻፮ የብድር አሰጣጥ**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ወቅታዊ እና ተደራሽነት ያለው የተለያየ የብድር ዓይነት እና መጠን ለአባላት ማሰራጨት አለበት፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት የሚያቀርበው ብድር በመጠየቂያ የተደገፈ፣ የብድር ወለድ መጠን እና የመክፈያ ጊዜ ሰሌዳ ሊኖረው ይገባል፤

፫ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለአባላት የሚሰጠው ብድር የሚከተሉትን ሁኔታዎችን ሊያሟላ ይገባል፤

ሀ) ለአባላቱ እና ለሌሎች አቻ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያሰራጨው የብድር ጥናትን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፤

ለ) ለብድር የሚውል ገንዘብ ምንጭ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል፣ ከአባላት ቁጠባ፣ መሰል ወይም ከሌሎች አቻ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከሚገኝ ብድር፣ ከመንግስት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ፣ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ ብድር እና ከሌሎች አቅም ገንቢዎች የሚገኝ ተዘዋዋሪ ፈንድ ሊሆን ይችላል፤

105. **Loan**

1. A savings and loan cooperative society provides loans to members and cooperative societies organized by proclamation in accordance with its bylaws;
2. The loan peak, loan interest and loan term of the cooperative society are determined by the general assembly;
3. Based on the representation given by the general assembly, the loan amount allowed by the management committee should be clearly defined in terms of percentage or money.

106. **Loan Issuance**

1. The cooperative society must distribute timely and accessible different types and amounts of loan to members;
2. The loan provided by the cooperative society to the members should be backed by invoice, loan interest rate and repayment schedule;
3. Any loan granted to members by a cooperative society must meet the following conditions:
   a) It should be based on a loan survey that it distributes to its members and other peer cooperative societies;
   b) The source of funds used for loans can be from the cooperative society's capital, members' savings, loans from similar or other equivalent cooperative societies, budget support from the government, loans from various financial institutions, and revolving funds from other capacity builders;

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባላት ከሚሰበስቡት ቁጠባ ጋር በሚደረገው ስምምነት መሠረት ከ ፸ እስከ ፹ በመቶ ድረስ ለብድር ሊያውሉ ይችላሉ፤

መ) ለአባላት ለሚሰጡት ብድር የሚያስከፍሉት የወለድ መጠኑን በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የተወሰነ እና በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ መሆን አለበት፤

ሠ) በወለድ አልባ ሥርዓት መሠረት የብድር አገልግሎት ክፍያ የሚሰጡ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጋር በሚያደርጉት ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፤

ረ) የብድር ውል ሲዘጋጅም ሆነ በብድር መመለሻ ጊዜ የብድር መክፈያ ጊዜ ሰሌዳ ለእያንዳንዱ ተበዳሪ አባል በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ወይም በኢሜል ወይም በማስታወቂያ በመጠቀም እንዲያውቁት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

**፻፯ ስለብድር ወሰን**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ አቅማቸውን ለማጠናከር ከአባላት፣ ከሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ከአበዳሪ ተቋማት መበደር ይችላሉ፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚበደሩት ብድር ካላቸው የካፒታል መጠን የማይበልጥ ሆኖ በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት፣

፫ ማንኛውም ማህበር ለሚበደረው ብድር የብድር መድን ዋስትና መግባት አለበት፤

፬ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚበደረው የብድር መጠንና ሁኔታ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ የሚበደረውን ብድር የመመለስ አቅሙን ያገናዘበ መሆን አለበት፤



c) The cooperative society may spend 70 to 80 percent on loans according to the agreement with the savings collected by the members;

d) The interest rate they charge for loans to members must be specified in their bylaws and approved by the general assembly;

e) Savings and loan cooperative society that provide loan service payments under an interest-free system will be carried out in an agreement with the members;

f) When the loan contract is prepared or during loan repayment, the loan repayment schedule can be made known to each borrower member in writing or electronic media by means of a short text message or e-mail or announcement.

107. **Loan Limit**

1. Cooperative societies can borrow from members, other cooperative societies or lending institutions to strengthen their financial capacity;
2. The amount of capital that cooperative societies borrow should not exceed the amount of loan they have, it must be decided by the general assembly;
3. Any society must take out loan insurance for the loans it borrows.
4. The amount and condition of the loan to be borrowed by the cooperative society must be determined by the bylaws of the cooperative society and must take into account the ability to repay the loan;

፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ መበደር የሚችሉት ገደብ በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት፤

፮ የኅብረት ሥራ ማህበራት በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የብድር አስተዳደር መመሪያ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

**፻፰ የብድር ዓይነትና ዘመን**

፩ መሰረታዊ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አ ጭርና የመካከለኛ ጊዜ ብድር ላይ ያተኩራሉ፤ እንዳስፈላጊነቱ የረጅም ጊዜ ብድር ሊሰጡ ይችላሉ፤

፪ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ዩኒዬንና ፌዴሬሽን የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ብድር ላይ ያተኩራሉ፤ እንዳስፈላጊነቱ የአጭር ጊዜ ብድር ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

**፻፱ ስለ ዋስትና ዓይነት እና አማራጮች**

ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የሚጠይቀው ዋስትና ዓይነት እና አማራጮቹን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚያበድሩት ብድር ለዋስትና የተለያዩ አማራጮችን እንደ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ዕድገት እና ደረጃ በመያዣነት መጠቀም ይችላሉ፤

፪ በዋስትና የሚያዙ ቋሚ ንብረቶች እና የገንዘብ ሰነዶች ትክክለኛነት በሚመለከታቸው አካላት መረጋገጥ አለባቸው፤

፫ ማንኛውም የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር ለሚያቀርበው የብድር አገልግሎት በዋስትና የሚይዘውን ንብረት ወይም ገንዘብ ዕዳው በወቅቱ ካልተከፈለ ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በመሸጥ ወይም ገንዘቡን ለዕዳ ማካካሻነት በማዋል ዕዳውን የማስከፈል መብት አለው፤

፬ ማንኛውም የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር ለሚሰጠው ብድር ተበዳሪዎችን የብድር ሕይወት ዋስትና እንዲገቡ አሰራሩን መዘርጋት አለበት፤

፭ በመተዳደሪያ ደንቡ እና በብድር መመሪያው ውስጥ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ለሚሰጠው ብድር የሚከተሉትን በዋስትናነት ሊይዝ ይችላል፡-

5. The limit that the management committee of the cooperative society can borrow must be determined by the general meeting;
6. Cooperative society may have loan management directive approved by the general assembly.

108. **Loan Type and Term**

1. Basic savings and loan cooperative societies focus on short- and medium-term loans; they can provide long-term loans as needed;
2. Savings and loan cooperative society unions and federations focus on medium- and long-term loans, they can provide short term loans as needed.

109. **Type of Guarantee and Options**

The types of guarantee and options required by any cooperative society for loan facilities include the following:

1. Cooperative societies can use various options as collateral for the loans they lend, depending on the growth and status of the cooperative societies.
2. Fixed properties and financial documents to be secured must be verified by the relevant parties;
3. Any savings and loan cooperative society has the right to collect the property or money that it holds as security for the loan service it provides, if the debt is not paid on time, by selling the property legally or using the money to pay off the debt;
4. Any savings and loan cooperative society must establish a procedure for the borrowers to enter the guarantee of the life of the loan;
5. Subject to the provisions of the bylaws and the loan directive, the cooperative society may hold the following as collateral for the loan:

ሀ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የተጠራቀመ የአባል ገንዘብ፤

ለ) የአባሉ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ሆኖ ንብረቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚቀርብበትና ከዚህ ቀደም በዕግድ ያልተያዘ መሆኑ ማስረጃ የሚቀርብበት፤

ሐ) በህግ ተቀባይነት ያላቸው ወደ ገንዘብ ሊለወጡ የሚችሉ ሰነድ ፤

መ) በድርጅት ወይም በመንግስት መስሪያቤት የተረጋገጠ የሠራተኛ የደመወዝ ዋስትና፤ ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተፈቀዱ ዋስትናዎች፡፡

፮ ብድር ጠያቂው በተለያየ ምክንያት የሚፈለግበትን ዕዳ መክፈል ባይችል የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባሉ ካለው የመደበኛ ቁጠባ፣ የዕጣና ሌሎች የአባሉን ድርሻ ለዕዳ ማካካሻ ማዋል ይችላል፣

፯ ተበዳሪው ዕዳውን መክፈል ካልቻለ የዋሱ ወይም የዋሶች ቁጠባና ዕጣ ለዕዳው ማካካሻ ይውላል፤

፰ የብድር ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አባል የቁጠባውን ፺፭ በመቶ ድረስ ያለ ተጨማሪ ዋስትና ሊበደር ይችላል፤

፱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፰) የተደነገገው ቢኖርም ብድሩ ከተጠቀሰው መጠን በላይ ከሆነ አባሉ ለተጨማሪው ብድር መጠን ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡

፻፲ <u>የብድር ወለድ</u>

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት ተመጣጣኝ ወለድ ያስከፍላል፤

፪ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ በጊዜና በዘርፍ ለሚሰጠው የተለያየ የብድር ዓይነት የተለያየ ዓይነት የወለድ ተመን ይኖረዋል፤



a. Member's money accumulated by the cooperative society;
b. The property is the member's fixed and movable property, where proof of ownership is provided and evidence is provided that it has not been seized in the past;
c. Legally convertible documents;
d. Employee salary guarantee certified by a company or government office, other warranties permitted by applicable law.

6. If the borrower is unable to pay the required debt due to various reasons, the member of the cooperative society can use the normal savings, allotment and other shares of the member to compensate the debt;
7. If the debtor is unable to pay the debt, the savings and lot of the guarantor or guarantors will be used to pay off the debt;
8. Subject to the loan peak, a member can borrow up to 95 percent of his savings without further collateral;
9. Notwithstanding the provisions of sub article (8) of this article, if the loan exceeds the specified amount, the member must provide a guarantee for the additional loan amount.

110. **<u>Loan Interest</u>**

1. The savings and loan cooperative society shall charge a reasonable interest for the loan service provided by the cooperative society;
2. The savings and loan cooperative society will have different interest rates for different types of loans given in time and sector;

፫ የብድር ወለድ በብድር ኮሚቴ ወይም በብድር ባለሙያ አማካኝነት እየተጠና በሥራ አመራር ኮሚቴ ከታዩ በኋላ በጠቅላላ ጉባዔ ሲፀድቅ ሥራ ላይ ይውላል፤

፬ በብሔራዊ ባንክ የሚደረግ የወለድ ለውጥን ተክትሎ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ወለድ መጠን ለውጥ ያደርጋሉ፤

፭ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር ወለድ ተመን ለማውጣት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡-

ሀ) ለብድር የሚውል ገንዘብ ዋጋ፤

ለ) ብድሩን ለማስፈፀም የሚደረግ አስተዳደራዊ ወጪ፤

ሐ) ለማይመለሱ ብድሮች መጠባበቂያ፤

መ) በወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም፤

ሠ) የቁጠባ ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ ማግኘት ያለበት ተመጣጣኝ ትርፍ፤

፮ የብድር ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ተበዳሪው ገንዘቡን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ወለድ መጠን ለውጥ ሲያደርግ በለውጡ መሰረት ቀደም ሲል የተበደሩትም ሆነ አዲስ ተበዳሪዎች ላይ የብድር ወለድ ማስተካከያ ይደረግባቸዋል፤

፰ ማህበሩ የብድር ወለድ ለውጡን ለተበዳሪዎች በጽሑፍ ወይም በማስታወቂያ ያሳውቃል፡፡

**፻፲፩ <u>የወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶች</u>**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የወለድ አልባ ብድር አገልግሎቶች እንደ ማኅበራቱ አቅምና ባህሪ የተለያዩ የወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶችን እያጠና በጠቅላላ ጉባኤ አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተሉት የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎቶች ለአባላቶቹ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) ሙራበሃ፤

ለ) ሰለም፤

ሐ) ኢጃራ፤

መ) ሙሻራክ እና የመሳሰሉትን ይሆናል፤

3. The loan interest will be studied by the loan committee or a loan expert and will be used after approval by the general meeting after the management committee.
4. Following the change in interest rate by the national bank, the cooperative societies will change the loan interest rate;
5. Cooperative societies should consider the following criteria to determine the loan interest rate:
   a) The value of the loan;
   b) Administrative expenses incurred in executing the loan;
   c) Provision for non-performing loans;
   d) Purchasing power at the time;
   e) The reasonable profit to be earned by the savings and loan cooperative society;
6. Interest on the loan will start from the date the borrower receives the money;
7. When the cooperative society makes a change in the loan interest rate, according to the change, the loan interest will be adjusted on both the previous borrowers and the new borrowers;
8. The cooperative society will inform the borrowers of the change in loan interest in writing or in a notice.

111. **<u>Interest Free Loan Services</u>**

1. The interest-free loan services provided by the cooperative societies will study various interest-free loan services according to the capacity and characteristics of the cooperative societies and approve and implement them in the general assembly;
2. According to sub article (1) of this article, the following interest-free financial services may be provided to the members:
   a) Murabaha;
   b) Silm;
   c) Ijara;
   d) It will be Musharak and so on;

፫. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ከላይ የተጠቀሱትን ሸሪዓ መር የፋይናንስ አገልግሎት ለብድር አስተዳደር አመቺ የሚሆኑ አሰራሮች፣ ሰነዶች፣ መዛግብቶች እና ቅፃቅፆችን ያዘጋጃል፤

፬. የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት መሰረት የሚያደርገው ግዥና ሽያጭን ሲሆን ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በአባላት ጥያቄ መነሻ መሰረት የገዛውን እቃ የራሱን ወጪ መሸፈኛ ጨምሮ ለአባሉ መልሶ በመሸጥ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤

፭. የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት የሚሰጠው ከወለድ አልባ ከተሰበሰበ ቁጠባ ብቻ ይሆናል፤

፮. በወለድ የተሰበሰቡ ገንዘቦች ለወለድ አልባ አገልግሎት አይውሉም፤

፯. ወለድ አልባ የሚሰበሰብ ብድር ገቢ የሚሆነው በወለድ አልባ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ይሆናል፡፡

**፻፲፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የብድር አስተዳደር መመሪያ ስለሚያወጡበት ሁኔታ**

፩. ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በኮሚሽኑ የብድር መመሪያ መሰረት የራሳቸውን የውስጥ የብድር አስተዳደር መመሪያ ማውጣት አለባቸው፤

፪. የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ ብድር አስተዳደር መመሪያ የሚከተሉት ይዘቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስምና አድራሻ፤
ለ) የብድር አገልግሎት ዓላማ፤
ሐ) የብድር አገልግሎት አስፈጻሚ አካላት፤
መ) የብድር ጣሪያ፤
ሠ) ተጨማሪ ብድር ስለመጠየቅ፤
ረ) የብድር ዘመንና ብድር ስለማራዘም፤
ሰ) የብድር ወለድ፤
ሸ) የወለድ አልባ ብድር፤
ቀ) የብድር ማመልከቻ አቀራረብና አወሳሰን፤
በ) የብድር ዋስትና፤
ተ) የብድር ውል፤
ቸ) ብድር ለማግኘት የሚያበቁና የሚያስከለክሉ ምክንያቶች፤

3. The savings and loan cooperative society prepares procedures, documents, records and forms that are convenient for credit management of the above-mentioned Shariah-based financial services;
4. Interest-free loan service is based on purchase and sale, and the cooperative society will be based on reselling to the member the goods purchased at the request of the members, including covering their own expenses;
5. Interest-free loan facility is provided only from interest-free savings;
6. Funds collected at interest are not used for non-interest-bearing purposes;
7. Interest-free loan proceeds will be deposited into the interest-free account number.

**112. Regarding the Issuance of Internal Loan Administration Directive for Cooperative Societies**

1. Every savings and loan cooperative society must draw up its own internal loan management directive in accordance with the commission's loan directive;
2. The internal credit management directive of savings and loan cooperative societies shall have the following contents:
   a) Name and address of the cooperative society;
   b) Objective of loan servicing;
   c) Loan service enforcement agencies;
   d) Loanpeak value;
   e) About requesting additional loans;
   f) About extending loan term and loan;
   g) Loan interest;
   h) Interest free loan;
   i) Presentation and determination of loan application;
   j) Loan collateral;
   k) Loan agreement;
   l) Reasons that end and prevent getting a loan;

ኀ) ስለ ብድር አሰጣጥና አሰባሰብ፤

ነ) በወቅቱ ስለማይሰበሰብ ብድርና መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች፤

ኘ) ሌሎች ቅጻቅጾች፤

፫ ማንኛውም የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የውስጥ የብድር አስተዳደር መመሪያ በጠቅላላ ጉባኤ በማጸደቅ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡

**፻፲፫ ስለ መድን ሽፋን**

፩ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብትና ንብረታቸውን ከተለያየ አደጋ ለመጠበቅ የመድህን ሽፋን ማግኘት ይችላሉ፤ ይኸውም ተፈጻሚ የሚሆነው በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን ነው፤

፪ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚሰጡት የቁጠባና ብድር አገልግሎት የመድህን ዋስትና ሽፋን ለቆጣቢዎችና ለተበዳሪዎች መስጠት ይችላሉ፡፡

## ክፍል አሥር
## የሂሣብ አያያዝ፣ ሂሳብ ምርመራ፣ ስለ ኢንስፔክሽን፣ የትርፍ አደላደል እና ቁጥጥር

**፻፲፬ የሂሳብ አካውንት ስለመክፈት**

፩ ማንኛውም ማህበር በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ድጋፍ ሲያገኝ ከሶስት ያልበለጠ የሂሳብ ቁጥር በአቅራቢያው በሚገኝ ህጋዊ እና አዋጭ በሆነ የፋይናንስ ተቋም ወይም ባንክ ላይ እንደ ሁኔታው የዝግ፣ የተንቀሳቃሽ እና የቁጠባ የሂሳብ ቁጥር መክፈት አለበት፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ከወሰኑት የገንዘብ መጠን በላይ በካዝና ወይም በእጅ ሊቀመጥ አይችልም፤

m) About lending and collection;

n) Uncollectible loans and measures to be taken;

o) Other formats;

3. Any savings and loan cooperative society's internal credit management guidelines must be approved by the general assembly and submitted to the commission or the office along with the cooperative society's bylaws.

113. **Insurance Coverage**

1. Savings and loan cooperative societies can obtain insurance coverage to protect their assets and property against various risks, that is, it will be enforced when decided by the general meeting of the cooperative society;
2. Savings and loan cooperative societies can provide insurance coverage to savers and borrowers for the savings and loan services they provide.

## PART TEN
## ACCOUNTING, AUDITING, PROFIT ALLOCATION AND CONTROL

114. **Opening a Financial Account**

1. Any cooperative society, upon obtaining the support of the commission or its office, shall open not more than three account numbers in the nearest legal and viable financial institution or bank, as the case may be, of closed, portable and savings accounts;
2. Subject to the provisions of sub article (1) of this article, more than the amount determined in their by-laws cannot be kept in cash or in hand;

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወለድ አልባ አሰራርን የሚከተሉ የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የመመዝገቢያና የዕጣ ክፍያ በወለድ አልባ የቁጠባ ሂሳብ እንዲቀመጥ በማድረግ ለብቻው አካውንት መክፈት አለባቸው፡፡

፬ ለማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚከፈቱ የሂሳብ ቁጥሮች በጠቅላላ ጉባዔ በተመረጡና በተወከሉ የሥራ አመራር ኮሚቴ የጋራ ፊርማ እንዲንቀሳቀስ በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣል፤

፭ የማንኛውም ማህበር በአዲስ የኮሚቴ አመራር ሲቀይር የኅብርት ሥራ ማህበሩ የተንቀሳቃሽ፣ የቁጠባ እና የጊዜ ገደብ የሂሳብ ቁጥር አዲስ በተመረጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ እና በተወከሉ አካላት የጣምራ ፊርማ ብቻ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

**፻፲፭ <u>የሂሳብ አያያዝ</u>**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ የሚያዘው በኅብረት ሥራ ማህበሩ ዋና ጽህፈት ቤት ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅርንጫፍ ካላቸው የራሳቸውን መረጃዎች በማደራጀት አስፈላጊ የሆኑትን መዛግብትና ሰነዶች በየወሩ በሂሳብ ሚዛን መሞከሪያ እና አባሪ ሰንጠረገሮች ተጠቃለው ለዋና ጽህፈት ቤቱ ይልካሉ፤

፪ የዋና ጽህፈት ቤት ከቅርንጫፍ መረጃውን በመሰብሰብ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የገቢና ወጪ መግለጫ ያዘጋጃል፤ ይህ የገቢና ወጪ መግለጫ ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭና የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓመታዊ የፋይንስ መግለጫ ለማዘጋጀት እንደመሰረት ያገለግላል፤

፫ የገቢና ወጪ እንቅስቃሴዎች በገቢና በወጪ መመዝገቢያ ላይ በዕየለቱ ይመዘግባሉ፤

፬ በወሩ መጨረሻ የገቢና ወጪ ምዝገባዎች እንቅስቃሴ የማጠቃለል ሥራ ይሰራል፤ የመዝገቡ ድምር ወደ አጠቃላይ ሌጀር በማስተላለፍ ይመዘገባል፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በረዳት ሌጀር ላይ በማስተላለፍ ይመዘገባል፤

3. Subject to the provisions of sub article (1) of this article, savings and loan cooperative societies that follow the interest-free system must open a separate account by depositing the registration and lot fees in an interest-free savings account;
4. A letter of support is given by the commission or the office to move the account numbers to be opened for any cooperative society under the joint signature of the management committee elected and represented by the general assembly;
5. When any cooperative society is replaced by a new committee management, the cooperative society's mobile, savings and time limit account number will be moved only by the joint signature of the newly elected management committee and its representatives.

**115. <u>Accounting</u>**

1. The accounts of the cooperative society are kept by the cooperative society's head office, and if the cooperative society has branches, they organize their own information and send the necessary records and documents to the head office every month in the form of balance sheets and attached tables;
2. The head office collects the information from the branch and prepares the income and expenditure statement of the cooperative society, this income and expenditure statement is distributed to users and serves as the basis for the preparation of the cooperative society's annual financial statement;
3. Income and expenditure activities are recorded on a daily basis in the income and expenditure register;
4. At the end of the month, the activities of income and expenditure registrations will be summarized. The total of the record is recorded by transferring it to the general ledger. Each movement is recorded by transfer on a subsidiary ledger;

፭ የአጠቃላይ ሌጀሩ ድምር በመውሰድ የወሩን የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ይዘጋጃል፤

፮ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ራሱን በራሱ የሚገልጽ የሂሳብ መለያ ወይም መግለጫ ሰንጠረዥ ያዘጋጃል ፤ እያንዳንዱ ሂሳብ የሚያዘው የሂሳብ መለያውን ወይም መግለጫውን መሰረት በማድረግ ነው፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ለኦዲት ዝግጁ ለማድረግ የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል፡-

ሀ) የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት፤

ለ) የመተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ፤

ሐ) የሂሳብና የኦዲት ሌሎች የተግባራት ማስፈፀሚያ መመሪያዎች፤

መ) በኦዲት ወቅት የተሰጡ ሙያዊ አስተያየቶች እና ግብረ መልሶች እና የተሰጡ የማስተካከያ እርምጃዎች፤

ሠ) በውስጥ ኦዲት፣ በቁጥጥር ኮሚቴ እና በኢንስፔክተሮች የተገኙ ግኝቶችና የተሰጡ ግብረ መልሶች፤

ረ) ከተለያዩ አካላት ጋር የተደረጉ ውሎችና ስምምነቶች፤

ሰ)የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔዎችና ውሳኔዎች፤

ሸ) ለአባላት የሚቀርቡ እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች፤

፰ የሂሳብ መለያ ወይም መግለጫ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻልና ሊስተካከል ይችላል፡፡

**፻፲፮ <u>ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ምርመራ ወይም ኦዲት አገልግሎት</u>**

፩ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ዘመን እንደ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ባህሪ የሚለያይ ቢሆንም ከሀምሌ ፩ እስከ ሰኔ ፴ ድረስ ያለው የሥራ ዘመን ይሆናል፤

5. By taking the sum of the general ledger, a monthly income and expenditure statement report is prepared;
6. The cooperative society shall prepare a self-explanatory account or statement table, each account is managed based on its account description or statement;
7. In order to prepare the accounts of cooperative societies for audit, attention should be paid to the following issues:
   a) Accounting documents and records;
   b) Bylaws and internal rules;
   c) Accounting and auditing other operational directives;
   d) Professional comments and feedback given during the audit and corrective actions taken;
   e) Findings and feedback provided by internal audit, control committee and inspectors;
   f) Contracts and agreements made with various parties;
   g) Minutes and decisions of the management committee meeting;
   h) Plans and performance reports for members;
8. An account or statement may be modified and amended as necessary.

**116. <u>Accounting Examination or Auditing Services for Cooperative Societies</u>**

1. The working period of any cooperative society varies according to the nature of the cooperative society's work, but the working period will be from July 1 to June 30;

፪. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘመናዊ የሂሳብ አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በኦዲት ተደራሽ በማድረግ በአባላት እና በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ዘንድ የሚኖራቸውን ታማኝነት ማሳደግ ይኖርባቸዋል፣

፫. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተከታታይነት ያለው የፋይናንስ አስተዳደር፣ የሥራ አመራር እና የማህበራዊ ኃላፊነት አፈጻጸም ደረጃ ያለበትን ሁኔታ ኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ኦዲት ይደረጋል፣

፬. የኅብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ የፋይናንስ እና አሰራራቸውን የሚቆጣጠሩ ተቀጣሪ የውስጥ ኦዲተሮች ሊኖሩት ይችላል፣

፭. ኅብረት ሥራ ማህበራት ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በግል ኦዲት ማስደረግ ይችላሉ፣ በግል ኦዲት ማካሄድ አቅሙ የሌለው ወይም በቀላሉ በአካባቢው የግል ኦዲት ተቋማት ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ሲረጋገጥ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ኦዲት ማድረግ ይኖርበታል፣

፮. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ኦዲት የሚያደርግ ማንኛውም አካል ከማንኛውም ጣልቃ ገብ አሰራር ነፃ ሆኖ የኦዲት ሥራውን በነፃነት ማከናወን ይኖርበታል፣

፯. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወይም እሱ የሚወክለው ሰው የአንድን ኅብረት ሥራ ማህበር አቋም የሥራ አፈፃፀም፣ መዛግብት ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሁኔታ በአዋጁ ፣ በደንቡና በመመሪያ መሠረት መጠበቅና ማስተዳደሩን ያረጋግጣል፣

፰. የኅብረት ሥራ ማህበራት አጠቃላይ ዕድገትን ለማጎልበት ቢያንስ በየዓመቱ የሒሳብ ምርመራ መደረግ ይኖርበታል፣

፱. የሒሳብ ምርመራ ሪፖርት ሙያዊ የሆነው አሰራር ትክክለኛነት በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለውሳኔ ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባል፡፡

2. Cooperative societies should develop a modern accounting system and make it accessible for audit to increase their credibility with members and other third parties;
3. The commission or the office will audit the state of continuous financial management, management and social responsibility performance of the cooperative societies;
4. Cooperative societies may have internal auditors employed to monitor their internal finances and operations;
5. Cooperative societies may conduct private audits in accordance with the directive issued by the commission; when it is confirmed that it is not possible to conduct a private auditor it is difficult to find private audit institutions in the area, the commission or the office should conduct an audit;
6. Any entity that audits cooperative societies should be free from any interference and conduct its audit work freely;
7. The appropriate authority or the person he represents ensures that the position of a cooperative society is maintained and managed in accordance with the proclamation, regulation and directive of the work performance, records, financial and property status;
8. In order to enhance the overall growth of cooperative societies, at least annual audit should be done;
9. After the correctness of the professional procedure of the audit report is confirmed by the commission or the office, it will be submitted to the general meeting of the cooperative society for decision.

**፻፲፯ ስለ ኢንስፔክሽን**

፩ በአዋጁ አንቀፅ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በህግ፣ ደንብና በተቀመጠው አሰራር ሥርዓት መሠረት እያከናወኑ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በኢንስፔክሽን ያረጋግጣል፤

፪ በየደረጃው ያሉ ለኅብረት ሥራ ማህበራት በማጠናከር ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎች በኢንስፔክሽን ምርመራ ውጤት የተሰጡ ሙያዊ አስተያየቶች እና ግብረ መልሶች ኅብረት ሥራ ማህበራት የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፡፡

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት በኢንስፔክሽን የተሰጡ ግብረ መልስ ውጤቶች ለጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ ግልፅ በሆነ ስፍራ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

**፻፲፰ የተጣራ ትርፍ አደላደል**

፩ በአዋጁ አንቀፅ ፵፭ ስለ ተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፋል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበራት በየዓመቱ ወጪ በመቀነስ እና ገቢ በማሳደግ ለአባላት ባላቸው ዕጣና ተሳትፎ መሰረት በማድረግ ተመጣጣኝ ትርፍ ያከፋፍላሉ፤

፪ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተጣራ ትርፍ ላይ ፴% እየቀነሰ በመጠባበቂያ ሂሳብ ያስቀምጣል፤ለመጠባበቂያነት የሚቀነሰው ገንዘብ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ካፒታል ፴% እስኪሞላ ድረስ የሚቀጥል ሆኖ የሚቀመጠውም በኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ ሂሳብ ውስጥ ይሆናል፤



**117. Inspection**

1. The commission or the office shall confirm through inspection that any cooperative society is operating in accordance with the law, regulations and the established procedure, subject to the provisions of sub article (1) of article 52 of the proclamation as well as other relevant laws;
2. The professional opinions and feedback given by the experts at all levels in strengthening the cooperative societies will support and monitor the cooperative societies to take corrective action;
3. Cooperative societies should present the results of the feedback provided by the inspection to the general assembly and keep them in a clear place.

**118. Net Profit**

1. Subject to the provisions of Article 45 of the proclamation regarding the distribution of net profit, cooperative societies shall distribute proportional profits to members based on their participation and share by reducing expenses and increasing income every year;
2. Any cooperative society shall deduct 30% of the net profit and keep it in a reserve account;

፫. ለመጠባበቂያ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ፸% የተጣራ ትርፍ ክፍፍል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሰረት ይሆናል፤ ሆኖም ጠቅላላ ጉባኤው በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከዚሁ የተጣራ ትርፍ ውስጥ ለትምህርት ወይም ለስልጠና ወይም ለማበረታቻ ወይም ለኦዲት ፈንድ ወይም ለማህበራዊ አገልግሎት በመደልደል ሊመድብ ይችላል፤

፬. ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት የትርፍ ክፍፍል ሲወስኑ እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓይነት እና የሥራ ባህሪ ለዕጣ ወይም ለተሳትፎ የሚከፈለው መጠን በኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛውን ድርሻ ለተሳትፎ ወይም ለዕጣ ሊወስኑ ይችላሉ፤

፭. ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ተሳትፎ የሚያበረታታ የአባላትን መረጃ በአግባቡ በተሳትፎ መዝገባ በወቅቱ መዝግቦ የትርፍ ክፍፍሉን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፤

፮. የኅብረት ሥራ ማህበሩ መጠባበቂያ ገንዘብ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል ፴ በመቶ በላይ ሲሆን ከተጣራ ትርፍ የሚቀነሰው መጠባበቂያ ገንዘብ ቀርቶ የተገኘው የተጣራ ትርፍ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሙሉ በሙሉ ለአባላት ይከፋፈላል፤

፯. እያንዳንዱ አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የገዛውን የዕጣና የከፈለው የገንዘብ መጠን እንዲሁም የተሳትፎ መጠንና አመዘጋገቡ በዚህ አንቀጽ መሰረት ስለመፈፀሙ በኦዲት ምርመራ ወቅት መረጋገጥ ይኖርበታል፤

፰. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለእያንዳንዱ አባል የትርፍ ክፍፍል ሲያከፋፍል እያንዳንዱ ግለሰብ አባል ከሚያገኘው ገቢ ላይ በሀገሪቱ የታክስ አከፋፈል ሥርዓት መሰረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ አማካኝነት ተቀንሶ በአቅራቢያው ለሚገኝ ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል፤

3. The remaining 70% of the net profit after deducting the reserve will be distributed as determined by the general assembly of the cooperative society, however, the general assembly may, according to the bylaws of the cooperative society, allocate from the same net profit for education or training or encouragement or audit fund or social service;
4. When cooperative society decide the dividend, depending on the type of cooperative society and the nature of the work, the amount paid for share or participation is determined by the regulations of the cooperative society, and they may determine the maximum allotment for participation or share;
5. Any cooperative society that encourages the participation of members should properly record the information of the members in the participation register and apply the dividend;
6. The reserve fund of the cooperative society is more than 30 percent of the capital of the cooperative society, and the net profit minus the reserve fund is deducted from the net profit and the net profit is distributed to the members in accordance with the bylaws;
7. The amount of money each member bought and paid from the cooperative society, as well as the amount of participation and the arrangements made in accordance with this article, should be verified during the audit;
8. When the cooperative society distributes dividends to each member, each individual member is required to deduct from the income of each member according to the country's tax payment system through the cooperative society and submit the income to the nearest tax collector's office;

፱ ከአበዳሪ አካላት ወይም ከሌላ አካላት የሚቀርብ ማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ሳይመለስ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት ምንም ዓይነት የትርፍ ክፍፍል አይደርግም፤

፲ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን ከኦዲት በኋላ የተገኘውን የትርፍ ክፍፍል ድርሻ የተዘረጋውን አሰራር እና የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ለአባላት በወቅቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

**፻፲፱ የሂሣብ ቁጥጥር**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት በየዕለቱ የሚደረግ ማንኛውም ገቢና ወጭ ወይም የሂሳብ እንቅስቃሴ በተዘጋጀለት ሰነድ በዕለቱ በአግባቡ መመዝገብ አለበት፤

፪ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሂሳብ በተከታታይ በየወሩ እየተዘጋ አጠቃላይ የሂሳብ አቋሙን የሚያሳይ የሒሳብ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፤

፫ የሥራ አመራር ኮሚቴውና የቁጥጥር ኮሚቴው የሂሣብ ሪፖርቶችን እየገመገሙ እንደየ ኃላፊነታቸው መጠን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

**፻፳ ልዩ ልዩ መዛግብትና ሰነዶች**

የኅብረት ስራ ማኅበሩን አመሰራረት ፣ የሥራ እንቅስቃሴ ፣ አሰራር ፣ ሀብት ፣ የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም በዝርዝር ሊያስረዳና ብክነትንና ምዝበራን ሊከላከልና ሊቆጣጠር የሚችል አሠራር እንዲሰፍን የሚከተሉት መዛግብትና ሰነዶች ሊሟሉ ይገባል፡-

፩ የአባላት መዝገብ፤

፪ የቃለ ጉባዔ መዝገብ፤

፫ የንብረት መዝገብ፤

፬ የብድር መዝገብ፤

፭ የተሳትፎ መዝገብ፤

፮ የገቢ ደረሰኝ ፤

፯ የወጪ ማዘዣ ፤

፰ የገቢ መዝገብ፤

፱ የወጪ መዝገብ፤

፲ የንብረት ገቢ ደረሰኝ፤

9. The cooperative society will not make any distribution of profits to the members without answering any claims from creditors or other parties;
10. The share of dividend received from the cooperative society union or federation after the audit shall be transferred to the members in a timely manner based on the established procedure and the needs of the members.

**119. Accounting Control**

1. Any daily income and expenditure or accounting activities of cooperative societies must be properly recorded on the day in the prepared document;
2. The accounts of the cooperative society must be closed every month and a financial report showing the overall financial position must be prepared;
3. The management committee and the control committee review the financial reports and take action according to their responsibilities.

**120. Various Records and Documents**

The following records and documents should be completed in order to explain in detail the establishment, activities, procedures, assets, financial management and use of the cooperative society and to establish a system that can prevent and control waste and embezzlement:

1. Register of Members;
2. Minutes of the Meeting;
3. Property Registry;
4. Loan Record;
5. Record of Attendance;
6. Receipt of Income;
7. Expense Order;
8. Income Record;
9. Expense Register;
10. Property Deposit Receipt;

፲፩ የንብረት ወጪ ደረሰኝ፤

፲፪ አጠቃላይ የሂሳብ ቋት፤

፲፫ የምርት አገልግሎት ዋጋ መተመኛ መዝገብ፤

፲፬ ሌሎች መዛግብቶችና ቅጻ ቅጾች ይገኙበታል፡፡

**፻፳፩ <u>የኅብረት ሥራ ማህበር የብድር አገልግሎትና አፈፃፀም</u>**

፩ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ላቀዳቸው ሥራዎች የገንዘብ ዕጥረት ሲያጋጥመው ከአባላት ፣ ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ከፋይናንስ ተቋማት ሊበደር ይችላል፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበር የሚበደረው ብድር ካለው የካፒታል መጠን የማይበልጥ ሆኖ በጠቅላላ ጉባኤ መወሰን አለበት፤

፫ የብድር መጠን ፣ የጊዜ ገደብ ፣ የወለድ መጠን እና ዋስትና በኅብረት ስረ ማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ጣሪያና በበጀት አመቱ የጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሰረት ብድሩ ሊፈጸም ይገባል፡፡

**፻፳፪ <u>ድርሻን እና ጥቅምን ስለማስከበር፣ ስለማቻቻልና ስለማስተላለፍ</u>**

፩ በአዋጁ አንቀፅ ፳፮፣ ፴፣ ፵፣ ፵፩ እና ፵፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከአባልነት ሲሰናበቱ ጥቅሞቻቸው ተከብሮላቸው ያለባቸው ዕዳ ተቻችሎ ይስተናገዳሉ፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል የኅብረት ሥራ ማህበራት ያስቀመጠውን የቁጠባ ገንዘብ ወዲያው የማግኘት መብት አለው፤

፫ ማንኛውም አባል ዕጣ ማግኘት የሚችለው የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኦዲት ተደርጎ ይሆናል፤

፬ ማንኛውም አባል የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ የሚያጋጥመው ከሆነ አባሉ ኪሳራውንም በሕጉ መሰረት የድርሻውን የሚካፈል ይሆናል፤



11. Property Expense Receipt;
12. A General Ledger;
13. Product Service Pricing Register;
14. Other Records and Forms are included.

**121. <u>Cooperative Society Loan Service and Perforce</u>**

1. When the cooperative society has a lack of funds for its planned activities, it may borrow from members, other cooperative societies, or financial institutions;
2. The amount of capital to be borrowed by the cooperative society must be determined by the general assembly;
3. The amount of loan, time limit, interest rate and guarantee should be done according to the ceiling of the cooperative society's bylaws and the general meeting of the financial year.

**122. <u>Upholding Share and Benefits, Setoff and Transferring</u>**

1. Subject to the provisions of articles 26, 30, 40, 41 and 42 of the proclamation, when the members of the cooperative societies are dismissed from membership, their interests will be forgiven.
2. Subject to the provisions of sub article (1) of this article, any member has the right to receive the savings deposited by the cooperative societies immediately;
3. Any member can get a lot if the cooperative society has been audited;
4. If any member of the cooperative society suffers a loss, the member will share the loss according to the law;

፭ አንድ አባል በፍላጎቱ ማህበሩን መልቀቅ ሲፈልግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ከአባልነት እንዲሰረዝ ሲደረግ ወይም በሞት ከተለየ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈልግበትን ዕዳ ከከፈለና ካቻቻለ በኋላ የሚቀረው ድርሻና ጥቅም የሚከበርለት ይሆናል፤

፮ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ መሠረት አንድ አባል ያለው ጥቅሙ ወይም ድርሻው ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ውጭ ላለበት ዕዳ ወይም ተጠያቂነት ሊከበር፣ ሊያዝ ወይም ሊሸጥ አይችልም፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባሉ ላይ የሚፈልገው ዕዳ የሚኖር ከሆነ አባሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ካለው ድርሻ ወይም ሌሎች ጥቅሞች ላይ በመቀነስ ዕዳውን ያቻችላል፤

፰ የአባሉ ዕዳ ከሚቻቻለው ዕጣ ወይም ጥቅም በላይ የበለጠ ከሆነ በሥራ አመራር ኮሚቴ አማካኝነት ዋስ እንዲሸፍን ይደረጋል፤ ሆኖም ዕዳው በዋሱ የማይሸፈን መሆኑ ሲረጋገጥ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል፤

፱ አባሉ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለውን ድርሻና ጥቅም ማስተላለፍ የሚችለው አባሉ በሚያቀርበው ማመልከቻ ብቻ ነው፤

፲ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ድርሻውንና ጥቅሙን ማስተላለፍ የሚችለው ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን ለገለጸ ሰው መሆን ይችላል፤



5. When a member wants to leave the society at his own will, or when he is terminated from membership by a court decision, or if he dies, the remaining share and interest will be respected after he has paid and settled the debt he wants from the cooperative society;
6. According to article 42 of the proclamation, the interest or share of a member cannot be secured, attached or sold for any debt or liability outside the cooperative society;
7. If there is a debt that the cooperative society wants from the member, the member will settle the debt by deducting from the share or other benefits in the cooperative society;
8. If the debt of the member is more than the possible lot or interest, it will be covered by the guarantee through the management committee, however, when it is confirmed that the debt cannot be covered by the guarantee, it will be submitted to the general assembly for a final decision;
9. The member can transfer the share and benefit from the cooperative society only by the application submitted by the member;
10. Any member of a cooperative society can transfer his shares and benefits to a person who is a member of the cooperative society or who has expressed his willingness to become a member of the cooperative society;

፲፩ ወራሹ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለመሆን ከፈለገ በዚህ ደንብና መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሰረት የአባልነት መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲወረስ የተፈቀደለትን ድርሻና ጥቅሙ ታስቦለት በአዲስ አባልነት መመዝገቢያ በመክፈል የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

**፻፳፫ የመንግስት ድጋፍ**

በአዋጁ አንቀፅ ፵፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት በተጨማሪነት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚከተሉትን ድጋፎች ያደርጋል፡-

፩ ኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ አንፃር የተለያዩ ድጋፍ ያደርጋል፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አሰራር በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማዘመን፤

፫ ምርታማነት ሊጨምሩ የሚያስችሉ ልምዶች፣ አሰራሮች በማምጣት እንዲጠቀሙ ማድረግ፤

፬ የውስጥ የፋይናንስ አቅማቸው እንዲያድግ የተለያዩ የፋይናንሰ አማራጮች ወይም የኅብረት ሥራ ፈንድ መዘርጋት፤

፭ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞች በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤

፮ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ስልጠና ተቋም እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግና፣ ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት፤

፯ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት የሚያግዙ ምክረ ሃሳቦችን የሚሰጡ የአማካሪ ምክር ቤቶችንና አማካሪ ባለሙያዎችን ማቋቋም፤

፰ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቢዝነሳቸውን በማስፋፋት ውጤታማ እንዲሆኑና ለዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ድጋፍ ማድረግ፤

፱ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤

11. If the heir wishes to become a member of the cooperative society, if he meets the membership requirements as determined by these regulation and bylaws, the cooperative society is allowed to be inherited. He can become a member of the cooperative society by paying a new membership registration for his share and benefits.

**123. Government Assistance**

Subject to the provision of article 43 of the proclamation, the government will additionally provide the following support for the development of cooperative societies:

1. It provides various support in terms of the level of development reached by the organization of cooperative societies;
2. Modernizing the operation of cooperative societies with the support of technology;
3. Bringing practices and procedures that can increase productivity and making them use them;
4. Developing various financing options or cooperative society funds to increase their internal financial capacity;
5. Designing and implementing various projects and programs;
6. Supporting the establishment of a cooperative society education and training institution and providing education and training based on existing conditions;
7. Establishing advisory councils and advisory experts who provide recommendations to help the development of cooperative societies;
8. If cooperative societies are established, they should be expanded to be effective and support the creation of employment opportunities for citizens;
9. Establishment of various operating procedures;

፲ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እንደአስፈላጊነቱ የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ድጋፍ፤

፲፩ የአገር ውስጥ እና የውጭ የገበያ ትስስር ድጋፍ፤

፲፪ የቁጥጥር እና ተከታታይነት ያለው የቴክኒክ ድጋፍ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፻፳፬ ስለ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት

፩ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ) አባላት ማኅበራቸውን ለማፍረስ በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ልዩ ውሳኔ እንዲፈርስ ከተወሰነ፤

ለ) የአባላት ቁጥር በዚህ ደንብ ከተደነገገው በታች ከሆነ፤

ሐ) ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሲወሰን ፤ወይም

መ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሰረት ለተከታታይ ሦስት ጊዜ የከሰረ እና የኪሳራውም መጠን የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ህልውና የሚያሳጣ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥና በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው ምክንያት ኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሚፈርስ ከሆነ ውሳኔውን በ ፯ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፫ አንድን የኅብረት ሥራ ማህበር በህጋዊ መንገድ ለማፍረስ የሚከተሉትን አሰራሮች ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡-

ሀ) የሂሳብ አጣሪ ማቋቋም፤

ለ) ለገንዘብ ጠያቂዎች ጥሪ ማስተላለፍ፤

ሐ) የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ማክበር፤

መ) ማኅበሩን ከመዝገብ መሰረዝ፤

10. Support for cooperative societies to find workplaces as needed;
11. Domestic and foreign market linkage support;
12. Monitoring and ongoing technical support can help.

## 124. Dissolution and Winding up

1. Any cooperative society may be dissolved for any of the following reasons:
   a) If members decide to dissolve their cooperative society in a special resolution at the general assembly meeting;
   b) If the number of members is less than stipulated in this regulation;
   c) When the cooperative society is decided to be dissolved by the court; or
   d) According to the results of the winding up of the cooperative society, it has been bankrupt three times in a row and the amount of the loss is such that the existence of the cooperative society is confirmed by the relevant authority and approved by the general assembly;
2. If the cooperative society is dissolved due to the reason mentioned in sub article (1) of this article, the decision must be notified to the commission or the office within 7 days;
3. In order to legally dissolve a cooperative society, the following procedures should be followed:
   a) Establishing liquidator;
   b) Calls on creditors;
   c) Protection of creditors;
   d) Cancellation of a society from the register.

፬ የሚቋቋመው ኮሚቴ በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ሆኖ የኮሚቴው ስብጥርም ከማደራጃና ማስፋፊያ፣ ከህግና ኢንስፔክሽን እና ከኦዲት የሥራ ክፍሎች ይሆናል፡፡

**፻፳፭ <u>የሂሳብ አጣሪዎችን ስለ መሾም እና መሻር</u>**

፩ በአዋጁ አንቀፅ ፶፮ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ የሚሾሙ የሂሳብ አጣሪ አባላት ቁጥር ሦስት ሲሆኑ አመራረጣቸውም የኦዲት፣ የህግ እና አደራጅ ባለሙያዎች ይሆናል፤

፪ አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር የመፍረስ ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ ሂሳቡ እንዲጣራ የሂሳብ አጣሪዎች በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ይመደባሉ፤

፫ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የመደባቸውን የሂሳብ አጣሪዎች ከመመሪያ ውጪ ሲሰሩ ከተገኙ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በማንኛውም ጊዜ በሙሉም ሆነ በከፊል ከሥራቸው ሊያግድ ወይም ሊሽር እና በምትካቸው አዲስ ሊሾም ይችላል፤

፬ ከሂሳብ ማጣራት ሥራቸው የተሻሩ የሂሳብ አጣሪዎች የስንብት ደብዳቤ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ በእጃቸው የሚገኘውን ንብረት፣ ማስረጃዎች፣ መዛግብት፣ ሠነዶች እና የመሳሰሉትን በምትካቸው ለተመደቡት ሂሳብ አጣሪዎች የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፤

፭ ከሥራቸው የተሰናበቱ ሂሳብ አጣሪዎች በሰባት ቀናት ውስጥ በእጃቸው የሚገኙትን ንብረቶች እና ሠነዶች ካላስረከቡ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይጠየቃሉ፤

፮ የሂሳብ ሥራውን ለማጣራት ለተሾሙት የሂሳብ አጣሪዎች ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ተገቢውን የአገልግሎት ዋጋ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲከፈል ሊወሰን ይችላል፡፡

4. The committee will be established by the commission or the office and the composition of the committee will be from the departments of organization and expansion, legal inspection and audit.

**125. <u>Appointment and Revocation of Liquidators</u>**

1. Subject to the provision of sub article (1) of article 56 of the proclamation, the number of liquidators appointed by the commission or the office will be three and their selection will be audit, legal and organizational experts;
2. After a decision to dissolve a cooperative society, liquidators are appointed by the commission or the office to audit the accounts;
3. If the commission or the office are found to be working outside of the directive, the commission or the office may suspend or revoke their duties in whole or in part at any time and appoint new ones in their place;
4. Liquidators revoked from their audit work are obliged to hand over their assets, evidence, records, documents, etc. to the liquidators assigned to replace them within seven days from the date of receiving the resignation letter;
5. If the revoked liquidators do not hand over the assets and documents in their possession within seven days, they will be asked according to the relevant law;
6. It may be decided that the commission or the office shall pay an appropriate service fee from the cooperative society to the liquidators appointed to audit the accounts.

**፻፳፮ ኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ ስለሚጣራባቸው ምክንያቶች**

የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ሊጣራ ይችላል፤

፩ ሕልውና እንዲያጣ ሲወሰን፤

፪ የዕዳ ጠያቂ አካላትን ለመለየት፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሃብት፣ ንብረትና ዕዳ ለመለየት እና የዕጣ ድርሻ ለማውቅ፤

፬ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ዕዳዎችን ለመለየት፤

፭ ቅጥር ሠራተኞችን ለመለየት እና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ፤

፮ የማይከፋፈል የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት ለመለየት፤

፯ በመከፈል ወይም በመዋሃድ ፈርሶ ዳግም ለመደራጀት ሲወሰን፤

፰ ተመዝግቦ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሥራውን ያልጀመረ ከሆነ፤

፱ ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በቋሚነት ካላስመዘገበ ወይም ጊዜያዊ ምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ወይም እንዲመልስ የሚደረግ ከሆነ፤

፲ ሂሳብ ተመርምሮ ኪሳራ ውስጥ የገባ እና የገባበት ኪሳራ በቀላሉ ከኪሳራው ውስጥ በማውጣት ወደነበረበት መመለስ የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

፲፩ ሥራውን በሌላ መልኩ ለመቀየር ሲወስን ወይም ዓላማውንና ተግባሩን ሲቀይር፤

፲፪ የአባላት ብዛት ወይም ቁጥር በሕግ ከተወሰነው በታች ሲቀንስ፤

፲፫ ከተቋቋመበት ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ ውጪ ሲሰራና የኅብረት ሥራ መርሆዎችን ጥሶ ሲገኝ፡፡

**፻፳፯ የሂሳብ አጣሪዎች ግዴታ እና ኃላፊነት**

የአዋጁ አንቀጽ ፶፯ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-



**126. Reasons for Winding up Cooperative Society Accounts**

Accounts of any cooperative society may be audited for the following reasons:

1. When it is decided to cease to exist;
2. To identify debtors;
3. To identify the resources, assets and liabilities of the cooperative society and to know the share;
4. To distinguish between receivables and payables;
5. To identify employees and protect their interests;
6. To identify the indivisible property of the cooperative society;
7. When it is decided to dissolve and reorganize through division or amalgamation;
8. If he has not started his work within six months of his registration;
9. If he does not register his temporary registration certificate permanently within a period of one year or if he returns or causes to be returned the temporary certificate;
10. When an account is examined and it is found that the loss cannot be recovered by simply taking it out of the loss;
11. When he decides to change his job in another way or when it changes his objective and function;
12. When the number or number of members is reduced below that determined by law;
13. When it works outside of the objective of his establishment and according to the bylaws and violates the principles of the cooperative society.

**127. Duties and Responsibilities of Liquidators**

Subject to the provisions of Article 57 of the proclamation:

፩ የሂሳብ አጣሪዎች ተጀምረው ለነበሩት ፩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ውል አፈፃፀም የሚያገለግሉ ሥራዎች ካልሆነ በስተቀር ወይም የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ ካላስገደደ በስተቀር አዲስ ሥራዎችን ለመጀመር አይችሉም፡፤ ከዚህ ውጪ ለሚሰሩ ሥራዎች በነጠላም ሆነ በአንድነት ተጠያቂ ይሆናሉ፤

፪ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ላይ እስከ መጨረሻው የሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ያለውን የሥራ እንቅስቃሴ መግለጫ፣ የማህበሩን ሃብትና ሠነዶች በኃላፊነት ይረከባሉ፤

፫ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያለውን የሚከፋፍልና የማይከፋፍል ንብረት ይለያሉ፤ ይሰበስባሉ፤ ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ተከፋይ ዕዳ በዝርዝር ያዘጋጃሉ፤

፬ ኅብረት ሥራ ማህበሩን የአባላት ቁጥር እና ያላቸወን የዕጣ ድርሻ ይለያሉ፤

፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ እንዲጣራ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት ሁሉ ይፈጽማሉ፤

፮ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት መሸጥ፣ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሆነው በፍርድ ቤት ቀርበው መከራከርና መገላገል እንዲሁም ነገርን በሽምግልና ዳኝነት ለመጨረስ ሊዋዋሉ ይችላሉ፤

፯ ለሂሳብ ማጣራቱ ሥራ የሚያገለግሉ ወጪዎችን ይወስናሉ፤

፰ ከዕዳ ጠያቂዎች ጋር ስለ አለው ዕዳና ስለ አከፋፈሉ ሁኔታ በመነጋገር ሊወስኑ ይችላሉ፤

፱ በኅብረት ሥራ ማህበሩ በማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ወይም ተቋም መካከል ስለ አለው አለመግባባት ወይም ክርክር ኅብረት ሥራ ማህበሩን በመወከል በግልግል ወይም በዕርቅ ለመጨረስ ይችላሉ፤

1. Liquidators cannot start new activities except for activities that are used for the execution of the contract of the cooperative society that has been started or unless the audit requires work. They will be responsible individually or jointly for any work done outside of this;
2. From the management committee of the cooperative society, they will be responsible for the description of the work activities until the final accounting period, the resources and documents of the society;
3. Distinguish between divisible and indivisible assets of the cooperative society, they collect. Prepare detailed accounts receivable and accounts payable;
4. They distinguish the cooperative society by the number of members and the share that they do not have;
5. They shall carry out all necessary duties for the audit of the accounts of the cooperative society;
6. They can sell the cooperative society's property, appear in court on behalf of the cooperative society, and agree to settle matters through arbitration;
7. Determine the costs of the winding up;
8. They can decide by talking to the creditors about the debt and the payment situation;
9. They can mediate or mediate on behalf of the cooperative society any dispute or dispute between the cooperative society or any person or organization or institution;

፲ ከዕዳ ክፍያ በኋላ በቀረው ገንዘብ ላይ ጠቅላላ ጉባኤውን በማነጋገር ስለ አከፋፈሉ ይወስናሉ፤

፲፩ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ የሚጠየቀውን ዕዳ በመመርመር የአከፋፈል ቅደም ተከተል ይወስናሉ፤

፲፪ የሂሳብ አጣሪዎች በሾማቸው አካል ሥልጣናቸውን የሚቀንሱ ውሳኔዎች ካልተደረጉ በስተቀር የሂሳብ ማጣራቱን ተግባር ከፍፃሜ ለማድረስ ሙሉ ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤

፲፫ የሂሳብ የማጣራት አካሄድ የሚገልፅ የደረሱበትን ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት በየሳምንቱ ለሾማቸው ወይም ለመደባቸው ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፤

፲፬ የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ ተጠናቆ ውህደቱ ወይም ክፍፍሉ ከተፈጸመ በኋላ በሥራ ምክንያት በእጃቸው የገቡትን ማንኛውንም መዛግብትና ሰነዶች በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ በአዲስ ለተቋቋመው ኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ወይም አባል ለነበረበት የሕብረት ሥራ ዩኒየን ወይም የሕብረት ሥራ ፌደሬሽን በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ያስረክባሉ፤

፲፭ በተገለጸው ቀን ውስጥ በእጃቸው የሚገኘውን ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበር ንብረት እና ሰነድ ካላስረከቡ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በሕግ መሠረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

፲፮ የሂሳብ ማጣራቱ ሥራ ሳይጠናቀቅና ከኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ፈቃድ ሳያገኝ የሂሳብ ማጣራት ሥራ ላይ የተመደበ ወይም የተሾመ ማንኛውም ሰው ስለሂሳብ ማጣራቱ ለሌላኛው አካል አሳልፎ መረጃ መስጠት አይችልም፤

10. They will decide on the distribution of the remaining money after debt payment by contacting the general assembly;
11. They will determine the order of disbursement by examining the debt owed to the cooperative society;
12. Liquidators shall be fully responsible for the completion of the audit unless decisions are made by the body appointing them to reduce their authority;
13. They must prepare a report detailing the accounting process and submit it to the commission or office assigned to them on a weekly basis;
14. After the winding up is completed and the merger or division is completed, they will hand over any records and documents that come into their hands as a result of work to the newly established cooperative societies or the commission or the office or the cooperative society union or cooperative society federation of which it was a member for safe keeping;
15. If they do not hand over any assets and documents of the cooperative society in their hands within the specified date, the commission or the office will cause them to be questioned according to law;
16. Any person who has been assigned or appointed to work on the winding up before the winding up is completed and without obtaining permission from the commission or the office cannot give information about the winding up to the other party;

፲፯ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ንብረቶችን ግልጽ በሆነ መንገድ ይሸጣሉ፣ ስም ያዛውራሉ፣ ክፍፍሉ እስኪፈፀምም በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሳብ ከፍተው በኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥም "በመጣራት ላይ ያለ ሂሳብ" በማለት ያስቀምጣሉ፤ የባንክ ሂሳቡን ያስተዳድራሉ፤ ክፍያዎችንም ይፈጽማሉ፣

፲፰ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፮) መሰረት የትኛውንም መረጃ አሳልፎ የሰጠን አጣሪ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ አግባብ ባለው ሕግ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

፻፳፰ <u>በሂሳብ ማጣራት ሥራው የኮሚሽኑ ወይም የጽህፈት ቤቱ ሚና</u>

፩ የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው ሚና ይኖረዋል፡-

ሀ) ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ባደረገው ሂሳብ ምርመራ ወይም ኢንስፔክሽን ወይም ከሌላ ወገን በቀረበለት ጥያቄ መሠረት የመዋሃድ ወይም መከፈል ወይም የማፍረስ ውሳኔ ሲሰጥ የሂሳብ ማጣራት ሥራ እንዲከናወን ያዛል፤

ለ) የሂሳብ ማጣራት ሥራው ለማካሄድ የማፍረስ ውሳኔው በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ መሰረት መጽደቁን ያረጋግጣል፤

ሐ) የሂሳብ አጣሪዎችን ይመድባል ወይም ይሾማል፤ አሥራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሂሳብ ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

መ) በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀውን የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት እና የመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም ለመፍረስ የተሰጠውን ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ለሂሳብ አጣሪዎች ያስረክባል፤

17. In accordance with the law, they sell assets in a transparent manner, transfer names, open a mobile bank account in the name of the cooperative society and keep it in the name of the cooperative society as "account in progress" until the distribution is done, they manage the bank account. They also make payments.

18. According to sub article (16) of this article, the investigation commission or the office may ask for any information that has been given to us by the relevant law.

**128. <u>The Role of the Commission or Office in the Winding up</u>**

1. The commission or office will have the following role:

   a) When the commission or the office makes a decision on amalgamation or division or liquidation based on an winding up or inspection on its own initiative or at the request of another party, it orders an audit to be carried out;

   b) Confirms that the decision to dissolve the accounts has been approved according to the special resolution of the general assembly;

   c) Assign or appoints liquidators, cause an audit to be conducted within fifteen days;

   d) Submits to the liquidators the audit report approved by the general assembly and the minutes of the decision to amalgamate or divide or dissolv

፪ ኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ የሂሳብ ማጣራት ሥራውን የሚያዘው፡-

ሀ) ፪/፫ኛ አባላት የማፍረስ ተግባሩ እንዲከናወን የተስማሙበት ቃለጉባኤ እና የማፍረስ ማመልከቻ ሲደርሰው፤

ለ) የአባላት ቁጥር በሕግ ከተወሰነው ዝቅተኛ ቁጥር በታች መሆኑን በማስረጃ ሲያረጋግጥ፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ ውስጥ መግባቱንና በቀላሉ ከኪሳራ የማይወጣ መሆኑን ሲያምንበት፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከኅብረት ሥራ ማህበራት መርህና አላማ ውጪ ሲሰራ መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

ሠ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ አለመግባቱ ሲያረጋግጥ፣

ረ) በአንድ አመት ውስጥ በቋሚነት ያልተመዘገበ መሆኑን ሲያረጋግጥ መሆን አለበት፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ማጣራትና የመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የማፍረስ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ በደብዳቤ መላክ እና በጋዜጣም ማውጣት አለበት፤.

፬ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የደረሰውን የሂሳብ ማጣራትና የማፍረስ ውሳኔ ከተቃወመ በጠቅላላ ጉባኤና በሥራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ አስወስኖ በ ፲፭ ቀን ውስጥ ለአደራጅ መሥሪያ ቤቱ ማቅረብ አለበት፤

፭ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የመቃወሚያ ደብዳቤውን በ ፲፭ ቀን ውስጥ ለአደራጅ መሥሪያ ቤቱ ካላቀረበ የማፍረስ ውሣኔውና የሂሳብ ማጣራት ሥራው ተግባራዊ ይሆናል፤

፮ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ አሳማኝ የሆነ ምክንያት በማንኛውም ጊዜ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዳይፈርስ እና ሂሳብ እንዳይጣራ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ሊሰርዘው ይችላል፤

2. The Commission or the Winding up Office shall:
   a) When 2/3 of the members agree to carry out the dissolution process and upon receipt of the dissolution application;
   b) When he proves with evidence that the number of members is below the minimum number determined by law;
   c) When he believes that the cooperative society has entered into bankruptcy and cannot easily recover from bankruptcy;
   d) When he confirms that the cooperative society is working outside the principles and objectives of cooperative societies;
   e) When the cooperative society confirms that it has not started working within the specified period;
   f) It must be confirmed that it has not been permanently registered within one year.
3. Before making a decision to winding up the cooperative society's accounts and amalgamate or dissolute it, the decision given by the commission or the office must be sent to the cooperative society by letter and published in the newspaper;
4. If the cooperative society disagrees with the decision to verify and dissolve the accounts, it must make a decision in the general meeting and the management committee and submit it to the organizing office within 15 days;
5. If the cooperative society does not submit the objection letter to the organizing office within 15 days, the dissolution decision and the winding up will be implemented;
6. The commission or the office may at any time, for good cause shown, revoke the order of winding up and liquidation of the cooperative societ

፯. የሂሳብ ማጣራት ሥራው እንዲከናወን አግባብ ባለው በኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ከተወሰነ በኋላ የሂሳብ ማጣራት ተግባር በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ይከናወናል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ማጣራት ተቃዋሚ ካለ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከነምክንያቱ እንዲቀርብ በተከታታይ ለሁለት ወራት በጋዜጣና አመቺ መንገዶችን በመጠቀም ማስታወቅ አለበት፤

ለ) በማስታወቂያው መሠረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ ዕዳ ጠያቂዎች የሚያቀርቡትን ማስረጃዎች ዝርዝር በመመዝገብ የማጣራት ሥራ ይከናወናል፤

፰. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር መረጃዎችን ከሥራ አመራር ኮሚቴና ከቁጥጥር ኮሚቴ ርክክብ ይደረጋል፤ ዝርዝር መረጃዎችም የሚከተሉትን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት በዝርዝር የሚገልፅ ሆኖ ጥሬ ገንዘብ በእጅ እና በባንክ እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች እና መዛግብቶች ካሉ ዋጋቸውንና ዝርዝር ሁኔታቸውን የሚገልፅ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ለ) የሚሰበሰብ እና ተከፋይ ዕዳዎችን የሚያስረዱ ሰነዶች መኖራቸውን፤

ሐ) የባለ ዕዳዎችን ስም፣ አድራሻና ሥራ በዝርዝር የሚገልጽ እና ለዕዳዎቹ የተያዘ መያዣ ካለ ዝርዝሩን የሚገልጽ ሰነዶች ያዘጋጃል፤

7. After the appropriate commission or office decides that the winding up should be carried out, the winding up will be carried out in the following order:

a) If there is an objection to the winding up of the cooperative society's accounts, it must be announced in newspapers and by convenient means for two consecutive months to submit the reasons within one month;

b) Pursuant to the notification, a verification work will be done by recording the list of evidences presented by the debtors against the cooperative society.

8. Detailed information describing the state of the cooperative society will be handed over from the management committee and the control committee, details should also ensure that they meet the following:

a) Declaring the cooperative society's property in detail, cash in hand and in the bank, and other financial documents and records, if any, to make sure that they state their value and details;

b) That there are documents explaining the debts to be collected and paid;

c) Prepares documents detailing the names, addresses and occupations of the debtors and, if there is any security for the debts, detailing the details;

መ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ ዕዳ የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ስም፣ አድራሻና ሥራቸው እንዲሁም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ የሚጠይቁትን ገንዘብ መጠን የሚገልጹ ሰነዶች፤

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የኦዲት ሪፖርትና ሌሎች መረጃዎችን ኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ የሚያዘጋጀው ዝርዝር መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት እና ዕዳ በዝርዝር በመለየት ይሰበስባል፡፡

**፻፳፱ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ የማጣራት ሥራ አካሄድ</u>**

፩ በአዋጁ አንቀጽ ፶፮ እና፶ ፶፯ ስለ ሂሳብ ማጣራት የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሂሳብ ማጣራት ሥራ የሚካሄደው፡-

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነው የውህደት ወይም የመከፈል ልዩ ውሳኔ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ሲረጋገጥ በኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ሂሳብ አጣሪ ይመደባል፤

ለ) የሂሳብ አጣሪዎች ሂሳቡን በማጣራት ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፤

ሐ) ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የቀረበለትን የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት እና በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ቃለ ጉባኤ መሰረት በማድረግ ውህደቱ ወይም መከፈሉ እንዲፈጸም ያደርጋል፤

፪ የሂሳብ ማጣራት ሥራው ሲከናወን ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚኖረው ሕጋዊ ሰውነትና የሥራ እንቅስቃሴ፤

ሀ) የአንድ የኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ የሚጣራው በዚህ ደንብ አንቀጽ 129 በተጠቀሱት ምክንያቶች ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለዚህ የሂሳብ ማጣራት አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ እስከ መጨረሻው የሕጋዊ ሰውነት መብት እንዳለው ይቆጠራል፤

d) Documents stating the names, addresses and occupations of individuals or organizations seeking debt from the cooperative society as well as the amount of money they are requesting from the cooperative society;

e) Collects the cooperative society's audit report and other information by identifying the cooperative society's assets and liabilities in detail based on the list prepared by the commission or the office.

**129. <u>Process of Winding up of Cooperative Societies</u>**

1. Subject to what is mentioned in the articles 56 and 57 of the proclamation about the winding up, the winding up will be carried out:
   a) When it is confirmed that the special decision of the amalgamation or division of the general assembly does not cause damage, the commission or the office will appoint liquidator;
   b) The liquidators shall submit a detailed report to the commission or the office after verifying the accounts;
   c) The commission or the office shall make the amalgamation or payment based on the report of the liquidators submitted to it and the minutes of the special resolution of the general assembly;
2. The legal personality and business activities of any cooperative society when the accounting work is performed:
   a) The accounts of a cooperative society are audited for the reasons mentioned in article 129 of this regulation, and the cooperative society is considered to have the right of legal personality to the end for all the things necessary for this accounting winding up;

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የገባውን ግዴታ ለመወጣት እና የተጀመሩትን ሥራዎች እስከ የሚፈርስ ድረስ ማካሄድ ይችላል፤ ሆኖም ግን አዲስ ሥራ ለመጀመር አይችልም፤

ሐ) በአዲስ መልክ እንደገና ለመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን ነባር አባላት ስብሰባ ይጠራል፣

መ) የሂሳብ ማጣራቱ ሂደት እንደተጠናቀቀ ህልውናውን ያጣው ኅብረት ሥራ ማህበር ህልውናውን ያጣ መሆኑን ኮሚሽኑ በጋዜጣና አግባብ ባላቸው የመገኛኛ ዘዴዎች በኩል ያሳውቃል፡፡

**፻፴ ስለ የማይከፋፋል የኅብረት ሥራ ማህበራት ንብረት፤**

፩ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ለአባላት በገዙት ዕጣ መጠን እና በተሳትፎ መሠረት ከሚከፋፈለው ትርፍ ክፍፍል ውጭ ለመጠባበቂያ፣ ለማኅበራዊ አገልግሎት ፣ ለትምህርትና ስልጠና የተመደበ ገንዘብ እና በስጦታና በውርስ የተገኘ ገንዘብ የማይከፋፈል የጋራ ገንዘብ ይሆናል፤

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕዳዎች ከመከፈላቸው በፊት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት አይከፋፈልም፤

፫ ለዕዳ ጠያቂዎች ክፍያ ተፈጽሞ ካልተጠናቀቀ ወይም ገንዘባቸውን ላልወሰዱ ባለገንዘቦች የሚከፈል ተብሎ ካልተቀመጠ በስተቀር የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ወይም ንብረት ለአባላት አይከፋፈልም፤

፬ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በውህደት ወቅት የነበረው የማይከፋፈል የጋራ ንብረት በውህደት ለተቋቋሙት አዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማይከፋፈል የጋራ ንብረትነት ተመዝግቦ ይተላለፋል፤

b) The cooperative society can fulfill its obligations and carry out the started operations until its dissolution, however, it cannot start a new work;

c) Call a meeting of existing members who wish to reorganize;

d) Once the accounting verification process is completed, the commission will inform through the newspaper and appropriate contact methods that the cooperative society that has lost its existence.

**130 Indivisible Asset of Cooperative Societies**

1. According to the bylaws of the cooperative society, apart from the profit distribution distributed to the members according to the share size and participation, money allocated for reserves, social services, education and training and money obtained from gifts and inheritance will be undistributed common funds;
2. Subject to the provisions of sub article (1) of this article, the asset of the cooperative society shall not be distributed before the debts of the cooperative society are paid;
3. The money or asset of the cooperative society shall not be distributed to the members unless the payment to the creditors has been completed or it has been set aside to be paid to the creditors who have not received their money;
4. The indivisible common property of any cooperative society at the time of merger shall be registered and transferred as indivisible common property to the new cooperative societies established by amalgamation;

፭. የማይከፋፈለውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ካፒታል ወደ ወል ንብረትነት ይመድባል፤

፮. አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር በህጉ መሰረት እንዲፈርስ ሲወሰንና ንብረቱ ተጣርቶ ለክፍፍል በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቶች አይከፋፈሉም፡

ሀ) በየአመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ የተቀነሰ የመጠባበቂ ሂሳብ ገንዘብ፤

ለ) በስጦታ፣ በውርስ ወይም በሽልማት የተገኘ ንብረት፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማጠነከርና ለማበረታታት ሲባል ከመንግስት በነፃ የተገኘ መሬት ወይም ህንፃ ወይም ማንኛውም ቋሚ ንብረት ከሆነ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ለረዥም ወይም ለአጭር ጊዜ በአደራ እንዲያስተዳድረው የተሰጠ ንብረት፤

ሠ) እንዳይከፋፈል በህግ ክልከላ የተደረገበት ንብረት ከሆነ፡፡

## ፻፴፩. ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት እና ክፍያ ስለመፈፀም

፩. አባላት ኅብረት ሥራ ማህበራቸውን በማንኛውም ሁኔታ የማፍረስ መብት ቢኖራቸውም የሦስተኛ ወገኖች ወይም አበዳሪዎች እና ተበዳሪዎች ተቃውሞ ከተነሳ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የመፍረስ ጥያቄውን ከህብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በመሆን መርምሮ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ሊያሰጥበት ይገባል፤

5. The indivisible property and money of cooperative societies cannot be used in any way for the members or any other party for loan or debt payment or debt settlement or for gift or reward or assistance and so on;
6. Allocates the indivisible capital of the cooperative society to common property;
7. When a cooperative society is decided to be dissolved according to the law and the assets are sorted and prepared for distribution, the following assets of the cooperative society will not be divided:
   a) Amount of reserve account deducted from net profit every year;
   b) Property acquired by gift, inheritance or prize;
   c) If it is land or building or any fixed asset obtained free of charge from the government in order to strengthen and encourage cooperative societies;
   d) Property entrusted to cooperative societies for long or short term management;
   e) If it is property whose distribution is prohibited by law.

## 131. Calling On and Paying Creditors

1. Although members have the right to dissolve their cooperative society under any circumstances, if objections are raised by third parties or creditors and debtors, the commission or the office must examine the request for dissolution together with the cooperative society and make a decision at the general assembly;

፪. የንብረት ክፍፍል ለማድረግ የሂሳብ ማጣራት ሥራው ሲጀመር የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሕልውናውን የሚያጣ መሆኑን በመግለፅ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለሁለት ተከታታይ ወራት በጋዜጣና አመች በሆነ መንገድ ማስታወቂያ ይወጣል፤

፫. ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ገንዘብ ጠያቂ አካላትና ህልውናውን ማጣቱን ያልተስማሙ አባላት ካልቀረቡ ወይም በወቅቱ ካልወሰዱ ንብረቱ አዲስ በተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበር በዕዳ ዋስትናነት ይቀመጣል፤

፬. በሚወጣው ማስታወቂያ ውስጥ የመጀመሪያው የጥሪ ማስታወቂያ ካወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ ተቃዋሚ ካልቀረበ ማኛውም ሰው የንብረት ክፍፍሉን የመጠየቅ መብት እንደሌለው መገለጽ አለበት፤

፭. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መዛግብት ውስጥ ለተጻፉ ገንዘብ ጠያቂዎች ወይም በሌላ መልኩ ለሚታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች በሪኮማንዴ ደብዳቤዎች የጥሪ ማስታወቂያቸው በቀጥታ መላክ አለበት ለሌሎች ግን ግልጽ በሆነ በማስታወቂያዎች ያሳውቃል፤

፮. በሂሳብ አጣሪዎች የተለየውን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዕዳ ለባለ ገንዘቦች እንዲከፋፈል ይደረጋል፤ ሆኖም ዕዳው እንደ ገና ወደ የሚደራጀው የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲተላለፍ የገንዘብ ጠያቂዎችን ፍላጎት በመጠየቅ ሲስማሙ በጠቅላላ ጉባኤ ያስወስናል፤

2. At least once a month for two consecutive months, an announcement will be published in a newspaper and in a convenient way, stating that the cooperative society will cease to exist when the audit work begins for the distribution of property;
3. If the creditors and members who do not agree with the loss of existence do not appear or take it within one month from the date of publication of the notice, the property will be kept as debt security by the newly established cooperative society;
4. In the notice issued, it must be stated that no person has the right to claim the property division if no opposition is presented within two months from the date of the first notice of summons;
5. Notice of summons shall be sent directly to creditors registered in the records of the cooperative society or to creditors known in any other manner by recommended letters, but to others it shall be notified by public notices;
6. The separate debts of the cooperative society will be distributed to the shareholders by the liquidators, however, the debt will be transferred to the reorganizing cooperative society after asking the creditors' interest and agreeing to it at the general meeting;

፯. ህልውናውን እንዲያጣ እና ሂሳቡ እንዲጣራ ውሳኔ የተሰጠበት የኅብረት ሥራ ማህበር ንብረት ክፍፍሉ ከመፈፀሙ በፊት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባላትና ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር በነበረው ግንኙነት ያለበትን ዕዳና የሚሰበሰብ ሂሳቡን የማጣራት ሥራ የሂሳብ አጣሪዎች ኃላፊነትና ግዴታ ይሆናል፡፡

፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሰረት የሂሳብ አጣሪዎች፡-

ሀ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ካልተከፈላቸው ወይም የእነርሱን ገንዘብ ለመክፈል አስፈላጊ የሆነው የገንዘብ መጠን ካልተቀመጠ በስተቀር አጣሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ለማከፋፈል አይችሉም፤

ለ) ለገንዘብ ጠያቂዎች በወቅቱ ያልተከፈለ የገንዘብ መጠን ለፍርድ ቤት አቅርቦ በማስወሰን በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት መቀመጥ አለበት፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ላልፈፀማቸው ግዴታዎች ወይም በክርክር ላይ ላሉት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ግዴታዎች ክፍያ የሚውል ተማጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወይም ገንዘብ ተይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

**፻፴፪ <u>የመጨረሻ ሂሳብ ሚዛን ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤ ስለማቅረብ</u>**

፩. የሂሳብ አጣሪዎች ማንኛውንም የማጣራት ሥራ ከፈጸሙ በኋላ የመጨረሻ ሂሣብ ሚዛን ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ስለ ክፍፍሉ ውሣኔ ያሰጣሉ፤ በተሰጠው ልዩ ውሣኔም መሠረት ያከፋፍላሉ፤

፪. በአዲስ መልክ እንደገና ለመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን ነባር አባላት ስብሰባ ይጠራል፤

7. Before the division of the assets of a cooperative society which has been decided to lose its existence and to have its accounts winding up, it will be the responsibility and duty of the auditors to verify the debts and accounts that the cooperative has with the members and other creditors;

8. Pursuant to sub article (7) of this article, liquidators shall:

a) Liquidators shall not disburse the funds of the cooperative society unless the creditors of the cooperative society have been paid or the amount necessary to pay them has been deposited;

b) The amount of money that has not been paid on time to the creditors should be submitted to the court and set according to the decision;

c) A reasonable amount of guarantee or money shall be reserved for the payment of the obligations that the cooperative society has not fulfilled or the obligations of the cooperative society that are in dispute.

**132. <u>Submitting Final Balance Sheet to General Assembly</u>**

1. After performing any verification work, the liquidators present the results of the final account balance to the general assembly and make a decision about the distribution, they will distribute according to the special decision;
2. Calls a meeting of existing members who wish to reorganize;

፫ አዲስ በሚደራጀው ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሆነው መቀጠል ለማይፈልጉ ወይም ለማይችሉ አባላት በተደለደለው መሠረት ድርሻቸውን የሚያገኙበትን የጊዜ ገደብና ሁኔታ ለጠቅላላ ጉባኤው ያስወስናል፣ሆኖም የጊዜ ገደቡ ከአንድ ዓመት መብለጥ የለበትም፤

፬ ኮሚሽኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ እንደገና ለመመዝገብ የማይችሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከመዝገብ በመሠረዝ በጋዜጣ ያሳውጃል፤

፭ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና ለመመዝገብ ያልፈለጉና ዕዳ ያለባቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዕዳቸውን ሳይከፍሉ በሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር ስም ሊመዘገቡ አይችሉም፡፡

## ፻፴፫ የተጣራው ሂሳብ አከፋፈል ቅደም ተከተል

የሂሳብ አጣሪዎች ማንኛውንም የማጣራት ሥራ ከፈጸሙ በኋላ ለማከፋፈል የመጨረሻ ሂሳብ ሚዛን ውጤት ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ስለ ክፍፍሉ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማድረግ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት የማከፋፈሉን ሥራ ከዚህ በታች ባለው ቅደም ተከተል መፈጸም ይኖርበታል፤

፩ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅጥር ሠራተኞች ደሞዝ ይከፍላ፤ የተረፈው ገንዘብ ለሁሉም ሰራተኞች የማይበቃ ከሆነ እንደ ደሞዛቸው መጠን እየታሰበ ቀሪው ገንዘብ መከፋፈል አለበት፤

፪ ማንኛውም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈለግ የመንግስት ዕዳ ይከፈላል፤

፫ ለውጭ ገንዘብ ጠያቂዎች በቅደም ተከተላቸው እና የክፍያ ጊዜያቸው ለደረሰው ቅድሚያ በመስጠት ይከፍላል፤

፬ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከአባላት ለተበደረው ዕዳ ይከፍላል፡፡

3. The general assembly shall determine the time limit and conditions for the members who do not want or are unable to continue being members of the newly organized cooperative society to receive their shares, but the time limit shall not exceed one year;
4. The commission or the office shall announce in the newspaper the deregistration of cooperative societies that cannot be re-registered;
5. Cooperative societies that do not wish to re-register within one year and have debts cannot be registered under the name of another cooperative society without paying their debts.

## 133. Net Payment Order

After the liquidators have done any verification work, they should present the results of the final account balance to the general assembly to make a decision about the distribution;

1. Pay wages to the employees of the cooperative society, if the remaining amount is not enough for all employees, the remaining amount should be distributed according to their salary;
2. Any government debt due from the cooperative society shall be paid;
3. Pays foreign creditors in their order and due date on a first-come, first-served basis;
4. The cooperative society pays the debts owed to the members;

፭ ለዕጣ ግዢ ለተከፈለው ገንዘብ ይከፍላል፤ ሙሉ ለሙሉ መክፈል ካልተቻለ ያለውን ገንዘብ ባለው እጣ መጠን እየተሰላ መከፋፈል አለበት፤

፮ ለዲቪደንድ ክፍያ በዕጣ መጠን ላይ በመመሰረት ይከፋፈላል፡፡

**፻፴፬ ማህበርን ከመዝገብ ስለመሰረዝ**

፩ የሂሳብ አጣሪዎች የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ እንደፈጸሙ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የምዝገባ የምስክር ወረቀትና ሂሳብ የተጣራበትን ሪፖርት አዘጋጅተው ለሾማቸው ወይም ለሰየማቸው ኮሚሽን ወይም ጽህፈት ቤት ያቀርባሉ፤

፪ የሂሳብ ማጣራት ሥራውን ያዘዘው ኮሚሽን ወይም ጽህፈት ቤት የሚከተሉትን ያከናውናል፡-

ሀ) በማናቸውም ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሰነዶች የመጨረሻ ገጽ ላይ “ሕልውናውን ያጣ ኅብረት ሥራ ማህበር” በማለት ምልክት አድርጎ ይፈረምበታል፤

ለ) ሥራ ላይ ላልዋሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የገንዘብ ነክ ሰነዶች ላይ በእያንዳንዱ ገጽ “ታሽጓል” ወይም “አይሠራም” የሚል ምልክት ያደርግበታል፤

ሐ) የሂሳብ አጣሪዎች ሂሳብ ያጣሩበትን ሪፖርት እና የኅብረት ሥራ ማህበራቱን የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የተለያዩ ማህተሞችና ቃለ ጉባኤ በመያዝ ለሾማቸው ወይም ለሰየማቸው ኮሚሽን ወይም ጽህፈት ቤት ማስረከብ አለባቸው፤

መ) ሕልውናውን ስላጣው ኅብረት ሥራ ማህበር ሰነዶችና መዛግብት አቀመጣጥ ውሣኔ ይሰጣል፤

5. Pays for the money paid for the purchase of shares, if it is not possible to pay in full, the available money must be divided according to the amount of the share;
6. Dividends are distributed based on share size.

**134. Cancellation of a Society from Register**

1. Once the liquidators have completed the audit, they will prepare the cooperative society's registration certificate and the audited accounts report and submit it to the commission or office designated by them;
2. The commission or office that ordered the winding up shall perform the following:
   a) Sign the last page of any cooperative society's documents as "dissolute cooperative society";
   b) Marks “sealed” or “not operational” on every page of the financial documents of the cooperative society that are not in operation;
   c) Account liquidators must submit the audit report and the cooperative society's registration certificate, various seals and minutes to the commission or office appointed by them;
   d) Gives a decision on the disposition of documents and records of the cooperative society that has lost its existence;

መ) ሕልውናውን ስላጣው ኅብረት ሥራ ማህበር ሰነዶችና መዛግብት አቀመጣጥ ውሣኔ ይሰጣል፤

ሠ) የፈረሰውን ኅብረት ሥራ ማህበር የማይከፋፈል ገንዘብ ወደ የኅብረት ሥራ ፈንድ እንዲገባ ያደርጋል፤

ረ) ኅብረት ሥራ ማህበሩን ከመዝገብ ይሰርዛል፤

ሰ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ህልውናውን ያጣ መሆኑን በመግለጽ በጋዜጣና አመቺ መንገዶችን በመጠቀም ለህዝብ ማስታወቅ አለበት፤

፫ የሂሳብ ማጣራት ሥራው ተጠናቆ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከመዝገብ መሠረዙ ከተረጋገጠ በኋላ በሂሳብ አጣሪዎች እጅ በሥራ ምክንያት የገቡት የማህበሩ ሰነዶችና መዛግብት እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በሚወስነው ቦታ ለ10 ዓመታት ይቀመጣሉ፡፡

**፻፴፭ የማይከፋፈል ንብረት አቀማመጥና አስተዳደር**

፩ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በእንቅስቃሴ በነበሩበት ወቅት በስማቸው በመጠባበቂያ ሂሳብ፣ በስጦታ፣ በውርስና ከመንግስት የተገኘ ድጋፍ ማህበሩ ሲፈርስ የማከፋፈል ንብረት ስለሆነ በቀጣይ ለሚቋቋሙት እና በሥራ ላይ ለሚገኙት የኅብረት ሥራ ማህበራት የማስፋፋት ሥራ ይውላል፤

፪ የማይከፋፈል ንበረትን ለማስተዳደርና በሥራ ላይ ለማዋል የኅብረት ሥራ ፈንድ ኮሚሽኑ በሚወስነው አካል ይቋቋማል፤

፫ የማይከፋፈሉ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቶች ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይረው በሚቋቋመው ኅብረት ሥራ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ይሆናል፤

e) Cause the indivisible funds of the dissolved cooperative society to be deposited into the cooperative society fund;

f) Cancelled the cooperative society from the register;

g) It must announce the fact that the cooperative society has lost its existence to the public through newspapers and other convenient means;

3. After the winding up is completed and it is confirmed that the cooperative society has been cancelled, the documents and records of the cooperative society and other information that came into the hands of the liquidators will be kept for 10 years in the place decided by the commission or the office.

**135. Disposition and Administration of Indivisible Asset**

1. During the time when the cooperative society was in operation, the reserve account, gift, inheritance and support received from the government in their name is the property to be distributed when the cooperative society is dissolved, so it will be used for the expansion of the cooperative societies that are established and in operation;
2. To administer and implement the indivisible asset, a cooperative society fund shall be established by a body determined by the commission;
3. The indivisible assets of the cooperative society shall be converted into cash and credited to the cooperative society fund account to be established;

፬ የኅብረት ሥራ ፈንድ እንዲመራ ኃላፊነት የሚሰጠው አካል ሂሳቡን ያንቀሳቅሳል፤ ይቆጣጠራል፤ በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ያውላል፤

፭ ከመንግስት በነጻ የተሰጠ መሬት ወይም ንብረት ለሚመለከተው የመንግስት አካል ይመለሳል፤ ሆኖም በመሬቱ ላይ ወይም በንብረቱ ላይ ለተካሄደው ግንባታ ወይም ማስፋፊያ የዋለው ገንዘብ ለፈረሰው ማህበር ተመላሽ ሆኖ በንብረት ክፍፍሉ ሂሳብ ውስጥ ይገባል፡፡

**፻፴፮ የክርክር አወሳሰን**

በአባላት መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ አግባብ ያላቸው የግልግልና ሽምግልና ህጎችን በመጠቀም አባላት ልዩነታቸውን መፍታት ይችላሉ፡፡

**፻፴፯ ማህበራትን ስለማጠናከርና ማዘመን**

፩ ኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ ማህበራትን ለማጠናከር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡-

ሀ) የአደረጃጀት፣ አመራር እና አሰራር ሥርዓት ማጠናከር፤

ለ) የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን ሥርጸት አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነት ማሳደግ፤

ሐ) የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ማስፈን፤

መ) አባላት ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤

ሠ) የፋይናንስ አቅም መገንባት፤

ረ) ንብረት አስተዳደር ማጠናከር፤

ሰ) የቁጠባ ባህልና መጠን በማስፋፋት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር፤

ሸ) በኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የሚኖረውን የእርስ በርስ ግንኙነት ማጠናከር፤

4. The person entrusted with the administration of the cooperative society fund shall operate the account, controls; it will be implemented in an appropriate manner;
5. Land or property given free of charge by the government shall be returned to the relevant government body. However, the money spent on the construction or expansion of the land or the property will be returned to the dissolved society in the property division account.

**136. Dispute Resolution**

When disputes arise between members, members can resolve their differences using the appropriate arbitration and alternative dispute resolution laws.

**137. Strengthening and Updating Cooperative Society**

1. The Commission or its office shall carry out the following activities to strengthen the societies:
   a) Strengthening the system of organization, leadership and operation;
   b) Increasing the accessibility of cooperative society extension system service delivery;
   c) Establishing a good governance procedure;
   d) Increase member participation and benefit;
   e) Building financial capacity;
   f) Strengthening property administration;
   g) Strengthening cooperative societies by expanding the culture and scale of savings;
   h) To strengthen the relationship between cooperative societies;

ቀ) የመሰረተ ልማት ግንባታና አስተዳደር ማጠናከር፤

በ) የመረጃ ሥርዓት ማጠናከር፤

፪ የማህበራት አሰራር አዋጭ እና ጊዜ ቆጣቢ በሆኑ ዘመናዊ በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ በማድረግ ፍትሃዊና ቀልጠፋ የሆነ አገልግሎትን ለአባላት ተደራሽ እንዲያደርጉ መሰራት አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## የኅብረት ሥራ ማህበራት ግንኙነትና የድጋፍ አግባብ

### ፻፴፰ ከአባላት ጋር ግንኙነትና ድጋፍ

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያደርጓቸው ማናቸውም እንቅስቃሴዎቻቸው ከአባላት፣ ከኮሚሽኑ ወይም ከጽህፈት ቤቱ፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከአቅም ገንቢዎች እና ሌሎች አካላት ጋር የተለያዩ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከአባላት ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ግንኙነት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡-

ሀ) በዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ፤

ለ) በሪፖርት አቀራረብና መረጃ አሰጣጥ፤

ሐ) በትምህርትና ስልጠና አገልግሎት፤

መ) ኤክስቴንሽን አገልግሎት፤

ሠ) በምርትና ፋይናንስ የግብይት አገልግሎት፤

ረ) የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት፤

ሰ) በልምድ እና ተሞክሮ ልውውጥ፤

i) Strengthening infrastructure construction and management;

j) Information system strengthening;

2. Societies should be supported by efficient and time-saving modern technology to make fair and efficient services accessible to members.

## PART TEN

## COOPERATIVE SOCIETIES COMMUNICATION AND SUPPORT

### 138. Communication and Support with Members

1. Cooperative societies may have different relationships with members, the commission or the office, stakeholders, capacity builders and other bodies in any of their activities;

2. The types of communications that cooperative societies have with their members are defined in their bylaws, and they can establish relations mainly around the following issues:

a) In planning and implementation;

b) Reporting and information delivery;

c) Education and training services;

d) Extension Service;

e) Marketing services in products and finance;

f) Accounting system;

g) Exchange of experience and knowledge;

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቅዱት ማንኛውም እቅድ የአባላትን ፍላጎት ዳሰሳ መሰረት ያደረገ ሆኖ ከአባላት አቅም በላይ የሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት ላይ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት፤

፬ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የዋና ዋና ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፤

፭ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሆነ ለማንኛውም አካል የሚቀርብ ሪፖርት እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት ዓይነት የሚለያይ ሆኖ ቢያንስ በሚከተሉት ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡-

ሀ) የአባላት የግብይት ተሳትፎ፤

ለ) የምርት ግብይት አፈጻጸም፤

ሐ) የግብርና ምርት መሳደጊያ ግብዓቶች አቅርቦትና ስርጭት፤

መ) የሒሳብ ሪፖርት፤

ሠ) የፋይናንስ አቅርቦት፤

ረ) የብድር እና ዕዳ አመላለስ፤

ሰ) የፍጆታ ምርት አቅርቦትና ስርጭት፤

ሸ) ያጋጠሙ ችግሮች፤

ቀ) በተመረጡ ሌሎች ጉዳዮች፤

፮ የኅብረት ሥራ ማህበራት የዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም መረጃዎችን በየግማሽ ዓመቱ አባላት ሊያዩ በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ይለጥፋሉ፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላቱ ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራቸው ተገቢውን መረጃ በወቅቱ እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርበታል፤ የተለያዩ ሚዲያዎች በመጠቀም መረጃ ሊሰጥ ይችላል፤



3. Any plan planned by the cooperative societies should be based on a survey of the needs of the members and focused on solving social and economic problems beyond the capacity of the members;
4. The report on the performance of the main activities plan of the cooperative society must be presented and approved by the management committee or board every month;
5. According to sub article (4) of this article, a report submitted to the management committee of the cooperative society or to any body, which varies according to the type of cooperative society, should at least focus on the following activities:
   a) Members' marketing participation;
   b) Product marketing performance;
   c) Supply and distribution of agricultural production inputs;
   d) Financial report;
   e) Financial provision;
   f) Loan and debt settlement;
   g) Supply and distribution of consumer products;
   h) Problems encountered;
   i) In selected other matters;
6. Cooperative societies shall post information on the performance of major activities every six months in places where members can see;
7. The cooperative societies must ensure that its members get timely information about their cooperative society, information can be provided using a variety of media;

፰. አባላት እና ሌሎች አካላት የአፈጻጸም መረጃ በጠየቁ ጊዜ መረጃ ማግኘት አለባቸው፤

፱. በየወሩ በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ የጸደቀ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፤

፲. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ መግለጫዎችን በወቅቱ በማዘጋጀት የሀብትና ዕዳ ሁኔታ ለአባላት ግልጽ ማድረግ አለባቸው፤

፲፩. ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የኅብረት ሥራ ጽንሰ ሃሳብ፣ ጠቀሜታና ፋይዳ፣ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት እና ሌሎች በጥናት በተለዩ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፤

፲፪. አባላት ምርትን በጥራት፣ በብዛት እና በወቅቱ ለኅብረት ሥራ ማህበራት ማቅረብ አለባቸው፤

፲፫. የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የግብይት አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚከተሉት ግዴታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) አባላት ለምርትና አገልግሎት የሚፈልጉትን ፋይናንስ የብድር አገልግሎት ማመቻቸት፤

ለ) ለአባላት የገበያ መረጃ መስጠት አለባቸው፤

ሐ) ለአባላት በምርት ጥራት እና በአጠቃላይ የግብይት አሰራር ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤

መ) ጥራትን መሰረት ያደረገ ክፍያ ሥርዓት መተግበር፤

ሠ) በምርት ዋጋ ትመና ላይ ለአባላት ግልጸኝነትን መፍጠር

ረ) የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፤

ሰ) ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ፤

8. Members and other parties should have access to performance information upon request;
9. Every month, a plan implementation report approved by the management committee or board must be submitted to the commission or the office;
10. They should prepare the financial statements of the cooperative society in a timely manner and make the status of assets and liabilities clear to the members;
11. Cooperative society are responsible for providing awareness training to members on the concept, importance and benefit of cooperative societies, their activities and other basic issues identified by research;
12. Members must provide produce to cooperative societies in quality, quantity and time;
13. Cooperative societies must fulfill the following obligations in order to benefit from the marketing services for their members:
    a) Facilitating credit services for the financing that members need for products and services;
    b) Provide members with market information;
    c) Create awareness among members on product quality and general marketing practices;
    d) Implementing a quality-based payment system;
    e) To create transparency for members on product pricing;
    f) Providing consumer products at reasonable prices based on the needs of members;
    g) Add value to the product and provide it to the market;

ሸ) የአባላትን ምርት በማስተዋወቅ እና የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት ምርቱን መሸጥ፤

ቀ) የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ምርት በስፋት መሰብሰብ፡፡

**፻፴፱ በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒዬን መካከል ስለሚኖር የግንኙነትና የድጋፍ አግባብ**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የዋና ዋና ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

፪ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች አገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማዘመን የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ማሟላት አለባቸው፤

፫ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አመራሮች የአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችን መደገፍ፣ ማብቃት፣ ልምድን ማካፈል፣ የአመራርነት ክህሎት የሚያገኙባቸውን ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር አለባቸው፤

፬ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን፣ ቅርጫፍችን እና መሸጫ ሱቆችን በዕቅድ አፈጻጸም እና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የባለሙያ ድጋፍና ክትትል ማድረግ አለባቸው፤

፭ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዕቅድ ዝግጅትም ሆነ በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ላይ አባላትን በንቃት ማሳተፍ አለበት፤

፮ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ወቅታዊ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብና በመተንተን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በማቅረብ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የምርትና አገልግሎት ግብይት እንዲፈጸም ማድረግ አለባቸው፤

h) Promote member's product and sell the product by expanding market access;

i) Mass gathering of quality products.

**139. Communication and Support Between Primary Cooperative Societies and Unions**

1. The Union of Cooperative society must notify the member primary cooperative societies in writing of the implementation report of the main activities plan every month;
2. Cooperative society unions need to develop various infrastructures to modernize their service delivery;
3. Union leaders of cooperative society must support, empower, share experience, and create favorable conditions for the leaders of member primary cooperative society to acquire leadership skills;
4. Cooperative society unions must provide expert support and supervision to member primary cooperative societies, branches and shops at least once a month in planning implementation and service delivery;
5. Any cooperative society must actively involve members in planning and evaluation of plan performance;
6. Cooperative society unions must collect and analyze current various information and provide it to the member's primary cooperative societies so that information-based marketing of products and services can be done;

፯. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒኖች የፋናንስ አቅም ለሌላቸው አባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎችን መቅጠር መደገፍ እንዲሁም በጀት በመመደብ ሂሳባቸውን ኦዲት ማስደረግ አለባቸው፤

፰. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማቅረብ እና የተለያዩ ዘመናዊ አሰራር መጠቀም የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት ይኖርባቸዋል፤

፱. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**፻፵ <u>በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን እና ዩኒዬን መካከል ስለሚኖር የግንኙነት እና የድጋፍ አግባብ</u>**

፩. የኅብርት ሥራ ፌዴሬሽን ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት አጋዥ የሆኑ ፕሮጀክትና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ሀብት በማፈላለግ ድጋፍ ያደርጋል፤

፪. የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ለሚሰጧቸው ስልጠናዎች ምቹ የስልጠና ቦታዎችን እንዲያገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፫. የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን የውጭ ሀገር ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በመቀመር በአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባራዊ እንዲደረግ ይደግፋል፤

፬. የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማመንጨት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች እና መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲተገብሩ ድጋፍ ያደርጋል፤

7. Cooperative society unions should support the hiring of accounting experts for member primary cooperative societies that do not have financial capacity, and audit their accounts by allocating budgets;
8. Union of cooperative society should provide new technologies that are important for the development of member's primary cooperative society and establish a system where they can use various modern methods;
9. The union of cooperative societies provides professional support to member primary cooperative societies in the annual inventory of assets.

**140. <u>Communication and Support between the Federation of Cooperative Societies and the Union</u>**

1. Federation of cooperative societies supports the development of member cooperative societies by designing projects and programs and finding resources;
2. Cooperative societies will provide the necessary support for the union to find suitable training places for their training;
3. Federation of cooperative societies supports the implementation of foreign experiences and practices by member cooperative societies;
4. Federation of cooperative societies supports cooperative society unions and primary cooperative societies to develop and implement new technologies;

፭ የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የግብርና እና የኢንዱስትሪ የፍጆታ ምርቶችን በጅምላ እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፮ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ጥናትና ምርምር ከሚያደርጉ አካላት ጋር በመቀናጀት በኅብረት ሥራ ማህበራት ጉዳይ ላይ ጥናትና ምርምር እንዲያካሂዱ ድጋፍ ያደርጋል፤

፯ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ሰራተኛ የሂሳብ ዝርጋታ አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣሉ፤

፰ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን በጀት በመመደብ የአባል መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግ ድጋፍ ያደርጋሉ፤

፱ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ለአባል ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዕድገት ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፲ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ በማካሄድ ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ግልጽ በማድረግ የግንኙነት አግባቡን የተጠናከረ ያደርጋል፡፡

**፻፵፩ <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የኮሚሽኑ ወይም የጽህፈት ቤቱ ግንኙነት</u>**

ኮሚሽኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ግንኙነት በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

5. Based on the needs of the members, it creates favorable conditions for the supply of agricultural and industrial consumption products in bulk and at reasonable prices;
6. Federation of cooperative society cooperate societies with research and research bodies and supports them in carrying out research on the issue of cooperative societies;
7. Federation of cooperative society provide support to member primary cooperative society with accountants' accounting services;
8. Federation of cooperative societies supports the audit of the accounts of member primary cooperative societies by allocating a budget;
9. Union of cooperative societies or the federation of cooperative societies adapts and implements new technologies that are important for the development of cooperative societies for its members;
10. Union of cooperative societies or the federation of cooperative societies shall conduct an annual inventory of assets and make it clear to member cooperative societies and strengthen communication.

**141. <u>Cooperative Societies and Communication of the Commission or the Office</u>**

Communication between the commission or the office and the cooperative societies will be as follows:

፩ የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በኀብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንባቸው የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት በዕቅድ ዝግጅት፣ በአደረጃጀትና አሰራር፣ በሂሳብ፣ ኦዲት፣ ህግ አገልግሎትና ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ድጋፍና ክትትል፣ በግምገማና ግብረ- መልስ ሪፖርት፣ በቁጥጥር እና በመረጃ ልውውጥ ዙሪያ፤

፪ ማንኛውም ኀብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀ እቅድ እና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በወቅቱ በማቅረብ፤

፫ ለኀብረት ሥራ ማህበራት በዕቅድ ትግበራ እና በሪፖርት ዝግጅት ላይ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ፤

፬ ኀብረት ሥራ ማህበራት የተሰማሩበትን የሥራ መስክ እና ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ መሰረት ያደረገ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ኀብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር፤

፭ ኀብረት ሥራ ማህበራት ህግና ሥርዓት ተከትለው እንዲቀሳቀሱ ጠንካራ የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት ዘርግቶ በመደገፍ፤

፮ በኀብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የመረጃ ሥርዓት ግንባታ እንዲጠናከር ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ፤

፯ የህብረት ስራ ማህበራት የሚጠይቁትን የውሃ፣ የመብራት ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችሉ ድጋፎችን በማድረግ፤

፰ የኀብረት ሥራ ማህበሩን መሰረታዊ መረጃ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በመቀበል፣ በማጠናከርና በማደራጀት፤

፱ ለምርትና አገልግሎት፣ ለግብይት እና ለኀብረት ሥራ ማህበራት እድገት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመስጠት፤

1. Types of communication they have are defined by the bylaws of cooperative societies, mainly in planning, organization and operation, accounting, auditing, legal service and qualification assessment, support and monitoring, evaluation and feedback report, control and information exchange;
2. Any cooperative society by submitting a plan approved by the general assembly and a report on the implementation of the plan to the commission or the office in a timely manner;
3. Providing professional support to cooperative societies in plan implementation and report preparation;
4. Strengthening cooperative societies by providing support and monitoring based on the field of work they are engaged in and their level of performance;
5. By establishing a strong support system for cooperative societies to operate according to law and order;
6. By providing professional support to strengthen the construction of information systems in cooperative societies;
7. By providing subsidies that enable cooperative societies to obtain the water, electricity or other services they require;
8. Receiving, consolidating and organizing the cooperative society's primary information at least once a year;
9. Providing information necessary for the development of products and services, marketing and cooperative societies;

፲ የኅብረት ሥራ ማህበራት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ዓመታዊ እቅዳቸውን በማሳወቅ እና የዋና ዋና ተግባራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ ለኮሚሽኑ ወይም ለጽህፈት ቤቱ በጽሑፍ በማቅረብ፡፡

**፻፵፪ ኅብረት ሥራ ማህበራት እርስ በርስ የሚኖራቸው ግንኙነት**

፩ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር የዓላማ፣ የመርህ እና እሴት አንድነትን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡-
   ሀ) በቴክኒካል ድጋፍ፣
   ለ) በአሰራርና አመራር ልምድ ልውውጥ፣ እርስ በርስ በመማማር፣
   መ) በቅንጅት በመሥራት፣
   ሠ) በፋይናንስ ትስስር፣
   ረ) በግብይት ትስስር፣
   ሰ) በመረጃ ልውውጥ እና
   ሸ) ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የርስ በርስ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

፪ አምራች እና የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት በእቅድ ዝግጅት ሂደት መረጃ የመለዋወጥ፣

፫ አምራች እና የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት እቅድ አፈጻጸማቸውን በጋራ የሚገመግሙበት ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ በማድረግ፣

፬ የኅብረት ሥራ ማህበራት የጋራ የምክክርና የውይይት ፎረም በማዘጋጀት የጋራ ተጠቃሚነትን በማሳደግ፣

፭ አምራችና ሸማች ኅብረት ማህበራት በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመረኮዘ የጋራ ዓላማ፣ መርህ እና ዕሴትን መሰረት ያደረገ፣ የመተጋገዝ ግንኙነት፣

10. Cooperative societies by notifying their annual plan at the beginning of the fiscal year and submitting a written report on the implementation of the main activities plan to the commission or the office every month.

**142. Communication of Cooperative Societies**

1. Types of relationships that cooperative societies have will be defined in their bylaws, mainly based on the unity of objective, principles and values with other cooperative society in the following matters:
   a) Technical support;
   b) Exchange of experience in operation and management,
   c) Learning from each other;
   d) By working in coordination;
   e) In financial connection;
   f) Through marketing links;
   g) Information exchange; and
   h) They should have mutual relations regarding other matters.
2. Producer and consumer cooperative societies exchange information in planning process;
3. By developing and implementing a system where producer and consumer cooperative societies plan to jointly evaluate their performance;
4. By setting up a joint consultation and discussion forum for cooperative societies, increasing mutual benefit;
5. Producer and consumer cooperative societies based on the principle of mutual benefit, based on mutual purpose, principle and value, mutual relationship;

፮. ሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን የግብይት ፍላጎት በመለየት ከአምራች ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ዘላቂ የግብይት ትስስር ውል በመግባት የመተግበር ፤

፯. ከቁጠባና ብድር ውጪ ያሉ ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ገንዘባቸውን የመቆጠብ፤

፰. ኅብረት ሥራ ማህበራት ስለ ፋይናንስ ግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርትና ስልጠናን ፣ስለ ቁጠባና ኢንቨስትመንት ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ግንዛቤ የማግኘት፤

፱. በተለያዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ በተለያየ ምክንያት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ገንዘቦች ሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት እርስ በእርስ የመበዳደር፡፡

**፻፵፫. ኅብረት ሥራ ማህበራት ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት**

፩. የኅብረት ሥራ ማህበራት ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር የሚኖራቸው የግንኙነት ዓይነቶች በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለፅ ሆኖ በዋናነት በትምህርትና ስልጠና፣ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ በሰው ኃይል ቅጥር እና በቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር እና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ሊገናኙ ይችላሉ፤

፪. ከባለድርሻ እና አጋር አካላት በኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚከፈቱ የትምህርትና ስልጠና ማዕከላት የሚያስፈልጉ በጀት እና ልዩ ልዩ ግብዓቶችን በማሟላት፣

6. Consumer cooperative societies identify the marketing needs of the members and implement them by entering into a permanent marketing relationship contract with the producer cooperative societies;
7. Other cooperative societies other than savings and loans to save their money in savings and loan cooperative societies;
8. Cooperative societies provide education and training on financial awareness, savings and investment from savings and loan cooperative societies;
9. Borrowing from each other by facilitating the use of funds that have been kept idle for various reasons in different cooperative societies.

**143. Cooperative Societies' Communication with Stakeholders and Partners**

1. The types of communications cooperative societies have with stakeholders and partners are defined in their bylaws and can be related mainly to education and training, infrastructure construction, human resource recruitment and technology and knowledge transfer and other issues;
2. By meeting the budget and various resources needed for the education and training centers opened by the cooperative societies from the stakeholders and partners;

፫. ከባለድርሻ እና አጋር አካላት የኅብረት ሥራ ማህበራትን በጽህፈት ቤት፣ በመጋዘን፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ በዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ግንባታ እና ሌሎች የመሰረተ ልማት ችግሮችን በማቃለል ዙሪያ ፣

፬. ከባለድርሻ እና አጋር አካላት በራሳቸው አቅም ሰራተኛ መቅጠር ለማይችሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ባለሙያዎችን በመቅጠር ኅብረት ሥራ ማህበራት በተማረ የሰው ኃይል እንዲመሩ በመደገፍ፣

፭. የኅብረት ሥራ ማህበራት እና አጋር አካላት ስለሚሰጡት ድጋፍ ከኮሚሽኑ ወይም ከጽህፈት ቤቱ ጋር በመግባባት መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል አሥራ አስራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፻፵፬ ስለተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች

፩. የልዩ ልዩ ኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር ፲/፪ሺ፲፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፤

፪. የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የአረጃጀትና የአሰራር መመርያ ቁጥር ፯/ ፪ሺ፲፫ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

፫. ማንኛውም ካቢኔው ያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

3. From stakeholders and partners, cooperative societies in offices, warehouses, modern technology, modern information system construction and alleviating other infrastructural problems;
4. By hiring various experts for the cooperative societies who cannot hire workers from the stakeholders and partners, supporting them to lead the cooperative societies with an educated workforce.
5. Cooperative societies, stakeholders and partners should work in coordination with the commission or the office regarding the support they provide.

## PART ELEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 144. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Establishment and Operation of Various Cooperative Societies Directive No. 10/2023 is repealed by this regulation;
2. Financial Savings and Credit Cooperative Societies Establishment and Operation Directive No. 7/2021 is repealed by this regulation.
3. Any Regulation and Directive or Customary Practices of the Cabinet which are inconsistent with this regulation shall have no effect.

**፻፴፮ <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፻፴፯ <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከወጣበት ከሰኔ &1 ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፣

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም አዲስ አበባ**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**



**136. <u>Duty to Cooperate</u>**

Any person shall be duty-bound for the implementation of this Regulation.

**137. <u>Effective Date</u>**

This regulation shall enter into force as of this 28th day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABEBE DESA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**